ቸው ፤ ብዙ መከራ እንደሚደርስባቸው አሰቡ ። ስለዚህ እኛ አንጓ
ዝም፤ አንቺም ብቻሽን አትኬጂም በማለት እምቢ አሏት ። "እኔ
እኬዳለሁ ብቻዬን አይደለሁም እግዚአብሔር ከእኔ ጋራ ነው ፤ የሚ
ገጥመኝም ቢኖር ነጻነት ወይም ሞት ነው።" በማለት ጉዞዋን ቀጠለች።
ቀን ቀን ጢሻ ውስጥ እየተኛች ሌሊት ሌሊት እየተጓዘች የባርያ አሰ
መላጬቹም እየረዷት ጉዞዋን ቀጠለች ። በመጨረሻ ፊላዳልፊያ ደረ
ሰች፤ በዚያም ነጻነቷን አገኘች። በፊዳልፊያም እንደ ደረሰች ኑሮዋ
ተስተካክሎ በደሞዝ ተቀጥራ መሥራት ጀመረች።

ሀሪዬት ተብማን ወደ ፔንሲልቫንያ ኬዳ ራሷን ከባርነት ነጻ
ከወጣች በኋላ "አንደር ግራውንድ ሬይል ሮድ" ተብሎ በሚታወቀው
የድብቅ የማመላለሻ ምስጢራዊ ዘዴዎች በመጠቀም ብዙዎች ወገኖ
ቿን ወደሰላማዊውና ነጻነት ወዳለበት ሰሜኑ ክፍል ማውጣት አለብኝ
ብላ ተነሳች።[113] የመጀመሪያው ጉዞዋን ያደረገችው ወደ አደገችበት
ከተማ ቦልቲሞር ነበር ። በዚያም የእኅቶቿን ልጆች ፤ የእከስቶቿን
ልጆች አንድ ወንድሟን ሌሎችንም አገልጋዮች አጓጉዛ ነጻ አወጣች።
ከጊዜ ወደ ጊዜ የማስመለጥ ዘዴ ልምዱን አካበተች ። ጓደኞቿን እያ
ስተባበረች ዋሻ ለዋሻ ፤ ጥሻ ለጥሻ እያሽሎከለከች ሳትፈራ እየደበ
ቀች ወደሰላማዊ ቦታ በሰሜን በሚገኙ ግዛቶች እና ካናዳ ብዙዎች እን
ዲወጡ አድርጋለች። 90 ጊዜ ተመላልሳ በደቡብ ክፍል ድረስ ወርዳ
እያስመለጠች ነጻ አውጥታለች። ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን ይህ ጉዳይ የባ
ርያ ባለአባቶችን አስቆጣ፣ አበሳጨ።

መንግሥት ባርያ ንግድ በ1850 ቢያስቆምም በጌቶቻቸው ሥር
ያሉትን ባርያዎች እንዲያመልጡ መርዳት የሚያስቀጣ መኾኑን ገለጸ፤
ማንኛውም ሰው ባርያን በቤቱ አስጠግቶ ሲረዳ ቢገኝ ንብረቱና ቤቱ
እንደሚወረስ ፤ የእርሻ ቦታውና ከብቶቹ እንደሚወረሱ ሕግ አወጣ ፤
ባርያ ሲያመልጥ የሚይዙና የሚሰልሉ ሰላዮች አዘጋጀ ። ሀሪዬት
ይህን በደንብ ተረዳች። ነገር ግን የማስመለጫ ዘዴዎች ብዙ ነበራት።
ከተያዙባት ለሌላው ማስተማሪያ ማስፈራሪያ እንዲኾኑ ጀርባቸው
እስከሚተለተል እንደሚገረፉም ታውቃለች። ለዚህም ጥንቃቄ ታደርግ
ነበር።

ሀሪዬት በአጠቃላይ ወደ 300 ሰዎችን በማውጣትዋ የደቡብ
የባርያ ከበርቴ ባለርስቶች ተበሳጩ። በሜሪ ላንድ ግዛት በማስታወቂያ
ሰሌዳ (ፖስተር) ላይ በኹሉም ቦታ ፎቶግራፏ ተለጥፎ እርሷን በሕ

[113] Susan Altman., *p., 256*



ይወትም ወይም ሞታም ይዞ ላቀረበ $40,000 ዶላር ሽልማት ለመስጠት
በጋዜጣ ጭምር አወጡ።[114] ጊዜውም ከ1850 እስከ 1860 ነበር። ነገር
ግን ማንም ሰው አላገኛትም ። በወገኖቿ የተሰጣት ቅጽል ስሟ ሙሴ
ነበር። ይህም ማለት እንደተገለጸው ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን ከግብፅ
ምድር ከባርነት ከጨካኙ ፈርኦን ነጻ ያወጣ መሪ ነበረ፤ እሷም ብዙዎ
ችን ከስቃይ ከለቅሶ ስላወጣች በሙሴ መሰሏት።

የባርነትን አገዛዝ የሚቃወመው አብርሃም ሊንከን፥ የዩናይትድ
እስቴት ኦፍ አሜሪካ ፕሬዚደንት ኾኖ ከተመረጠ በኋላ ሀሪይት ተብ
ማን የውሕደቱ ጦርነቱ ሲጀመር አገልግሎት እንድትሰጥ ተፈቀደላት።
በመጀመሪያ ነርስ ኾና አገለገለች ከዚያም ለጦሩ ሰላይ በመኾን አገል
ግላለች ። ከጦርነቱ በኋላ 48 ዓመት ኖራ ዕድሜ ጠግባ መጋቢት 10
ቀን 1913 በ93 ዓመቷ ሞተች።[115]

ይህ ሰውን በሰው መግዛት በሰብአዊነትም ይኹን በሃይማኖት
አይደገፍም የተባለው የነጻ ማውጣት እንቅስቃሴ (አቦሊሽኒስት ሙቭ
መንት) የመጀመሪያው የሰብአዊ መብት እንቅስቃሴ ተብሎ ይጠራል።
በደቡብ ግዛት በሚፈጸመው ግፍ በሰሜኑ ያሉት ብዙዎች አይደሰቱም
በጣም ብዙ ክርክሮች ተደረጉ ። በዚህም የተነሳ ከ1820 እስከ 1840
ድረስ ወደ 75,000 ሺህ የሚደርሱ በባርነት ቀንበር ውስጥ ይኖሩ የነ
በሩ ጥቁሮች በድብቅ በተለያየ መንገድ አምልጠው ወደሰሜኑ ግዛቶች
እና ካናዳ ገብተዋል ። ነገር ግን ገና ያልተለቀቁና ለቅሷቸው ያልቆመ
ብዙዎች ነበሩ።

## መዕራፍ ፮
## ሰሜን እና ደቡብ የሕዝቦች ጦርነት

የፈርዖን ልብ ደነደነ ፤ ሕዝቡን ለመልቀቅ እምቢ አለ።
(ዘፀአ. 5 ፤ 7፥14)

በቅዱሱ መጽሐፍ ታሪክ እንደምንረዳው ፈርኦን እስራኤላውያን ባሮ
ችን ለመልቀቅ ያልፈለገው ጡብ የሚሠራና ሌላውም የጉልበት ሥራ
ይቆማል ብሎ በመፍራት ነው። የነዚህ አገልጋዮች ጉልበታቸውን እና
ሥራቸውን ይፈልግ ስለነበር ትንሽ ከቦዘኑ አሠሪዎች በጣም አድርገው

[114] Harry Smith., *p., 151*
[115] PBS HOME VIDEO Alfre Woodard *Underground Railroad*

በጅራፍ ይገርፏቸው ነበር ። በቅዱስ መጽሐፍ ለዚህ የሚነገር ታሪክ አለ።

> ራሔል የምትባል ሴት ባሏ ሞቶ በሱ ተተክታ ለጡብ የሚኾን ጭቃ በእግሯ እንድታቦካ ተደረገች፤ ፀንሳ ስለነበረ አስወረዳት ደንግጣ ቆማ ፅንሱን ብታይ ከጭቃው ጋር አብረሽ እርገጭው ጡቡን ያጸናዋል ብሎ እየገረፈ ያሠራት ጀመር። በዚህ ጊዜ "የእስራኤል አምላክ በዚህ ሰማይ የለህምን?" ብላ ምርር በማለት አልቅሳ እንባዋን ወደሰማይ ረጨች ፤ ለቅሶዋ በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰማ ፤ እግዚአብሔርም ለሙሴ ተገልጾ የሕዝቤን መከራ አይቻለሁ ጩኸታቸውንም ሰምቻለሁ ፤ ስቃያቸውንም አውቄአለሁ፤ አድናቸዋለሁ፤ አለው። (ዘጸ. 3፥7 ፤ ማቴ. 2፥18 ፤ ወንጌል ትርጓሜ.)።

እስራኤላውያንን እግዚአብሔር ጎበኛቸው፤ መሪ ረዳት ሙሴን አስነሳ። ትግሉ የፈርኦን እና የእግዚአብሔር ኾነ፤ በኋላ ፈርኦን ድል ተደረገ።

እንደዚሁም ኹሉ አሜሪካ ብዙ ፈርኦኖች ልባቸው ደንድኖ ሀብት ለማግኘት ከፍተኛ መንሰፍሰፍ ላይ ስለነበሩ ። ዐይናቸውን ጨፍነው ብዙ አይነት ግፍ ፈጽመዋል ፤ ምንም አይነት ሕግ ቢወጣ ላለመልቀቅ እምቢታቸውን ገለጹ። በሕገ መንግሥቱ የሰፈረ ፤ እንዲሁም በነጻነት አዋጁ ላይ የተገለጸ "ኹሉም የሰው ዘር የተፈጠረው በእኩል ነው" የሚለው ቃል በተግባር አልታየም።

በ1835 በደቡብ ባፕቲስት ፣ ሜተዲስት እና የፕሬስቤተርያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ይህ ጉዳይ በሐሳብ ከፋፈላቸው። አንዳንዶቹ በባርነት ይዞ ማሰቃየት እርኩስ ነገር ነው በማለት ይሰብኩ ጀመር።[116] ስለዚህ የሰሜንና የደቡብ የሕዝቦች የርስ በርስ ጦርነት ዋና መነሻ የባርነት ሥርዓትን ተቃውሞ በየአቅጣጫው በመነሳቱ ነው።

የባርያ ንግድ 1850 በዋና የመንግሥት አስተዳደር ከተማዋ በዋሽንግተን ተወስኖ ሲወገድ በሰሜኑና በደቡቡ ክፍለ አገሮች በጣም ከፍተኛ የኾነ ልዩነት ተፈጠረ። በተጨማሪ የበለጠ እንዲቀጣጠል ምክንያት የኾነው ባርነትን አጥብቆ የሚጠላው አብርሃም ሊንከን ለአሜሪካ ፕሬዘዳንትነት ኾኖ በመመረጡ ነው።

በ1860 ላይ በሰሜኑ የሚገኙ ነዋሪዎች ወደ 20 ሚሊዮን ይደርሱ ነበር ። እነዚህ የሰሜኑ ክፍል ነዋሪዎች ፋብሪካዎች ያሏቸው

[116] **Lutz Norma Jean**., *p., 19*



ናቸው ። ጥጥ በማሽን እየፈተሉ ለልብስ የሚኾን ጨርቃጨርቅ እንዲሁም የወፍጮ ፋብሪካ የመሳሰሉት ነበራቸው ። ሀብታቸው ከደቡብ ያላነሰ ሀብት ነበር ። ብዙዎችም በሰሜኑ ክፍል የፋብሪካ ሥራ ለመሥራት ከባርነት ያመለጡት ጭምር ከየአቅጣጫው እየኼዱ ይኖሩ ነበር።

በደቡብ የአሜሪካ ባለሀብቶች ባብዛኛው ገበሬዎች ሲኾኑ ወደ ሰባት ሚሊዮን የሚደርሱ ናቸው ፤ በባርነት ቀምበር የያዟቸው ደግሞ ወደ 4 ሚሊዮን የሚደርሱ አገልጋዮች ነበሩ።[117] በደቡብ ክፍል ብዙ ሰዎች ከአፍሪካ የተለመደውን የባርያ ንግድ በማካኼድ ወይም ገንዘብ ማትረፍ የሚችሉ ሰብሎችን በማምረት (Cash Crops) ንግድ እያጧጧፉ ይኖሩ ነበር ። በእርሻ ቦታቸው ላይ ባርያዎች ትንባሆና የጥጥ እርሻ ላይ ሲሠሩ ይውሉ ነበር። በዚህም የተነሳ ባርያ መግዛትንና ማስገባትን የሚከለክለውን በኰንግረንስ ሕግ እንደገና በ1857 ወጣ ። ነገር ግን ባርያ ዜጋ አይደለም ስለዚህ ነጻ መውጣት አይችልም በማለት የአገሪቱ የበላይ ፍድር ቤት እምቢ አለ ፤ ብዙ ክርክር ተካኼደ ። በሰሜኑ ባርነት ሰውን እንደ ዕቃ መግዛት እንዲያበቃ የሚል ሐሳብ ቀረበ። የደቡብ የባርያ ሀብታም ባላባቶች ኢኮኖሚያቸውን የሚነክ ስለ ኾነ ፈሩ፤ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ይበልጥ መከፋፈል እና መጣላት ጀመሩ።

በዚህ ዘመን (በ1850) ዐዳዲስ የእምነት ግሩፕ (Sects) መፈጠር ጀመረ። ሞርሞኒዝም ፣ ፐርፌክሺኒዝም ፣ ሚሊሪዝም (ሰሸን አድቬንቲስት) የሚባሉ ከተለመደው ትምህርት በጣም የራቁ ሰብስቦች ተፈጠሩ ። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ግን በአይሪሾች፣ በፈረንሳዮች፣ ትገለገል ነበር ። በተጨማሪ ከላይ እንደተገለጸው የባርያ ሥርዓትን የሚቃወሙና የማይቃወሙት ክፍል በተፈጠረ ግጭት ብዙ መከፋፈል መጣ።

## (፩) ፲፮ኛው ፕሬዘዳንት አብርሃም ሊንከን (ባፕቲስት?)

ስለ አብርሃም ሊንከን ታሪክ ከማንኛቸውም ፕሬዘዳንት የበለጠ ብዙ መጽሐፍ ተጽፎለታል ። ከቤተሰቡ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የባፕቲስት የክርስትና እምነት ተከታይ ነው ። ከኹሉም የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች በጣም ሃይማኖተኛ እንደኾነ ይነገራል።[118] አንዳንዶቹ ደግሞ ሃይ

[117] **Jackie Staddon** *Baedeker's., p., 30*
[118] **Mark A. Noll & Nathan O. Hatch** *Christianity in America., p., 266*

ማኖተኛ አልነበረም የሚሉም አሉ። ኾኖም ግን አብርሃም ሊንከን በቅ ጽል ስሙ ታማኙ አቢ (Honest Abe) ይባላል።

አብርሃም ሊንከን በ1809 ከደሀ ቤተሰብ ተወለደ ፤ አባቱ ማን በብና መጻፍ የማይችል አናጢ ነበር ። ስምንት ዓመት ሲሞላው ዲርት ፍሎር ከሚባለው የትውልድ ቦታው ወደ ኢንዲያና ከቤተሰቡ ጋር በመኾን ኼደው መኖር ጀመሩ፤ መንፈሳዊ መኾን የጀመረው ገና በእናቱ እቅፍ ላይ እያለ ነበር ፤ በየቀኑ እናቱ በቃሏ የምታንበለብለ ውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ይሰማል ፤ እሱም እንደ ጨዋታ እያደ ረገ በቃሉ ያጠና ነበር ። ይህች ተወዳጅ እናቱ ናንሲ ሀንከን ዘጠኝ ዓመት ሲሞላው ሞተችበት። ታላቅ እኅቱ ሣራና እሱ ከአባታቸው ጋር በመኾን ኑሯቸውን ይገፉ ጀመር። ከጥቂት ዓመታት በኋላ አባታቸው አግብታ የፈታችና ሦስት ልጆች ያላትን ሣራ ጆንሰንን አገባ ፤ እሷም ለቤተሰቡ መልካም ኾነች። አብርሃምንም በችሎታው ታበረታታውና ትወደው ነበር። እሱም ስለእሷ በዚህ ዓለም ምርጥ ጓደኛዬ ናት ይላት ነበር ። መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የቃል ጥናት ከእሷም አጠና።

አብርሃም 16ዓመት ሲሞላው ቁመናው ረዥም ቀጭንና ጠንካራ ኾነ ። ሥራ ወዳድ በመኾኑ ለመሥራት የሚመርጠው የሥራ አይነት አልነበረውም ። የግሮሰሪ ጸሐፊ የባቡር ጣቢያ ሠራተኛ ፤ ወታደርና የግብርና ባለ ሙያ ኾኖ ሠርቷል ፤ መጽሐፍ ማንበብ ከመውደዱ የተነሳ እየደጋገመ በማመላለስ ያገኘውን የወዳደቀ ወረቀት በማንሳት የሚችለውን ያኽል ከማንበብና ከማጥናት አልቦዘነም ነበር።[119] በዚህም ራሱን አስተምሯል።

አብርሃም በሚሲሲፒ ወንዝ ከኦሀዮ ወደ ኒው ኦርሌአንስ በጀ ልባ ላይ እንዲሠራ ተቀጥሮ ሰዎችን ሲያጓጉዝ ሳለ ከሀብታሞቹ የባርያ ባላባቶች የጠፉ ባርያዎችን ደርሰውባቸው በመያዝ በሰንሰለት አስረው በጅራፍ እየገረፉ፣ እየደበደቡና እንዳይለያዩ እንደ ከብት አንገታቸው በቀንበር ጠምደው፤ እጃቸው በሰንሰለት አስረው እየነዱ ሲወስዱ አየ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ባርነትንና የባርያ ባለቤቶችን ጠላቸው ፤ ባርነትን ለማስቆም ለመታገል የሚያስችለውን ሕግን ማጥናት ፈለገ ። በ1836 የአሜሪካ ሕግ እንዲያጠና እና ልምምድ እንዲያደርግ ከመንግሥት ፈቃድ ተሰጠው ። እሱም ከሌሎች የጥብቅና ሙያ ካላቸው ጋር በመኾን በፈረስ ከመንደር መንደር ፤ ከአገር አገር መዘዋወር ጀመረ። በክርክሩ ሰውን የሚያሳምን ጥበብ የተሞላበትና ዐዲስ ሐሳብን የሚያ

[119] George Sullivan., *2001*



ፈልቅ ሰው ኾነ ። 30 ዓመት ሲሞላው ብቻውን ቤተ ክርስቲያን በሌለ በት ከእስፕሪንግ ፊልድ በጣም ያልራቀ ነው ሳሌም በሚባለው ቦታ ኑሮውን ጀመረ።

ተቃራኒው የፓርቲ ቡድን በ1843 በፖለቲካ ተቀባይነት ለማሳ ጣትና በሕዝብ ዘንድ እንዲጠላ በሃይማኖቱ እምነት እንደሌለው ተደርጎ ሊከራከሩት ሞከሩ ። እሱም በፖለቲካ ሊያጠቁት እንደ ኾነ በመረዳት ፖለቲካውን ቀየር አድርጎ ክርስቲያን መኾኑን ተናገረ።

> እኔ ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈው ትክክል መኾኑን አምና ለሁ፤ ነገር ግን የማንኛውም የእምነት ቡድን ተከታይ አይደለ ኹም፤ እያለ ይናገር ነበር።[120]

አብርሃም ኅዳር 4 ቀን 1842 በእስፕሪንግ ፊልድ ሜሪ ቶድ የምትባል የከበርቴ ልጅ አገባ ። እሷም የኤጲስቆፓል ቤተ ክርስቲያን አባል በመኾኗ ዘወትር የጸሎት አገልግሎቱን ስትከታተል እሱም አብሮ ይከ ታተል ነበር ። ቀስ እያለ የቤተሰቡ ቁጥር በመጨመር የዐራት ወንዶች ልጆች አባት ኾነ።[121] በ1847 የዋሀግ ፓርቲ ተወካይ ኾኖ ለኮንግረስ ተመረጠ፤ ጥሩ ፖለቲከኛ ኾነ ። ነገር ግን እንደ ገና ወደ እስፕሪንግ ፊልድ ኢሊኖይስ በመመለስ ሕግን በደንብ ለማወቅ ወስኖ በጥሩ ኹኔታ ጥናት አደረገ፤ በኢሊኖይስ ዝነኛ ጠበቃ መኾኑ ታወቀ።

አብርሃም በ1850 2ኛ ልጁ ኤድዋርድ ሞተበት ፤ በዚህ በልጁ ሞት ሐዘን ስለገባው የፕርስቤተርያን ቄስ እስሚዝ ዘወትር ያጽናናው ነበር ። በኋላም የቅርብ ጓደኛ ኾነው። ብዙ ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር በመ ኾን ወደ ፕርስቤተርያን ቤተ ክርስቲያን በመኼድ ይጸልዩ ነበር።

አብርሃም በ1855 ለኹለተኛ ጊዜ ሐሳቡን ወደፖለቲካ አደረገ "ካንሳስ ኔብራስካን አክት"[122] የተባለውን የኢሊኖይስ ሴናተር ዳግላስ ያወጣውን ሕግ ባለመደገፍ ድምጹን አሰምቶ ተቃውሞውን አሰማ ። በ1858 ከቀድሞው የዋሀግ ፓርቲ ወጥቶ የባርነት አገዛዝን ተቃዋሚ ወደ ነበረው ሪፐብሊካን ፓርቲ በመግባት መሪ ኾነ። ይህ የሪፐብሊካን ፓርቲ የሰውን በሰው መግዛትን የሚቃወመው ድርጅት ነበር።[123] ዲሞ

[120] PBS HOME VIDEO *Abraham Lincoln Collection 1994*

[121] Harry Smith., *p., 147*

[122] KANSAS -NEBRASKA ACT

[123] ሪፐብሊካን ምልክት ዝሆን ሲኾን ። የዲሞክራቲክ ደግሞ የአህያ ምልክት ነው ። በአኹኑ ጊዜ ለአሜሪካ ፕሬዘዳንትነት የሚወዳደሩት እነዚህ ፓርቲዎች ብቻ ናቸው። የቀድሞው የዋሀግ ፓርቲ የሚባለው አልቀጠለም ።

ክራት የነበረው የሴናተር አባል ዳግላስን በመቃወም ከፍተኛ ክርክር አደረገ ፤ ክርክሩ ዝነኛ አደረገው። ለዚህም የረዳው መጽሐፍ ቅዱስ በማንበቡ እና ሃይማኖተኛ በመኾኑ ነው።

> እግዚአብሔር ምርጥ ስጦታን መጽሐፍ ቅዱስን ለሰው ልጆች ሰጠ። ሰው በዚህ መጽሐፍ ከዓለም አዳኝ ጋራ ይገናኛል፤ ይል ነበር።[124]

አብርሃም በኅዳር በ1860 የሪፓብሊካን ፓርቲ ፕሬዚዳንት ኾኖ ተመረጠ። ቀጥሎም በጥር በ1861 የአሜሪካ 16ኛ ፕሬዚዳንት በመኾን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እጁን ጭኖ ቃለ መሐላውን ፈጸመ። እንደ ተለመደው በተመረጠ በስድስት ሳምንት ውስጥ የፕሬዚዳንት ቢሮውን ያዘ፤ የባርነት ሥርዐትን በግልጽ መቃወም ጀመረ። የባርያ ሥርዐትን የሚፈልጉ የደቡብ ግዛቶች መመረጡን ተቃወሙ ። በሰሜኑ ግዛትና በደቡቡ ግዛት መካከል ከፍተኛ ልዩነት ተፈጥሮ የእርስ በእርስ ጦርነት ተጀመረ ። ዋና መነሻው ደቡቡ ክፍል በእርሻ መሬቶቻቸው ላይ በባርነት ቀምበር የሚያሰቃዩዋቸውን ሰዎች ነጻ ለማውጣት በመፈለጋቸው ነው ። ይህንንም ትግል የሚደግፉት በደቡብ በባርነት ወጥመድ ያሉት ግማሾቹ እያመለጡ ወደ ሰሜኑ ገቡ ። ሌሎቹ ከረዥም የመራራው የባርነት የስቃይ ዘመን ነጻነትን ለማግኘት ጸሎት ይጸልዩ ነበር።

በአብርሃም ሊንከን ውሳኔ ያልተሰማሙ የደቡብ ሀብታሞች አልተደሰቱም። እንዲያውም እያንዳንዳቸው ግዛቶች (እስቴቶች) ከውሕደቱ እየወጡ የራሳቸውን ነጻነት አዋጅ ማወጅ ጀመሩ። በመጀመሪያ የደቡብ ክፍል የካሮላይና ግዛት ተገንጥሎ ከውሕደቱ ወጣ ። ዋናው ምክንያት የባርያ ሥርዓቱን ለመልቀቅና ባርያን ነጻነት ለመስጠት ባለመፈለግ ነው ። በዚህ የተነሳ ሌሎቹም የደቡብ ግዛቶች ተከትለው ተገንጥለው ለመውጣት ትግል ጀመሩ።

> ሚሲሲፒ፣ ፍሎሪዳ፣ አላባማ፣ ጆርጂያ ፣ሉዊዚያና፣ ቴክሳስ ፣ ቨርጂንያ፣ አርካንሳስ፣ ኖርዝ ካሮላይና እና ቴነንሲ ተከተሉ።

በአላባማ ግዛት በሞንትጎምሪ ከተማ ላይ ታላቅ ስብሰባ አድርገው ራሳቸውን በራሳቸው "ኮንፌደሬት እስቴስ ኦፍ አሜሪካ"[125] ብለው ሰየሙ። ራሳቸውን ማስተዳደር ቀጠሉ ፤ መደቡ ቀይ የኾነ ባንዲራም አዘጋጁ ። ይህን ባንዲራ ኖርዝ ካሮላይና በአንዳንድ ቦታዎች የሚኖ

[124] **Mark A. Noll & Nathan O. Hatch.**, *p., 267*
[125] **CONFEDERATE STATES OF AMERICA**



ሩት አንዳንድ ነጮች እስከ ዛሬ ድረስ ታሪካችንን አንለቅም ብለው በታሪካዊነቱ ይዘውት ይገኛሉ።

በዚህ የደቡቦች መከፈል የተነሳ አለመግባባቱ ቀጠለ። ሰሜኖች በደቡብ ግዛት ያሉት ተገንጥለው ራሳቸውን የተለየ አገር ያደርጋሉ ብለው አላሰቡም ነበር ። በዚህ አሳፋሪ የባርነት ሥርዓት የተነሳ በመጀመሪያ በ1776 የነጻነት አዋጅ ከታወጀ በኋላ፣ ለኹለተኛ ጊዜ በአሜሪካ ታሪክ የርስ በርስ ጦርነት ሚያዚያ 12 ቀን 1861 ተጀመረ። አብዛኛው ጦርነት የተጀመረው በደቡብ ግዛት ውስጥ ነው።

## (፪) የርስ በርስ ጦርነት

> እርስ በእርሷ የምትለያይ ቤት አትጸናም ትፈርሳለች ፤ (ማቴ. 12፥25 ፤ ሉቃ. 11፥15)

ይህ ቃል ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን ስለውሕደቱ እና ስለፓርቲው የተናገረው የንግግሩ መክፈቻ ነበረ ። የርስ በርሱ ጦርነት ከመነሳቱ በፊት ስለ አገር አንድነት ብዙ ሰባኪዎች ይሰብኩ ነበር ። ከነዚህም ውስጥ የታወቀው ሰባኪ ዳዋይት መዲ (1837 –1899) የሚባለው ሰው ብዙ ተከታዮች ነበሩት ። ይህ ሰባኪ ስብከቱን የጀምረው የሰንበት ትምህርት ቤት ሕፃናትንና ወጣቶችን በማሰባሰብ በቺካጎ ከተማ በጣም ድህነት ካጠቃው ሰፈር ውስጥ ነበር ። ቀስ እያለ ተከታዮቹ በዙ ፤ በእስታዲዮም ውስጥ የሚያደርገውን ስብከቱን ለመስማት ከ12 ሺ በላይ ሰው ይሰበሰብ ነበር ። በወንጌል ስብከት ጦርነቱ እንዳይደረግ ለማስቆም ሞከሯል ፤ ግን አልኾነም ጦርነቱ ቀጠለ ።

በሰሜኑ ክፍል ብዙ ጀግኖች፣ እንዲሁም መሣሪያ፣ መድፍ ፣ ጥይት የሚሠሩባቸው ፋብሪካዎች ነበሯቸው ። በተጨማሪ ለአሜሪካ ምንጊዜም የማይገኝ ታላቅና ተወዳጅ መሪ ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን ነበር። እሱም ለጦርነቱ ፈቃደኛ የሚኾኑ ሰዎችን ጠየቀ አሰለፈ። በፈቃደኝነት ለጦርነቱ 75,000 ሰዎች ቀርበው አጭር ስልጠና ተሰጧቸው ተዘጋጁ።[126]

ደቡቦች ለብሪታንያ የሸጡት ጥጥ በጣም ብዙ ሀብት አስገኝቶላቸዋል። የባርያን ነጻነት የማይፈቅዱት ዋናው ምክንያት የኢኮኖሚ ገበያቸውና ሀብታቸው እንዳይቀነስባቸው መኾኑ የታወቀ ነው። ፕሬዚዳንት አድርገው የመረጡትም ሰው ጀፈርሰን ዴቪስ ይባል ነበር ።

[126] **Harry Smith.**, *p., 149*

በጣም ምርጥ የኾኑ ወታደሮች ነበሯቸው ። ከነዚህ ውስጥ ታዋቂው ሮበርት ኢ. ሊ ይገኝበታል ። ሮበርት ኢ. ሊ በመጀመሪያ አብርሃም ሊንከን ለውሕደቱ ጦር መሪ እንዲኾን የመረጠው ጀንራል ነው ። ነገር ግን የትውልድ ቦታው ቨርጂኒያ በለነበር ለትውልድ አገሩ በማድላት ከደቡብ ክፍለ ጦር ጋር ተቀላቀለ። ደቡቦች ባርያዎቻቸውን በጦርነቱ እንዲካፈሉና ሰሜኑን እንዲወጉ ፈቃድ ሰጥተው አሰለፏቸው።

በዚህ በባርያ ሥርዓት ምክንያት የተነሳው የርስ በርስ ጦርነት መከፋፈላቸው አመቺ ኹኔታ ፈጥሮ አውሮፓውያን እንዳያጠቋቸው የግድ አንዱ ክፍል በኀይል ተቆጣጥሮ መያዝ አለበት የሚል ሐሳብ ነበር። ጦርነቱን በቀላሉ እናሸንፋለን የሚል ሐሳብ በኹለቱም አቅጣጫ ነበር ። ኹለቱም ክፍሎች ይህን ጦርነት እግዚአብሔር የፈቀደው ነው ብለው ያምናሉ ። ለዚህ ጦርነት መሰለፍ ሰማዕትነትና ቅዱስ መኾን ነው ይሉም ነበር ። ኹለቱም ክፍሎች በተለያየ መንገድ ለራሳቸው እንዲስማማ አድርገው ይተረጉሙ ነበር ። መጽሐፍ ቅዱስ ተሸክመው የጦርነት መዝሙር እየዘመሩ ይጓዙ ነበር። በእግዚአብሔር እናምናለን (IN GOD WE TRUST) የሚለው የኹለቱም መፈክር ነው ። ከአባቶቻቸው ሲወርድ የመጣ ትልቁ መሣሪያቸው ነበር። ጥቂሮች የመጽሐፍ ቅዱስ ሰባኪዎች በጣም ይሰብኩ ነበር።[127] ለማንኛውም ጦርነቱ እየገፋና እየተዛመተ ኼደ የመጀመሪያው ጦርነት ቡል ራን እና ማንሳስ በሚባለው በቨርጂንያ ግዛት ላይ ግጥሚያው ተካኼደ ። በዚህ ጊዜ የሰሜኑ የውሕደቱ የጦር ኃይል ተሸነፈ። ሰሜኖች ሊሸነፉ የቻሉበት አንዱ ያለግዛታቸው ስለኼዱ እና ደቡባውያኑ መሽገው ስለጠበቋቸው ነበር።


በሰሜኖቹ ወገን የተሰለፈው የውሕደቱ (የዩናይትድ እስቴት) ጦር ወታደሮች ሚያዚያ 19 ቀን 1861 የደቡብ ባሕር ወደቦችን ዘጉ። ባስደናቂ እና በተሳካ ኹኔታ ኮንፌዴሬት እስቴስ ኦፍ አሜሪካንን በማሸነፍ ይመሩ ጀመር። በመጀመሪያም ኒው ኦርልኢንስ ያዙ ። በጣም ታዋቂ የኾኑት ኹለቱ የሰሜኑ አዝማቾች ጀንራል ዩልየስ ግራንት እና ጀንራል ሸርማን ነበሩ። በጀንራል ሸርማን የሚመሩ 60,000 ወታደሮች ከአትላንታ ተጉዘው ጆርጂያ በመግባት ወደ አትላንቲክ የባሕር ጠረፍ ደርሰው የኮንፌድሬሽኑን መንግሥት ለኹለት መሐል ለመሐል ቆርጠው

[127] Jeffrey B. Webb, *the complete Idiot's Guide to Christianity. ,p., 48*



ያዙ። ጦሩም ይመራበት የነበረው የውሕደቱ መዝሙር "በእግዚአብሔር እናምናለን" የሚል ነበር።

የካቲት 20 ቀን 1862 አብርሃም ሊንከን ዊሊያም የሚባለው ልጁ ሞተበት። በዚህ የተነሳ በጣም አዘነ ። በእግዚአብሔር ላይ እምነቱ የጠነከረ ኾነ ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ባለመቋረጥ በእጁ መጽሐፍ ቅዱስ ይታይ ነበር ። ይህም የበለጠ ለሰው ልጆች ርኅራኄ እንዲያድርበት አድርጎታል ተብሎ ይነገራል።



A book-lover all his life, Abraham Lincoln reads to his youngest son, Tad. Lincoln always remembered a book he had read about another president, George Washington.

አብርሃም ሊንከን እና ልጁ ቴድ

አብርሃም ሊንከን በአንድ ወቅት ለጓደኛው ደብዳቤ ሲጽፍ ፤[128]
መጽሐፍ ቅዱስ በማንበቤ ብዙ ተጠቅሜያለሁ። እስቲ አንተም በመንፈስና በእምነት አንብበው። ያለጥርጥር በሕይወት ዘመን ኹሉ የተሻለ ሰው ኾነህ ትኖራለህ ፤ እንደ ተከበርከም ታልፋለህ ።
ይህ ስለቅዱስ መጽሐፍ የገለጸው አገላለጹ መንፈሳዊ ሰው እንደነበረ ያመለክታል።

[128] Michael Collins &Matthew *The story of Christianity* p. 186 --187

## (፫) የነጻነት ሕግ እና አዋጅ

አብርሃም ጦርነቱ እንገፍግፎት ነበር። በሰሜኑ ሜሪላንድ እንቲ
የታም በምትባለው ቦታ በ1862 ድል አደረጉ ። በዚህ የድል ቀን አብ
ሃም ሊንከን የጻፈውን ወዲያው በዐዲስ ዓመት ጥር 1 ቀን 1863 ዩናይ
ትድ እስቴትን የተቃወሙትን የታገላችኹ፣ በባርነት ቀምበር የተያ
ችሁ ኹሉ ነጻ ናችሁ የሚል ጽሑፍ አነበበ፤ ይህም ንግግሩ "ኢማንሲ
ፔሽን"[129] (ሕግ እና አዋጅ) በመባል ይታወቃል፤ ለ250 ዓመታት በዩናይ
ትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ በባርነት ተይዘው ይኖሩ የነበሩ ጥቁሮች ነጻ
ወጣችሁ ተባሉ፤ የዘመናት ለቅሷቸውና ጸሎታቸው ተሰማ። ለብዙዎቹ
ጥቁሮች እውነት አልመሰላቸውም ነበር።

በሰሜኑም ክፍል እንዲሁ የተሟላ የእኩልነት ሥርዓት ጎልቶ
ብዙ ባይታይም የአንድነቱ ጦርነት አፍሪካን አሜሪካን በወታደርነት
ሙያ በመሰለፋቸው ዕድል ተከፍቶላቸዋል ። እስከ 200,000 የሚደር
ሱት ግለሰቦች በባሕር ኃይልና በወታደርነት ሙያ ማዕረግ እያገኙ አ
ልግለዋል ። በመጀመሪያ ጦርነቱ ሲጀመር ከነጮቹ ጋር ጎን ለጎን ተሰ
ልፈው እንዳይዋጉ ይደረግ ነበር። እንዲኹም ደሞዛቸው በግማሽ ከነ
ጮቹ ያንስ ነበር ። ሥራቸውም ምግብ ቀቃዮች ፤ ጠጉር አስተካካ
ዮች ፣ መቃብር ቆፋሪዎች ፣ ተላላኪዎች ፣ ሰላዮች ፣ በጦርነቱ የቆሰ
ሉትን ቁስለኞች የማጠብና የማከም ሥራ ነበር ። ከጦርነቱ ፍጻሜና
ከአዋጁ በኋላ ግን ኹለቱም ክፍሎች አንድ ዐይነት ክፍያ ይደረግላ
ቸው ጀመር።

## (፬) ጸሎት እና የጌትስበርግ ንግግር

**በስሜ የተጠሩ ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ ፊቴ
ንም ቢፈልጉ ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ በሰማይ ኾኜ እሰ
ማለሁ ። ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ። ምድራቸውንም
እፈውሳለሁ (መጽ. ዜና መዋ. 7፥14)።**

ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን ከሚያዚያ 30 እስከ ግንቦት 1 ቀን 1863
ብሔራዊ የጸሎትና የጾም ቀን (United cry of the Nation) እንዲኾን
ሕዝቡን ጠየቀ ። ሕዝቡም በታዘዘው መሠረት የኹለት ቀን ጸሎት
አደረገ ። ቀደም ሲል የአሜሪካ መሥራች አባቶች በ1775 የግዛቱ

[129] EMANCIPATION PROCLAMATION



ተወካዮች ከብሪታንያ መንግሥት ቅኝ ግዛት አስተዳደር ለመውጣት በተሰበሰቡ ጊዜ በጾም በጸሎት ለዐራት ቀናት ቆይተው ነበር ። ይህ ባህል ቀጥሎ በአሜሪካ ለአገር ደኅንነት የጸሎት ቀን ተወስኖ በየዓመቱ ይከበራል።

ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን ጸሎትና ጾም ካስደረገ ከኹለት ወር በኋላ በፔንሲልቫንያ ጌትስበርግ ሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ እስከ ሐምሌ 3 ቀን 1863 በተደረገ የጦርነት ውጊያ የደቡብ የኮንፌዴሬት ጦር ሠራዊት በጄንራል ሮበርት ኢ. ሊ የሚመራው ጦር በድል ተመታ

በድጋሚ ሐምሌ 4ቀን የነጻነት በዓል በሚከበርበት ቀን በደቡብ ሚሲሲፒ ወንዝ የደቡቡን የኮንፌዴሬት ጦር ለኹለት ከፈሉት። በዚህ ወቅት በጄንራል ዩልየስ ግራንት የውሕደቱ ጦር ቪክስበርግ ከተማን በመቆጣጠሩ በድጋሚ ድል ተቀዳጁ።

ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን እንደገና በሐምሌ 15 ቀን ለኃያሉ እግዚአብሔር የአንድ ቀን የጸሎትና የምስጋና ቀን እናቅርብ በማለት ለዜጎች ኹሉ አዋጅ እንዲታወጅ አደረገ።

በዚሁ ዓመት ኅዳር 19 ቀን 1863 አብርሃም ሊንከን ስለ ጀግኖች ወታደሮችና በጦርነቱ ስለሞቱ ጀግኖች ወታደሮች በሰሜኑ ጌትስበርግ በመኼድ ንግግር አደረገ። ይኼም ንግግር የጌትስበርግ ንግግር በመባል ይታወቃል። ከፕሬዚዳንቱ ንግግር ውስጥ እንዲህ የሚል ይገኝበታል።

> የዛሬ ሰማንያ ሰባት ዓመት አባቶቻችን ለዚህች ምድርና ዐዲስ ሕዝብ በነጻነት እንዲኖር በማሰብ በስምምነት ሐሳብ በማቅረብ "ሁሉም የአዳም ዘር የተፈጠረው በእኩል ነው" በማለት ሕይወታቸውን ሰጡ። እኛም ያሕዝብ ወይም ሌላ መኾናችንን ተፈቱንን። ስለዚህም ለዚህ ታላቅ የእርስ በእርስ ጦርነት በቃን።...
>
> ................
>
> ...ይህ ታላቅ ተግባር ሕያው ኾኖ ይኖራል ፤ በከንቱ አይቀርም። ይኸም ሕዝብ በእግዚአብሔር ሥር የሚተዳደር ሕዝብ ነው። ዐዲስ የነጻነት ልደት አግኝተናል ። ይህም የነጻነት ልደት የሕዝቦች መንግሥት በሕዝቦች ለሕዝቦች ስለኾነ ከምድረ ገጽ አይጠፋም።

በማለት ንግግር ካደረገ በኋላ በቁጥር 23 ለሚኾኑ ጥቁሮች (አፍሪካን አሜሪካን) የጀግንነት የክብር ሜዳልያ ሸለመ። ወዲያው የደቡብ የጦር መሪ የኮንፌዴሬት ጄንራልሮበርት ኢ. ሊ በትውልድ ቦታው በኮንፌዴሬት ዋና ከተማ በቨርጂንያ ሪችመንድ ከተረፈው የጦር ሰራዊቱ ጋር

እንደደረሰ በጦርነቱ መቀጠሉ ጥቅም የሌለው መኾኑን በማመን እጁን ሰጠ፤ ጦርነቱም አበቃ።

ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን በድጋሚ በ1864 ተመረጠ ፤ በዚህ የምርጫ ጊዜ የተናገረው ይህ ጦርነት የእግዚአብሔር ዓላማና ምክንያት ተጨምሮበታል የሚል ነበር ።[130]

## (፭) የፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን ሞት

ልክ ጦርነቱ ካበቃና ጄንራል ሮበርት ኢ. ሊ ከተማረከ ከ5 ቀን በኋላ ሚያዚያ 14 ቀን 1865 የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ የስቅለት በዓል (Good Friday) በሚከበርበት ቀንአሳዛኝ ኹኔታ ተፈጠረ ። ይኼውም የነጻነት እና የኩልነት መብት ተከራካሪ የነበረው አብርሃም ሊንከን ከባለቤቱ ጋራ ፎርድ በሚባለው ትያትር ቤት ኼደው ትርኢት በማየት ላይ እያሉ ጆን ዊልኬስ ቡዝ የሚባል ሰው ከበስተ ኋላው እየዳኸ ኼዶ ራሱን በሽጉጥ ተኩሶ መታው ፤ በማግሥቱ ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን ሞተ ። ይህም ለሕዝብ ተገለጸ ፤ የነጻነት እና የእኩልነት መብት ተከራካሪው ዝነኛው አብርሃም ሊንከን በመሞቱ ለተከታዮቹ አሜሪካውያን ሐዘኑ ከፍተኛ ኾነ።

ይህ የፕሬዚዳነት አብርሃም ሊንከን ታሪክ በመጠኑም ቢኾን ከኢትዮጵያው መሪ ከነበሩት ዐፄ ቴዮድሮስ ጋር ይመሳሰላል ይባላል። ኹለቱም የሞቱበት ዘመን የሦስት ዓመት ልዩነት አለው። አብርሃም ሊንከን 1865 ሲሞት፤ ቴዎድሮስ የሞቱት 1868 ነው። ዐፄ ቴዎድሮስ መሳፍንቱ ለጥቅም የከፋፈሏትን ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ፤ በሌላ በኩል ወደ ኢትዮጵያ የሚስፋፋትን የግብፅና የቱርኮች ወረራ ለማቆም ታገለዋል ። ሥልጣኔን ለማስገባት በፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን እየተረዱ መድፎችንና አዳፍኔዎችን አሠርተዋል ። የጦር መሣሪያ የሚሠሩ ሙያተኞችን ከብሪታንያ ለማግኘት ለንግሥት ቪክቶርያ መልእክት ልከው ነበር። በተፈጠረው ጠብ ዐፄ ቴዎድሮስ የብሪታንያ ቆንሲል እና ሌሎችን የውጭ አገሮች ዜጎች በቤተ መንግሥቱ አሠሩዋቸው። ስለዚህ የብሪታንያ መንግሥት ጦር ላከ፤ የጦሩ መሪ ጄንራል ሮበርት ናፒር ጥቅምት 12 ቀን 1868 ዙላ ላይ ሰፍሮ በሚያዝያ ወር 1868 ቴዎድሮስ እመሸጉበት መቅደላ አምባ ላይ ደረሱ ። ጦርነቱ ሚያዚያ

[130] The second Inaugural address one of the most theologically intense political speeches in America "the Almighty has his own purposes …"



ሦስት ቀን ተጀመረ ። የብሪታንያ ወታደሮች ቴዎድሮስን ሊማርኩ ሚያዚያ ስድስት ቀን 1868 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ ማግስት የማእዶት ዕለት ምሽጉን ጥሰው ገቡ ። ቴዎድሮስ ከመማረክ ሞትን መርጠው ከብሪታንያ ንግሥት ቪክቶሪያ ከዐራት ዓመት በፊት በተላከላቸው ሽጉጥ ጭንቅላታቸው ላይ አድርገው ጠጥተው ሞቱ።

ከአብርሃም ሊንከን ጋር የሚያመሳስላቸው ሊንከን አሜሪካንን አንድ ለማድረግ የታገለ ሲኾን ፤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ታግለዋል ። የሞቱበት ዘመን የሦስት ዓመት ልዩነት ሲኖረው ዕለቱም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በአል በሚከበርበት አካባቢ ነው፤ ይህም የሦስት ቀን ልዩነት አለው። ኹለቱም የሞቱት ጭንቅላታቸው በሽጉጥ ተመቶ ነው፤ በጠላት አልተማረኩም።

ከአብርሃም ሊንከን በኋላ በቦታው የተተካው ፕሬዚዳንት አንድሪው ጆንሰን ጠንካራ ፕሬዚዳንት አልነበረም።[131] ሰሜኑንና ደቡቡን በአንድ ላይ ለማገናኘት ለማዋሐድ አንድ ለማድረግ አልጣረም። በዚህም የተነሳ በሕዝቡ መካከል ቁጣና አለመግባባት እንዲሁም በአብዛኛው የጥቁሮች ሕዝቦች የመብት ጥያቄ እንደገና መነሳት ቀጠለ።

የእርስ በእርስ ጦርነቱ ካለቀ በኋላ በሰሜን ያሉት አብያተ ክርስቲያናት መደበኛ ትምህርት ቤት፣ የሰንበት ትምህርት ቤት እየከፈቱ ጥቁሮችን ማስተማር ጀመሩ ። በዐሥር ዓመት ውስጥ ብዙ የጥቁሮች አብያተ ክርስቲያናት ተስፋፉ ። የጥቁርና የነጭ ቤተ ክርስቲያን በማለት ክፍፍሉ ቀጠለ። በባርነቱ ዘመን በእርሻ ቦታ ያንጐራጕሩ ያቀነቅኑ የነበረ ፤ የምስጢር የመነጋገሪያ ፤ ማስጠንቀቂያ እና የማምለጫ መመሪያ የነበረው በቅኔ እና በግጥም የተዋበው እንጉርጉሮ እና ዘፈናቸው ፤ ከነጻነት በኋላ በአደባባይ ወጥቶ የተዋጣላቸው ዘፋኞችና ዘማሪዎች እንዲኾኑ አደረጋቸው ። በስሜት መዘመር ፤ እየጮኹ እንደፉከራ ከወዲያ ወዲህ እየተወናጨፉ መስበክ የተለመደ ባሕርይ ኾኖ ቀጠለ

በተገኘው ነጻነትና በአዋጁ መሠረት ቦታ ገዝተው፣ ቤት ሠርተው ፣ ትዳር መሥርተው ከፈለጉም ተከራይተው መኖር ጀመሩ።

ነጮቹ የደቡብ ከበርቴዎች ባርያዎች ነጻ በመውጣታቸው በጣም ተበሳጩ ። ከፍተኛ ቂም ያዙ ፤ በፍጹም የኩልነት መብት እንደ ነጮቹ ሊሰጧቸው አልፈለጉም ። ነጭ የተመረጠ ፍጡር ነው

[131] Lutz Norma Jean., *p.. 25*

ብለው ስለሚያምኑ ቂሙ እና ጥላቻው ለቀጣዩ መቶ ዓመት ያኽል ሲንገዳገድ ቆየ።

## (፮) ኩ ክሉክስ ክላን

በነጻነቱ ያልተደሰቱት ዘረኛ ነጮች ጥቁሮች ነጻነት መውጣትና መለቀቅ የለባቸውም ይሉ ነበር። አሜሪካ የፕሮቴስታን አገር ናት እና የሌላ እምነት ተከታይ ሊኖርባት አይችልም በማለት፤ ካቶሊካውያን፣ አይሁዳውያን ጭምር ይቃወሙ ጀመር።

የአድማውንም ስም ኪክሎስ አሉት ። ይህም ማለት በግሪክ ቋንቋ ክብ ማለት ነው ። በዚህ የተነሳ ኩ ክለክስ ክላን (Ku Klux Klan)[132] በሌላ ስሙ ደግሞ "የክርስቲያን እንቅስቃሴ መለያ ሰብስብ"[133] የሚባለው ቡድን አብርሃም ሊንከን ከሞተ በኋላ በ1866 ተመሠረተ። ይህ ቡድን በደንብ የተጠናከረበት ጊዜ ከጦርነቱ ማብቂያ ጀምሮ እስከ በ1870 ድረስ ባለው ጊዜ ነው።

የኩ ክላክስ ክላን መሥራቾች ስድስት ጓደኛሞች ነበሩ ። እነ ዚህም ጂሚ ክሮው (ጄምስ) ሪቻርድ ሪድ ፣ ካልቪን ጆናስ ፣ ጆን ሌስተር፣ ፍራንክ ማክኮርድ እና ጆን ኬኔዲ የተባሉ ዝርያቸው ከእስኮትላንድ ሲኾን በውሕደቱ ጦር በውጊያ ሽንፈት ያገኛቸው የደቡብ ነዋሪዎች ናቸው። በሰሜኑ ጦር መሸነፋቸው በጣም አበሳጭቷቸዋል። ስለዚህ አድማ በማደም ፤ ጥቁሮችን በመደብደብ ፤ በድብቅ መደራጀት ጀመሩ ። መንግሥት በ1871 ሕግ አውጥቶ ለማስቆም ሙከራ አደረገ ፤ ነገር ግን ይህ ሕግ ሊገታቸው አልቻለም ። እንዲያውም ጥቁሮች በትምህርት ቤት፣ በትያትር ቤት፣ በባቡርና በአውቶቡስ በተለየ ቦታ እንዲኾኑ ከእኛ እንዳይደባለቁ በማለት ወሰኑ፤ የነጭ ሆቴል ወይም ምግብ ቤት (ሬስቶራንት) ሲገቡ ከነጭ ጋር የማያገናኝ ኾኖ የተለየ ቦታ እንዲሰጣቸው አደረጉ ። የነጭ ጠጉር ማስተካከያ ቤቶች ለብቻ ፤ ሽንት ቤቶች ለብቻ፤ ውሃ መጠጫ ለብቻ፤ ጥቁሮች በነጭ ቲያትር ቤቶች እንዳይገቡ ተደረገ ። ይህ አሳዛኝ ተግባር ሰግርጌሽን ሎው ወይም ጂሚ ክሮው (ጄምስ) ሕግ በመባል ይታወቃል።[134] ይህም

[132] **Ku Klux Klan** = Greek word for circle *–kyklos* – and threw in a nod to their Scottish roots and their clans to come up with the Ku Klux Klan. The supposed goals of the group: mischief and amusement.


[133] CHRISTIAN IDENETITY MOVEMENT

[134] **Lutz Norma Jean.**, *p. 30*



በመላው ደቡብ የአሜሪካ ክፍል ተቀባይነት አገኘ ። የጄምስ ክሮው ሕግ (James Crows Law) በጽሑፍ በወረቀት ላይ የሠፈረ ሕግ አይደለም። በነጭ የበላይነት (በዘረኝነት) መንፈስ ላይ የተመሠረተ ነበር ። በእንዲህ ያለ ኹኔታ እስከ 1954 ድረስ ለአንድ ክፍለ ዘመን ያህል ቆየ።

የኩ ክላክስ ክላን አባላት ዘንድ ጥቁር ማለት በትምህርቱ የማይገፉ አእምሮው ደካማ አድርገው ስለሚያምኑ ትምህርትም እንዲማሩ አይፈቀድም ። ፕሬዚዳንትን ኾነ ሴናተሮችን የመምረጥ ዕድል አይፈቅዱላቸውም። ጥቁሮች ምንም እንኳን መብት አላችሁ ቢባሉም ስለሚፈሩ እነሱም አይሞክሩትም ። ልምረጥ እንኳን ቢሉ መሐይም ነህ በማለት ይከለክሏቸው ነበር ። በአንደኛው ዓለም ጦርነት ወቅት ነጻነት ወደ አለበት፤ በጅራፍ መገረፍ ወደ ሌለበት ከግብፅ ወደ ከነዓን ምድር ለነጻነት እንኺድ እያሉ ከደቡብ ወደ ሰሜን በብዛት እንደቀድሞው መጓዝ ጀመሩ ። በሰሜኑ ነጻነት ብቻ ሳይኾን ፋብሪካ የበዛበት ሥራ ለመሥራት የሚመች በመኾኑ ብዙዎች ከደቡብ ፈለሱ። በተለይ በኒው ዮርክ ብዙ ዘፋኞችና የሙዚቃ አቀንቃኞች ተፈጠሩ። እዚያም ቢኾን ሙዚቃቸው ይወደድ እንጂ በጥቁርነታቸው የተገለሉ ነበሩ።



**በደቡብ የተደራጁት ኩ ክላክስ ክላን**

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ይህ የፕሮቴስታንት ድርጅት በ1915 እንደገና በጣም ተደራጅቶ በአትላንታ ጆርጂያ መንቀሳቀስ ጀመረ ።

የአባላቱ ብዛት ከዐራት ሚሊዮን እስከ ዐምስት ሚሊዮን ደርሶ ነበር።
ማታ ማታ በሚሰባሰቡበት ጊዜ የክርስትናና የሰላም ምልክት የኾነውን
መስቀል ከተማ ያሉት ኹሉ እንዲያዩት በማለት በከፍተኛ ቦታ በተ
ራራ ላይ በመውጣት ተክለው ያቃጥሉ ነበር ። ማንነታቸው እንዳይታ
ወቅ ነጭ ልብስ በመልበስ ለዐይናቸው ብቻ የሚያዩበት ቀዳዳ አውጥ
ተው (ጉጉት ወፍ መስለው) በከተሞች በሚያስፈራ ኹኔታ ይጓዛሉ ።
የጥቁሮችን ቤተ ክርስቲያኖችን ያቃጥላሉ። እንዲሁም የጥቁር ሰባኪያ
ችን እና መሪዎችን በጅራፍ በጭካኔ በመግረፍ እና በመደብደብ እየገ
ደሉ በባሕር ዳር ይጥሉ ነበር። ክርስቲያን ነን ቢሉም የክርስትናን ቃ
የማያስተውሉ ፤ ሰይጣናት ያደሩባቸው ጨካኞች ነበሩ (ማቴ. 13፥19)።
በዚህ ጭካኔ መንገድ የሰውን ልጅ ማሰቃየት ፣ መደብደብ ፣ ከስፈ
ገም ምክንያት ፈጥሮ በገመድ አንጠልጥሎ በግንድ ላይ መስቀል
በጊዜው የተፈጸመ ግፍ ነበር ። በዚህ የጭካኔ ተግባር በመግረፍ የሚ
ሲሲፒ ግዛት አንደኛ ነበር ። በኹለተኛ ደረጃ በመግረፍ የሚታወቅ
ጆርጂያ ግዛት ነበር።

ከእርስ በእርስ ጦርነቱ በኋላ በአሜሪካ ግዛት ከ1882 እስከ
1960 ባለው ጊዜ ውስጥ 4735 ጥቁሮች በግርፋት ድብደባና በመሳሰለ
ሕይወታቸው ባሰቃቂ ኹኔታ አልፏል። ኾኖም ግን ይህ በጥናት ቀረበ
እንጂ ሪፖርት ያልቀረበለት ያልተገለጸ ከዚህ የበለጠ ይገኛል።[135]
አኹንም በአሜሪካ ግዛቶች አልፎ አልፎ እንደበፊቱም ባይኾንም ጥ
ቶች የዚህ የኩ ክላክስ ክላን ቡድን አባላት አለን የሚሉ አሉ ።
አንዳንዶቹ ደግሞ በዕድሜ የገፉት አባላት በፈጸምነው መጥፎ ተግባር
እና ጭካኔ ተጸጽተናል የሚሉም አሉ።

## ምዕራፍ ፺

## በዐዲሲቷ አሜሪካ ስደተኞች

**እናንተ በግብፅ ምድር መጻተኞች ነበራችኹና ስደተኛውን አት
በድሉት።
ግፍም አታድርጉበት፤ መበለቲቱንና ድሀ አደጎቹን አታስጨንቋ
ቸው (ዘጸአ. 22፥21 ፤ ዘዳግ. 10፥19)።**

በቅዱስ መጽሐፍ በመከራ ከአገራቸው የፈለሱ ስደተኞች እንደነበሩ
ተጠቅሷል ። እስራኤላውያን በግብፅ ስደተኞች ስለነበሩ ስደተኞችን

[135] Toby Mac & Michael UNDER GOD p.108 (1995)



እንዲረዱ እንጂ እንዳይንቋቸውና እንዳያስቸግሯቸው ግፍ እንዳይፈ
ጽሙባቸው ተገልጿል ። ሄሮድስ መንግሥቴን የሚቀናቀን ንጉሥ ተወ
ለደ ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊያጠፋው በመፈለጉ ጌታም
ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ከእናቱ ጋር ተሰዷል ። በረሀብ ምክንያት የእስ
ራኤል ልጆች ብዙ ጊዜ ወደ ግብፅ ተሰደዋል፤ ይኼም በግብፅ የዓባይ
ውሃ ሳያቋርጥ ስለሚፈስባት ድርቅ አግኝቷት አያውቅምና ስደቱ በዚ
ያን ጊዜ ወደዚያ ነበር ። ይህ በቅዱስ መጽሐፍ የተጠቀሰ እውነታ
ነው።

ክርስቶፎር ኮለምበስ አሜሪካንን ካገኘ ጀምሮ አሜሪካ ምድር
የተሰደዱ ሰዎች ከአፍሪካን አሜሪካውያንና ከኢንዲያን ሕዝቦች በስ
ተቀር፤ ሌላው ማለትም አውሮፓውያን ጭምር በትውልድ አገሩ የሚደ
ርስበት የፖለቲካ አመለካከት፣ የሃይማኖት፣ የዘር ልዩነት፤ የኩልነት
መብት ሲነፈገው እና ይኽን ለማስከበር የሚያስችለው ጉልበት ሲያጣ
ነጻት ወደሚያገኝበት ቦታ ይሸሻል ። በተጨማሪ በኑሮ ችግር (በኢኮ
ኖሚ) የተሻለ ሀብት እናገኛለን በማለት ብዙዎች በአሜሪካ ምድር ገብ
ተዋል።

ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ አውሮፓውያን ፣ እስያ
ውያን ፣ አፍሪካውያን በዓለም ላይ ያሉት ነገዶች ኹሉ ፥ በድህነት
የሚኖሩ ሥራ ለማግኘት በተስፋ ከአገራቸው ፈለሱ ። እስፓኞች ፣
ቻይናዎች ፣ ኪዩባኖች፣ ቬትናሞችና ኮርያኖች የኑሮ ትግል ጀመሩ ።
በዚህ የብዙ ዘመን ኑሯቸው የአሜሪካ ዜጋዎች ኾኑ ። አሜሪካ የስደ
ኞች አገር ናት ። የሚሰደድ ኹሉ ሲሰደድ ንብረቱን መውሰድ ባይች
ልም የማንነቱን መለያ ምልክት ባህሉን ፤ የመንፈስ መጽናኛ ስለሚፈ
ልግ ያመልከው የነበረው እምነቱን ይዞ በመኼድ በዐዲሱ የመኖሪ
ያው ሥፍራ ይዞ መኖሩ የተለመደ ነው።

አሜሪካ ዛሬም እንደበፊቱ የተሻለ ኑሮ ፣ ሀብት፣ ለማግኘት
የሚመኝ ሰው ኹሉ ይኖርባታል። ይህም የአሜሪካ ሕልም (American
Dream) ይባላል ። ኾኖም አንዳንድ ጊዜ ይህ የብልጽግና ፣ የሰላም
ሕልም ለኹሉ ላይሳካ እና እንደ ጠበቁት ላይኾን ይችላል ። ከመስከ
ረም 11 ቀን 2001 ጀምሮ ፥ በኒው ዮርክ በሽብር ፈጣሪዎች በተፈጠ
ረው ከፍተኛ ጥፋት ሳቢያ ለዐዲስ ስደተኛ ሕጉ የጠበቀ ኾኗል ። ከዚ
ህም በላይ ስደተኛ አገሩን እስከሚለምድ ድረስ አይደላውም ።
"ለአገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ" ስለሚኾን በቀላሉ አይለምድም ፤ በዚህ
የተነሳ ብዙ ለቅሶና ሐዘን አለበት።

## (፩) በኒው ዮርክ የገቡ ስደተኞች

ኒው ዮርክ በዓለም ታላቅ ከሚባሉት ከተሞች አንዷ ናት ። በቅጽል ስሟ "ቢግ አፕል" ተብላ ትጠራለች ። በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቱሪስቶች ወደዚህች ከተማ ይጓዛሉ ፤ ሌትና ቀን ዕረፍት ሳይኖር የሚሮጥባት ከተማ ነች፤ በጣም ታላላቅ ሕንጻዎች አሉባት።

ቀደም ባለው ዘመን በ1609 ከአዎሮፓ የፈለሱት የዳች ዜጎች ሰፍረውባት ስለነበር "ኒው አመስተርዳም" በመባል ስትጠራ ኖራለች። በኋላ ግን በ1664 የብሪታንያ ንጉሥ ቻርለስ 2ኛ በብሪታንያ ይዞታ ሥር መጠቃለል አለባት በማለት ዮርክ በሚለው የእንግሊዝ አውራጃ ስም "ኒው አመስተርዳም" የሚለውን ሰርዞ "ኒው ዮርክ" ብሎ በቁጥጥር ሥር አደረጋት ። ግዛቱም ኒው ዮርክ ተብሎ ተጠራ።

በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ 47 ሚልዮን አውሮፓውያን የትውልድ ቦታቸውን ለቀው በዚህች የኒው ዮርክ ከተማ በኩል በማድረግ ዐዲስ ዓለም (አሜሪካ) ገብተዋል።[136] በኒው ዮርክ እና በሌላም ቦታ ተጉዘው የገቡት የዛሬ የአሜሪካ የነጭ ዝርያዎች የቀድሞ አባቶቻቸው የመጡት ከብሪታንያ (ከእንግሊዝ፣ ከአየርላንድ፣ ከእስኮትላንድና ዌልስ) ከኢጣሊያ ፣ ከፈረንሳይ፣ ከጀርመን፣ ከኔዘርላንድ ፣ ከፖላንድ ከሌሎችም አገሮች ነው ። እነዚህ ሰዎች ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው ገበሬዎች፣ የፋብሪካ ሠራተኞች እና የንግድ ሰዎች ነበሩ። እንደ ደረሱም ያላቸውን ኀይልና ጉልበት በመጠቀም በፍጥነት ማደግ እና መለወጥ ጀመሩ ። ፋብሪካዎች ገነቡ ፤ የአሜሪካ ከተሞች በፍጥነት ማሳደግና መስፋፋት ጀመሩ። በየዘመኑ የተፈጸሙ ኀስት ታላላቅ የስደት ማዕበላት የነበሩባቸው ዘመናት ነበሩ።

**፩ኛው የስደት ማዕበል** በ1815 እስከ 1860 ነበረ። በዚህ ዘመን ውስጥ 5 ሚልዮን ሕዝቦች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ከአየርላንድ ተሰድደው አሜሪካ ገብተዋል። እነዚህ የአየርላንድ ዜጎች (አይሪሾች) በእንግሊዙ ንጉሥ በሄንሪ 8ኛ ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መገንጠል ምክንያት ከእንግሊዝ ወይም ከአንግሊካን ፕሮቴስታንቶች ጋር ተቃቅረው ይኖሩ ነበር ። አየርላንዳውያን የሃይማኖቱ የበላይ ጠባቂው የሮም ፖፕ መኾኑን ተቀብለው የሚኖሩ ናቸው ። በዚህ

[136] Jackie Staddon., *p., 28*



ምክንያት አንግሊካን ፕሮቴስታንትና ካቶሊክ አማኞች ለብዙ ዘመን የእርስ በእርስ ጦርነት አደረጉ።

የብሪታንያ ነጉሥ የአይርላድን ቦታ ለኹለት ከፍሎ ሰሜኑን ለእንግሊዝ ፕሮቴስታንት ሰጠ ። ካቶሊካውያን አይሪሾች ቦታቸውን ለማስመለስ ብዙ ጦርነት ቢያደርጉም አልቻሉም ። እስከነ አካቴው ዊልያም ኦሬንጅ የሚባለው የብሪታንያ ንጉሥ በ1690 እንዳይንሰራሩ አድርጎ በጦርነት ወጋቸው። ከዚያ በኋላ ከፍተኛ ውጊያ አላደረጉም፤ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ግጭቱ አልቀረም ፤ ኑሯቸው ኹሉ የድኽነት ኑሮ ኾነ፤ ፕሮቴስታንቶቹ እንግሊዞች ሀብታም ሲኾኑ፤ ካቶሊክ አይሪሾች ድንጋይ በበዛበት በደቡብ ክፍል ድንች በማምረት ምርት ስላላገኙ እንዲሁም የድንች ምርታቸው በተመች (ተባይ) ስለተመታ ረሀብ አጠቃቸው ። ይህም ወደ አሜሪካ እንዲፈልሱ አደረጋቸው ።

ዋናው የፍልሰት ጊዜ ከ1846 እስከ 1848 የድንች ተምች አከታትሎ ምርቱን በመጥፋቱ ለኹለት ዓመት ከፍተኛ ረሀብ ኾነ። ገበሬዎች የተለመደውን ምርት ስላላገኙ በሚልዮን የሚቆጠሩ በረሀብ አለቁ ። ከረሀቡ መጽናት የተነሳ የባሕር ውስጥ ቅጠል (አልጌ) ይበሉ ነበር ። ጐረቤት እንግሊዞች የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ካልኾኑ በስተቀር ለካቶሊክ አይሪሾች በምግብ ሊረዷቸው አልፈለጉም። እነዚህም ካቶሊክ አይርሾች እንግሊዞችን ከመጥላታቸው የተነሳ እና በረሀብ ስለተጎዱ ኹለት ሚልዮን የሚኾኑ በጀልባ ተጉዘው ወደ አሜሪካ በስደት ገቡ ። በሚልዮን የሚቆጠሩትም በረሀብ አለቁ ። ወደ አሜሪካ ሲሰደዱም በጉዞ ላይ ብዙዎች አልቀዋል።[137] የተረፉት አሜሪካ ከደረሱ በኋላ ብዙዎቹ የሰፈሩበት ቦታ በሰሜኑ ክፍል ይበልጥ በኒው ዮርክ ከተማ ነበር ፤ በዚያ የካቶሊክ እምነታቸውን ይዘው በነጻነት ይኖሩ ጀመር ።

ይህ ከእንግሊዞች ጋር ያለው ቂም አልበርድ ብሎ እስከዛሬ ድረስ በካቶሊኩ ደቡብ አየርላንድና በሰሜኑ ፕሮቴስታንት አየርላንድ የክርስትና እምነት ተከታዮችጥላቻው እንደቀጠለ ለብዙ ዘመን ኖረ። በተለይ ሐምሌ 12 ቀን ፕሮቴስታንት ኦሬንጅ ሜን (Orange Men) የሚባለውን ዓመታዊ በዐል ሲከበር እና ሰልፍ ሲካኼድ ብጥብጥ ቀርቶ አያውቅም ነበር ። ይኹንና በቅርቡ የተካኼደው ምርጫ ኹለቱ ወገኖች የጥምር መንግሥት አቋቋመው አገሪቱን በታላቋ ብሪታንያ ፓር

[137] Patricia S. Daniels &Stephen G. B. *Almanac Of World History., p., 243*

ላማ አመራር ውስጥ ተካፋይ እንድትኾን የተቀየሰው መንገድ ይህን የረዥም ዘመን ጥላቻና ግብግብ የሚያስቀር የዐዲስ ታሪክ መጀመሪያ ምዕራፍ ይኾናል የሚል ተስፋ አሳድሯል።

በዚህ ስደት ዘመን ከብሪታንያ (ከእንግሊዝ፣ ከዌልስ እና ከእስኮትላንድ) ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ፤ ከጀርመን ደግሞ 1.7 ሚሊዮን ያህል ሉተራውያን ከተወለዱበት አገር ወጥተው ወደ አሜሪካ ተሰደው ገብተዋል ። በመቀጠልም እንደዚሁ በከፍተኛ ችግርና ረሀብ የተነሳ የኖሮዌይ ሕዝቦች ወደ አሜሪካ ተሰደዋል ። የኖሮዌ ሕዝቦች በረሀብ ስደት ከአየርላንዶች ቀጥሎ ኹለተኛ ናቸው ።

**፪ኛው የስደት ማዕበል** ከ1860 እስከ 1890 ባለው ዘመን ውስጥ ነው። በዚህ ዘመን 10 ሚሊዮን አውሮፓውያን ወደ አሜሪካ ገብተዋል ። እነዚህ በድጋሚ የበላይነትን የያዙት የብሪታንያ ነዋሪዎች እና የደቡብ የአይርላንድ ዜጎች እንዲሁም ጀርመናውያን ዜጎች ሲኾኑ የሰፈሩበት ቦታ በሰሜኑ ከተሞች ነው። በዚኽ ዘመን ግማሽ የኒው ዮርክ ነዋሪ በሌላ አገር ተወላጆች ተያዘ። ቺካጎ ፣ ሲኒሲናቲ ፣ ሚሊዋኪ ፣ ዲትሮይት እና ፊላደልፊያ በስደተኞች ተያዙ።

የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ጣሊያን፣ ሀንጋሪ እና ፖሊሽ የስደተኞች ቤተ ክርስቲያን አቋቋሙ ። የራሽያ ኦርቶዶክስ አማኞችም በ1794 በአላስካ ከገቡት ሌላ እንደገና በተጨማሪ በ1867 በዚሁ በአላስካ በብዛት ገቡ።

**፫ኛው የስደት ማዕበል** ፤ በ1890 እስከ 1924 ባለው ዘመን ውስጥ ነው። በዚህ በሠላሳ አራት ዓመት ውስጥ 15 ሚሊዮን ሕዝቦች ወደ አሜሪካ ገብተዋል። አብዛኛዎቹ የመጡት ከደቡብ እና ከደቡብ ምሥራቅ እንዲሁ ከምሥራቅ አውሮፓ ነው ። ከኢጣልያ የፈለሱት ዐምስት ሚልዮን የሚኾኑ ስደተኞች ሲኾኑ እነዚህም የሮማ ካቶሊክ አማኞች ናቸው። በአኹኑ ጊዜ በኒው ዮርክ ሮም ከተማ ከሚኖረው የጣሊያ ነዋሪ የማይተናነስ የጣሊያን ስደተኞች ይኖራሉ ። የሚኖሩበትም ቦታ ሊትል ኢጣሊ ይባላል ፤ በዚሁ ቦታ ታላላቅ የምግብ ቤቶች ፤ ሱቆች አሏቸው ።






በአሜሪካ በኤሊስ አይላንድ
የጣሊያን ቤተሰቦች በስደት ሲገቡ።[138]

ከሚልዮን የሚበልጡ ደግሞ ከራሽያ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ከኮሚኒዝም ሥርዓት በመሸሽ ሃይማኖታቸውን ይዘው የተሰደዱ ናቸው ። የግሪክ፣ የአርመንያ፣ እና የዩክሬንያን ኦርቶዶክስ፣ የፖላንድ ካቶሊክ በአሜሪካ ቀደም ሲል ያልታዩ እምነቶች ተሰደው ሰፈሩ ። ከሌሎች አገሮች ማለት ከምሥራቅ ፣ ከደቡብ ምዕራብ አውሮፓ ሥራ እናገኛለን የመኖር ነጻነት ይኖረናል ብለው ተስፋ በማድረግ ከአገራቸው ፈለሱ።[139]

አሜሪካ እስከ በ1924 በሯን ሳትዘጋ ስደተኞችን አስገብታለች። ከዚያ በኋላ ግን የስደተኞች ቁጥርን መቀነስ አስፈላጊ ነው በማለት ሕግ ወጣ ። በመጀመሪያ ከአውሮፓ የፈለሱት ስደተኞች በኒው ዮርክ ኤሊስ ደሴት ሲደርሱ በሽታ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው እንዲሁም ሌላ ችግር እንዳለባቸው ይፈተሹና ይመረመሩ ነበር።

---

[138] Chronicle of 20th Century p. 1902
[139] **Jackie Staddon**., *p., 28-29*



የነጻነት ሐውልት
(፪) የአሜሪካ የነጻነት ሐውልት

የአሜሪካ የነጻነት ሐውልት[140] በሴት ምስል የተቀረጸች ከመዳብ የተሠራች ሐውልት ነች። ሐውልቷን የሠራው ፌዴሪክ ኦጉስቴ ባረተአልዲ ይባላል። ሐውልቷን የሠራው የእናቱን መልክ አስመስሎ ነው።

አሜሪካውያን ከብሪታንያ የቅኝ አገዛዝ ነጻነት የወጡበትን የመቶኛ ዓመት በዓል ለማክበር ሲዘጋጁ ፈረንሳዮች እንኳን ለዚህ አበቃችሁ በማለት ሐውልቷን አቆሙላቸው። ይህችን ሐውልት ያቆሙት ጥቅምት 28 ቀን 1886 ነው። የቆመችበትም ቦታ በኤሊስ ደሴት ነው።

ሐውልቷ ዘውድ ጭና፤ መጽሐፍ በግራ እጇ ይዛ፤ በቀኝ እጇ ችቦ ጨብጣ ቆማለች። 93 ሜትር ከፍታና እስከ ዘውዷ ድረስ ውስጥ ውስጡን 354 ደረጃዎች አሏት ። ዐሥራ ኹለት ሰዎችን በችቦው መጨበጫያ ዙሪያ ማስቀም ትችላለች፤ ነገር ግን ወደ እጇ ላይ አይወጣም። ከሐውልቷ ሥር ቤተ መዘክር (ሙዚየም)አለ ። ብዙዎች ስደተኞች ወደ አሜሪካ የገቡት በዚህች በውሃ በተከበበች ደሴት አካባቢ ነው ። ስለዚህ የእንኳን ደኅና መጣችኹ ምልክት፤ እንዲሁም ዐዲስ

[140]Statue of Liberty



የነጻነት ሕይወት በዐዲስ ዓለም ለማለት በሐውልት ላይ እንዲህ የሚል ተጽፏል "ድካምኽን ፣ ድህነትኽን ስጠኝ....." ይላል።[141] እሷን ለማየት ብዙ ጎብኚዎች (ቱሪስቶች) ከየአህጉራቱ ይጓዛሉ ። የአሜሪካ ጎብኚዎች ቅድመ አያቶቻቸው የገቡበት ቦታ ስለኾነ ታሪካቸውን ለማየት ከየግዛታቸው ወደዚህች ሐውልት ይኼዳሉ።

በዚህ ቦታ የቀድሞ ዐዲስ ስደተኞች አሜሪካ ሲገቡ ሃይማኖታቸውና ባህላቸውን ይዘው ነው። ኾኖም ግን ይህ ያልተለመደ ባህል እና ቋንቋቸው ከቀድሞዎቹ ነዋሪዎች የተለዩ ያደርጋቸው ነበር ። ይህ ብቻ አይደለም በኑሯቸው ድህነት ያጠቃቸዋል ፤ አብዛኛዎቹ በትምህርት ቤት ገብተው ሳይማሩ ይቀራሉ ። በዚህ የተነሳ በነዚሁ ቀደምት ነዋሪዎች ጥላቻና መጥፎ አስተያየት ይታዩ ነበር።[142]

በ1930 በአውሮፓ የሚኖሩ እና በተለይ ከጀርመን (በናዚ) የተሰደዱት አይሁዳውያን በከፍተኛ ቁጥር አሜሪካ ገብተዋል።[143] ከ1880 እስከ 1930 ድረስ በአጠቃላይ 27 ሚሊዮን ሕዝቦች ወደ አሜሪካ በስደት ገብተዋል።

አይሪሾች፣ ጣሊያኖች እና የምሥራቅ አውሮፓውያን በኒውዮርክ ፣ በቦስተን እና በቺካጎ ከተሞች እንዲሁም በምሥራቁ ወይም በመካከለኛው ምዕራብ በፋብሪካ ሥራ ላይ ተሰማርተው በስደት መኖር ጀመሩ ። እንግሊዘኛ ተናጋሪ ካልኾኑ አገሮች የደረሱት ደግሞ አብዛኛዎቹ እንግሊዘኛ ቋንቋ ተምረው ለማሻሻል አሜሪካውያን ኾነዋል። በአኹኑ ጊዜ ይህ የቀድሞው ስደተኛ ዝርያ ትውልዱ ወደ አራተኛ ደረጃ የልጅ ልጅ ወርዷል። እነዚህ ኹሉ የራሳቸውን ባህልና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ሥርዓታቸውን አክብረው ይዘው ይኖራሉ ። በአብዛኛው ከተሞችም ትንሿ ጣሊያን፣ ወይም ትንሿ የቻይና ከተማ የሚባሉ ይገኛሉ። የቻይና እና የጣሊያን ምግብ ቤቶች በየቦታው አሉ።

በሜሪላንድ ቦልቲሞር ትንሿ ጣሊያን (ሊትል ኢጣሊ) የምትባል መንደር ነበረች። በአኹን ጊዜ የቀድሞዎቹ መሥራቾች አልፈው ትውልዱ ተተክቷል የጣሊያኑን ቋንቋ የሚናገረው ጥቂቱ ተወላጅ ነው፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያናቸው ፣ ባህላቸው ፤ የምግብ ቤታቸው እንደተጠበቀ ነው ። ባንዲራም የጣልያንና የአሜሪካ በአንድነት በየበሩ ላይ

[141] **Stephanie Abraham H.**, *p., 332*
[142] (Prejudice)
[143] **Jackie Staddon.**, *p.. 29*

ይውለበለባል ። አብዛኛው የቀድሞው የአውሮፓ ስደተኞች አሜሪካ የገቡት በኒው ዮርክ በኤሊስ ደሴት በኩል አድርገው ነበር ።

## (፫) ከላቲን አሜሪካ የገቡ ስደተኞች

በአኹኑ ዘመን ብዙውን ቁጥር ይዘው የሚገኙ ስደተኞች የእስፓኝ ቋንቋ ከሚናገሩ አገሮች ከሜክሲኮ ፣ ከፖርቶሪኮ እና ከሌሎች ላቲን አሜሪካ አገሮች የመጡት ናቸው ። ከ1980 ጀምሮ እነዚህ ከደቡብ አሜሪካ ተጉዘው እስከ ዛሬ ድረስ እየገቡ ያሉት ስደተኞች ቁጥራቸው ከ25 ሚሊዮን በላይ ደርሷል።

ዛሬ በአሜሪካ ነዋሪ ውስጥ ከዐሥር አንዱ የእስፓኝ ቋንቋ ተናጋሪ ነው። ስለዚህም በኹለተኛ ደረጃ ከእንግሊዘኛ ቀጥሎ የሚነገረው የእስፓኝ ቋንቋ ነው ። እነዚህ ከደቡብ አሜሪካ ፈልሰው የገቡ ሰዎች የተመሰከረላቸው ጠንካራ ሠራተኞች እና ሥርዓት ያላቸው ሕዝቦች ናቸው። ይህም ሊኾን የቻለው አብዛኛዎቹ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ብርቱ አማንያን በመኾናቸው ነው የሚል ግምት አለ። የቦልቲሞር ከተማ ውስጥ ብሮድ ዌይ በተባለው ቦታ የነዚሁ የደቡብ አሜሪካ ተወላጆች የእስፓኝ ቋንቋ ተናጋሪዎች መናኸሪያ ነው ። በአጋጣሚ ይህ እነሱ የሰፈሩበት ቦታ የደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች ተመሥርቶ ለምእመናኖች አገልግሎት ይሰጣል።

## (፬) በካሊፎርንያ የገቡ ስደተኞች

በ1849 በካሊፎርንያ የወርቅ ማዕድን በተገኘ ጊዜ ብዙ ሰዎች ሀብት ፍለጋ ወደዚያ ተጓዙ። ይህ የወርቅ ማዕድን ተገኘ በተባለበት ወቅት ማዕድኑን ፍለጋ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማፈስ የተሯሯጡት ሰዎች አርባ ዘጠነኛዎቹ (ፎርቲ ናይነርስ)[144] የሚባል ስም ተሰጣቸው።

እነዚሁ ፎርቲ ናይነርስ የተባሉ ሰዎች በሌላው አጠራር ወርቅ ለማግኘት እሽቅድምድም ስለነበረ "ጎልድ ረሽ" በመባል ይታወቃሉ ። እነዚህ ከምሥራቁ ክፍል ተነስተው ማዕድኑን ለማውጣት የሚገሠግሡት ሰዎች የአገሩን ተወላጅ የኾኑትን ኢንዲያኖችን እየገደሉ እና

[144] (Forty niners) (Gold Rush)



እያስለቀቁ በመስፋፋት ነበር ። ዛሬ ካሊፎርንያ ከፍተኛውን የአሜሪካ ነዋሪዎች ቁጥር ይዛ የምትገኝ ግዛት ነች።

## (፭) ቻይናውያን በአሜሪካ

በ1865 ምሥራቅን እና ደቡብ ምዕራብን ለማገናኘት የባቡር መስመር እንዲዘረጋ ታሰበ። ከርስ በርሱ ጦርነቱ በኋላ ነጭ የጉልበት ሠራተኛ ለመሥራት ፈቃደኛ ባለመኾኑ ለዚሁ ሥራ በመጀመሪያ 50 ቻይናውያን ተቀጠሩ ፤ በኋላ ቀስ እያሉ እየተጠሩ በሰላማዊ ውቅያኖስ አቋርጠው ብዙ ቻይናውያን ለሥራ ገቡ። ግንቦት 10 ቀን 1869 የመጀመሪያው የባቡር መሥመር ከምሥራቅ ወደ ደቡብ ምዕራብ የአሜሪካ ጠረፍ (ከአትላንቲክ ውቅያኖስ እስከ ሰላማዊ ውቅያኖስ) የሚያገናኝ መሥመር ተዘርግቶ አበቃ። ይህን ድንጋያማ የኾነ ተራራ የበዛበትን እንዲሁም የኔቫዳ በረሀ ቋጥኞችን ሰንጥቆ የተዘረጋው የባቡር መስመር የተሠራው በይበልጥ ጥቂት የገንዘብ ክፍያ በሚሰጣቸው በነዚሁ ቻይናውያን ነበረ።[145]

ቻይናውያን እንዲህ አይነቱን የመንገድ ሥራ ለመሥራት የቻሉትም በተራራማው አገራቸው ቻይና መንገድ በመሥራት ልምድ ስለነበራቸው ነው ። ቀስ እያለ የቻይናውያን የስደተኛ ቁጥር 300,000 ሺ ደርሶ ነበር ። በዚህ የቁጥራቸው መጨመር የተነሳ ፤ መልካቸውና ባህላቸው ከአውሮፓውያን ዝርያ ለየት ያለ ስለኾነ በመጥፎ ዐይንና በጥላቻ ይታዩ ነበር። እንደ ጥቁር አሜሪካውያን እና እንደ አገሬው ተወላጅ ኢንዲያን ያህል እንኳን ሰብአዊ መብታቸው አልተከበረላቸውም ነበር ። እስከነ አካቴው በ1882 አሜሪካ ምድር እንዳይገቡ ተከለከሉ ። እነዚህ ቀደም ብለው የገቡት የአሜሪካንን የባቡር ድልድይ ሲሠሩ ኖረው በ1943 ከ75 ዓመት የስደት ዘመን በኋላ ዜግነት እንዲያገኙ ተፈቀደላቸው።

ዛሬ ቻይናውያን በኒው ዮርክ ከተማና በሎሳ አንጀለስ ከተማ በቁጥር ከፍተኛ የሚኾኑት ይኖራሉ ። በኒው ዮርክም በሎሳ አንጀለስ ስም ታላቅ መንደር አላቸው፤ ታላላቅ ሱቆች እና የምግብ ቤቶች አሏቸው። ቦታቸውም የቻይና ከተማ (ቻይና ታውን) በመባል ይጠራል።

[145] John Escott *California., p., 3*

## (፮) ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ

**በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን ? (ትን. ኤር. 13፥23)**

ከነቢዩ ኤርምያስ ትንቢት የምንረዳው ኢትዮጵያውያን የሚያስደንቅ የእግዚአብሔር ጸጋ ያላቸው ሕዝቦች መኾናቸውን ነው ። ምንም እንኳን የተለያየ ነገድ ቢኖርም የኢትዮጵያዊነቱ መንፈስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ጸጋ ነው። ራስን ለመግለጽ ወይም ለመደበቅ ቢሞክር እንኳን መታወቁ አይቀርም ። ኢትዮጵያውያን በባሕርያቸው ፣ በባህላቸው ፣ በማኅበራዊ ኑሯቸው ፣ በገጻቸው ፣ በውበታቸው ፣ የተለዩ ናቸው ፤ ይህ ጸጋ የተለየ ስለኾነ በአሜሪካም ኾነ በዓለም በየትኛውም ቦታ ቢኖሩም ኢትዮጵያዊ መልኩ ሊሰውር አይችልም ። ከማንኛውም ኅብረተሰብ ተለይቶ ይታወቃል።

ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያ መውጣት እና መኖር የጀመሩት ጣሊያን የኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ እና ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው ። የጣሊያ ጦርነት ሲጀመር ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በእንግሊዝ አገር በባዝ ከተማ ለዐምስት ዓመታት ያህል ኖረዋል።

በ1974 (1966 ዓ. ም. ) የኮሚኒዝም ሥርዓት ኢትዮጵያ ሲገባ ከፍተኛው ቁጥር ያለው ሕዝብ ካገሩ ወጥቶ በባዕድ አገር ይኖር ጀመር። ከነዚህ አገሮች አንዱና ዋናው የመሰደጃ ቦታ አሜሪካ ነበረ። ዛሬ በቁጥር ከፍተኛ የኾኑ ኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች በአሜሪካ የመንግሥት አስተዳደር ከተማ በዋሽንግተን ዲ ሲ ፣ በሎሳ አንጀለስ፣ በሲያትል፣ በኒው ዮርክ ፣ በዳላስ እና በአትላንታ እንዲሁም በመላው የአሜሪካ ግዛት እና ከተሞች ተሠራጭተው ይገኛሉ።

ዋና ከተማዋ ዋሽንግተን ዲ. ሲ. በቁጥር 113 የሚደርሱ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገርባት የተለያዩ የዓለም ሕዝቦች የሚኖሩባት ከተማ ነች። በአኹኑ ጊዜ በዚህ የመንግሥት ዋና ከተማ የዐማርኛ ቋንቋ በዐምስተኛነት ደረጃ የመግባቢያ ቋንቋ ኾኗል ። በየሆቴሉ በጽሑፍ ጭምር ይዘጋጃል ። እንዲሁም በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲሠራበት በማለት በከተማዋ ከንቲባ ተወስኗል ። ይህ የተወሰነበት



ቀን ሚያዚያ 21 ቀን 2004 ሲኾን በፊርማው ያጸደቀው ከንቲባ (ሜየር) አንቶኒ ዊልያም ነው ።[146]

በምህፃረ ቃል ዲ. ቪ. (ዳይቨርሲቲ ቪዛ) ፕሮግራም የሕግ መወሰኛው ምክር ቤት (ኰንግረስ) በ1990 ለውጭ አገር ዜጎች አሜሪካ ለመኖር ለሚፈልጉት የሎተሪ ዕድል አወጣ ፤ በዚህ ሎተሪ በየዓመቱ ከተለያዩ አገሮች 55,000 ሺ ሰዎች የመግባት ዕድል አላቸው ። ይህ ምክንያት ኾኖ በየዓመቱ ብዙ ኢትዮጵያውያን ዕድል እየገጠማቸው ይገባሉ ። በአጠቃላይ በተለያየ ምክንያት ወደ አሜሪካ የገባው የኢትዮጵያዊ ቁጥር በዋሽንግተን ዲ. ሲ. አካባቢ 110,000 ሺ ሲደርስ በመላው የአሜሪካ ግዛቶች በየሥፍራው የሚኖረው አንድ ሚሊዮን የሚደርስ መኾኑ ይነገራል። በዚህም ቁጥር ከአፍሪካ አህጉር ወደ አሜሪካ ከገቡት ከናይጄርያውያን ቀጥሎ ኢትዮጵያውያን በኹለተኛ ደረጃ ላይ መኾናቸውን በኢንሳይክሎፒዲያ ተመዝግቧል። በማኅበራዊ ኖሮ ረገድ ዕድር፣ ዕቁብና የጽዋ ማኅበር በሰፊው ይከኼዳል። አንዳንድ ጊዜም አለመግባባት ቢከሰትም ለማኅበራዊው ኑሮ ጠቀሜታ አለው።

በካሊፎርንያ ሎሳ አንጀለስ "ትንሿ የኢትዮጵያ ስትሪት" የሚል መንገድ በኢትዮጵያ ስም ተሰይሟል ። በዋሽንግተን ዲሲ እንደ ሎሳ አንጀለሱ ሊትል ኢትዮጵያ የሚል መንገድ እንዲሰየም ተጠይቋል ። በመንገዶቹ ዳርና ዳር መርካቶ ገበያና ሌሎችም የምግብ ቤቶች አገርን የሚያስታውሱ አሉ። ቁርጥ ሥጋ፣ ክትፎ፣ እንጀራ እንደልብ ነው ። ይህን የኢትዮጵያውያን እንጀራና ክትፎ ነ... የአሜሪካዊ ነዋሪው ሳይቀር ለምዶታል።[147] የዋሽንግተኑ የዱከም ምግብ ቤት (ሬስቶራንት) በጣም ታዋቂ ከኾኑት አንዱ ነው ። በኒው ዮርክ፣ በአትላንታ በሌሎችም ግዛቶች ብዙ ምግብ ቤቶች አሉ።

የዜና ማሠራጫ ጣቢያዎች ዋሽንግተንና በተለያዩ ግዛቶች ያሉትን ጨምሮ ከሃያ ያላነሱ የሬዲዮ ጣቢያዎች እና የቴለቪዥን ፕሮግራሞች ለኢትዮጵያውያን በያሉበት ግዛት ይተላለፋሉ ። ከእነዚህም ለምሳሌነት አንዱ አንጋፋው የአሜሪካ ሬዲዮ ቪ.ኦ.ኤ.፤ በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘው የአዲስ ድምጽ ፣ ትንሳኤ ኢትዮጵያ ፣ ፍኖት፣ በመንፈሳዊም በብዛት ይገኛሉ ። በቦስተን የሚገኘው "አቡጊዳ የቴሌቪዥን

---

146 *Exትra Ze Ethiopia., p. 1*

147 ቦልቲሞር ከተማ ያለው የዱከም ምግብ ቤት (ሬስቶራንት) በዐዲስነቱ ሲመረቅ ጸበል ለመርጨት (ጸሎት) ገብቼ ከኢትዮጵያዊው ይልቅ የውጭው ዜጋ በልጦ ክትፎውን በእንጀራ እያጣበቀ ሊበላ አይቼ ተደንቄለሁ።

ፕሮግራም" እና በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ቶክ ሾው አድናቆትን ያተረፉ ስለኾኑ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ብዙሐኑ ኢትዮጵያዊ ግን በሥራ ተወጥሮ ስለሚኖር ጊዜ አግኝቶ ቴሌቪዥን የማየት ዕድል የለውም፤ የራዲዮኑን ፕሮግራም ግን በኢንተርኔት ስለሚያገኘው በቀላሉ ይከታተለዋል።

እንደቀድሞው ጊዜ ብዙ ነገሮችን ከኢትዮጵያ ማጓጓዝ እየ ቀነሰ መጥቷል ። ለምሳሌ የጤፉ ምርት በካሊፎርኒያ፣ በሚቺጋን እና ኢይዳሆ ግዛቶች እየተመረተ ነው፤ ነጭ ፣ ጥቁር (የሩዙ፣ የሰንዴው ሌላም) እንጀራ በአይነት ይጋገራል ። በርበሬ እና ሽሮ ከአገር ቤት ከማስላክ ይልቅ እዚያው ቢመረት ሳይሻል አልቀረም ። ችግሩ አገር ውስጥም ስለተፈጠረ ከአገር ከማውጣት በቶሎ ማምረት ቢጀመር መልካም ነው።

ለቤተ ክርስቲያን የሚኾኑ ንዋየ ቅድሳት ለምሳሌ ከበሮ በኦሀዮ ግዛት እየተጠረዘ አብያተ ክርስቲያናቱ ኹሉ ከዚያ እየገዙ እየተገለገሉ ናቸው። ሌሎችም ንዋየ ቅድሳት በዚያው እየተዘጋጁ ነው።

ሌላው እስከ አኹን በአሜሪካ እየተመረተ ነው ተብሎ ያልተሰማ አንዱ ነገር ቢኖር ጥንግ ድርብ ወይም ጃኖ፣ ኩታ እና ነጠላ ፤ የሴት-ወይዘሮ ጥበብ ነው። ይህ የኢትዮጵያውያ ሕዝብ የሚያሸበርቅበት ልብስ ምንጩ እዚያው ሹሮ-ሜዳችን ነው። በዚህ ጥበብ ሴቶች ልጆቻችን ዉበት (ሞዴል)፤ እንዲሁም እናቶቻችን በየቤተ ክርስቲያኑ የሚዋቡበት ፤ በወንዝ ፣ በሃይማኖት የተራራቁትን ኹሉ በአንድነት ባህል የሚያዋሕድ የኢትዮጵያውያን መለያ በአሜሪካ እና በአውሮፓ በወገን አሸብርቆበት ይታያል ። ዱሮ በፈረንጅ አገር መልበስ ይታፈር ነበር ፤ ዛሬ ግን ለብሰው ሲሽቀረቀሩበት ማፈር ሳይኾን ኩራትን እያሳደረ የማንነት መገለጫ አንዱ ምልክት ኾኗል።

በየዓመቱ ሐምሌ 4 ቀን ከአሜሪካ ግዛቶች (እስቴቶች) የተወጣጡ ኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ቡድን ግጥሚያ ይዘጋጃል ። ይህን ውድድር ለማየት የሚጓዘው ኢትዮጵያዊ ቁጥሩ እጅግ ብዙ ነው ። በዚህ ዝግጅት ላይ ብዙዎች ተለያይተው ሳይገናኙ የኖሩ ቤተሰቦች ፣ የጥንት ጓደኞሞች ቀጠሮ ቀጥረው ናፍቆታቸውን በመወጣት አብረው ያሳልፋሉ። በዚህ ወቅት ኳስ ጨዋታ ብቻም ሳይኾን ፤ የባህል ጨዋታዎች፤ የተለያዩ የባህል ዕቃዎች ንግድ ፤ ካሴቶች ፣ የኢትዮጵያ ባንዲራ ፤ ሌሎችም በግለሰቦች ለሽያጭ የሚቀርቡ አሉ ። ይህ ከእናት አገር ውጭ ከአብያተ ክርስቲያናት ቀጥሎ በአሜሪካ አገር ኢትዮጵያውያንን የማሰባሰብያ አንዱ ምክንያት ነው።



በአሜሪካ እና በአውሮፓ በዙ የኢትዮጵያውያን ቅርሶች አሉ። አገር ጎብኝዎች (ቱሪስቶች) ጥንታዊ የኢትዮጵያ ቅርሶችን እየገዙ ካገር በማውጣት ብዙዎች በየቤታቸው እንዲሁም በግለሰቦች እጅ በብዛት ይኖራሉ ። ከነዚህም ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት የብራና መጻሕፍት ፤ የብር መስቀሎች ፤ ጥንታዊ ሥዕሎች ሌሎችም የጥንት ዕቃዎች (አንቲክ) በየሱቁ ተደርድረው በከፍተኛ የአሜሪካ ገንዘብ (ዶላር) ዋጋ ተተምኖላቸው ገበያ ላይ የዋሉ ሞልተዋል ። ከኹሉ የሚያሳዝነው መስቀሎቻችን መንፈሳዊ መልእክት የያዙ መኾናቸው ተዘንግቶ በአንዳንዶች ዘንድ እንደባህል ዕቃ ተቆጥረው ለጌጥ በየምግብ ቤቱ ግርግዳ ላይ መደርደራቸው ነው ። ይህ የኦርቶዶክሳውያን ባህል አልነበረም ፤ የኦርቶዶክሳውያን ባህል በሥዕል ቤት በተከበረ ቦታ ተደርድረው እንዲጸለይባቸው ማድረግ ብቻ ነው።

በሜሪላንድ ቦልቲሞር ከተማ የሚገኘው የዋልተር ቤተ መዘክር (ሙዝየም) ብዙ ከኢትዮጵያ የወጡ ንዋየ ቅድሳት አሰባስቧል ። እነዚህም ቅዱሳት መጻሕፍቶች፣ መስቀሎች፣ ቅዱሳን ምስሎች ሌሎችም አብዛኛውን የቤተ መዘክሩን ቦታ ይዘው ለሕዝብ ይታያሉ። በየጊዜው እየኼድኩ እነዚህ ከአገሬ ከየአድባራቱ እና ከየገዳማቱ የተሰበሰቡት ንዋየ ቅድሳት በመስታወት ውስጥ ተቀምጠው እጇ ሳይነካቸው በናፍቆት ዐይኖቼ ብቻ ተፈቅዶላቸው ሳያቸው ሰንብቻለሁ። በክብር ሳይጎሳቆሉ መቀመጣቸው ደስ ሲለኝ ከአገራቸው መሰደዳቸው ሳያሳዝነኝ አልቀረም ። ይኹን እንጂ የብራና መጻሕፍት፣ ሥዕላትና መስቀሎች የወጡበት ጊዜ በቅርብ ዓመታት ውስጥ መኾኑ አያጠራጥርም ። ከገጠሪቷ ኢትዮጵያ በኑሮ ውድነት የተነሳ ችግርን ማሚያ በጣም ርካሽ በኾነ ዋጋ በአገር ጎብኝዎች ወይም በነጋዴዎች ተገዝቶ ለቤተ መዘክሩ በከፍተኛ ዋጋ-እንደሚሸጥ ጥርጥር የለውም ። ይህ ኹሉ ከአሜሪካ ምሥረታ በፊት የነበረው ታሪካችን የስደተኞች አገር በኾነችው በአሜሪካ በእንዲህ አይነት መልኩ በግለሰቦች እጅ ሳይቀር ገብቷል።

የኢትዮጵያ አረንጓዴው ቡና ከዓለም ተወዳዳሪ የማይገኝለት አንደኛ መኾኑን ከአገራችን ጀምሮ ስንሰማው ኖረናል ። አረንጓዴው ቡናችን ከኢትዮጵያ ምድር ከአራሹ ገበሬ በነጋዴዎች ተገዝቶ 67% በመቶ የሚኾን የውጭ ምንዛሪ የሚያስገባው ስለኾነ ለዓለም ገበያ በማቅረብ ይላካል ። "የኢኮኖሚ ዋልታ ቡናችን" የምንለው ወደ አሜሪካ እና አውሮፓ በደረስን ጊዜ የሚታወሰን ያገራችን ልዩ ምልክት ያለበትን ቡና ለማየት በጉጉት ስንጠይቅ ሳናየው ኖረናል ። አንድ የኢትዮጵያን ስም የያዘ የቡና እሽግ ያየን እንደኾነ ብርቃችን ነበር።

ቡናችን ለዓለም ሕዝብ እንደ ዐረብ ነዳጅ የሚጠቅም መኾኑ ምንም ጥርጥር የለውም ። አኹን እያደር ዓይናችን እየተገለጠ ስናይ በተለይ የአሜሪካንና የአውሮፓን ሕዝብ እየመገብነው ኖረናል። ጠዋት ቁርሱን ቡና፣ ከሥራው በዕረፍት ሰዓቱ ቡና (በተለየ ስሙ ስፕሬሶ፣ ካፕቺኖ..) ራሱን ሲያመው ወይም ድካም ሲሰማው ቡና ፤ በቀን ውስጥ ቢያንስ ሦስት ጊዜ በትልቅ ሲኒ (በመግ) ሲጠጡ ኖረዋል።

ይህንን ባለውለታውን ቡናችንን ስታርባክ የተባለው የካፒታሊዝም ኩባንያ ከኢትዮጵያ የመጣ ቡና ነው ማለትን ሳይፈልገው ኖረ። ኢትዮጵያ በጥሩ ነገር እንዳትታወቅ ዘወትር ረሀብተኛ ነች እየተባለ እንዲኖር ከብራዚል ወይም ከሌሎች ከእስያ አገሮች ወይም እነሱ በቅኝ ግዛት ይዘዋቸው ከነበሩት ያፍሪካ አገሮች እንደሚያመጡ በማድረግ ልዩ ምልክት ሰጥተው ከሚገባው በላይ ትርፍ ያገኙበታል ። ልዩ ስሙም "ብላክ ጎልድ" ተብሎ ይጠራል ። እንደቀድሞው የባርያ ንግድ "ወርቃማው የሬክታንግሉ ንግድ" ተብሎ ጠቀሜታ እንደሰጣቸው ኹሉ ፤ ዛሬም "ብላክ ጎልድ" ወርቃማው ኢትዮጵያዊው ቡናችን ምዕራባውያንን ሚሊዬነሮች እያደረጋቸው ኖሯል።

ቡና የተገኘባት ከፋ (ኮፊ) የትውልድ አገር የኾነችው ኢትዮጵያ ለዘመናት ስሟ ሳይጠራ ኖሮ በቅርቡ ኢትዮጵያዊው ኹሉ በአንድነት በመረባረቡ በመጠኑ ለውጥ ሊመጣ ችሏል። ይህ አንዱ ኢትዮጵያውን ላይ የሚደርሰው የካፒታሊዝም ተፅዕኖ የሚያሳይ ነው።

በአሜሪካ ብዙ ኢትዮጵያን ምሁራን፤ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ካህናት፣ ሳይንቲስቶች፣ አስትሮኖሚስቶች ፣ የህክምና ዶክተሮች ፣ በተለያየ ሙያ የተሰለፉ ዶክተሮች ፤ ነርሶች ፣ ፓይለቶች ፣ ኢንጂነሮች፣ ኢኮኖሚስቶች፣ አስተማሪዎች፣ ጋዜጠኞች፣ አርቲስቶችና የጉልበት ሠራተኞች ሌሎችም ፤ አሜሪካንን በሥራ በመጥቀም ላይ ይገኛሉ ። ለመኖር መታገሉ ጥሩ ነው ፤ ኾኖም ግን ወልዳ ያሳደገች እናት ኢትዮጵያን ልጆቿ በተለያየ አመለካከት የእርስ በእርስ የሐሳብ ልዩነት ቢኖርባቸውም ተንኮልንና ክፋትን በመተው ፤ እንዲሁም በመታገሥ አርቲስቶቹ እንደሚሉት "መቻቻል ይቻላል" እና ተቻችሎ ይቅር በመባባል፣ መረዳዳት ፣ መተሳሰብ እና ተቀራርቦ መነጋገር በሰላም መኖር ተገቢ ነው።

እናት ኢትዮጵያም የወላድ መኻን እንዳትኾን በማንኛውም አቅጣጫ ፤ በየሙያው ፣ በችሎታው ተሠማርቶ ለአሜሪካ የሚሠራ ኹሉ በግል እና በኅብረት እየተደራጀ እናት አገርን መርዳት እና ተተኪውን ተውልድ ማስተማር የኹሉም ኃላፊነት ነው።



# ምዕራፍ ፳

# የኢትዮጵያ ወዳጆች

## (፩) ማርቆስ ጋርቬይ

"እኔ የማምነው አንድ አምላክ በኾነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ፤ በኢትዮጵያ አምላክ ነው" ደግሞም "እኔ ከማንኛውም ነጭ ጋር እኩል ነኝ"(ማርቆስ ጋርቬይ)

በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ብዙ የአውሮፓ ነጮ ሰደተኞች ወደ አሜሪካ ሲገቡ የዘር አድለዎ በኒው ዮርክ በጥቁሮቹ ነዋሪዎች የበለጠ እየተስፋፋና እየከፋ መጣ። ሥራ የሚያገኙት እና የሚቀጠሩት ነጮቹ ስደተኛ አውሮፓውያን ብቻ ነበሩ። እዚያው ተወላጅ ነዋሪ የኾኑ ጥቁሮችን ለተሻለ ቦታ የሚቀጥር አልነበረም። በዚህ ወቅት ማርቆስ ጋርቬይ ከጃማይካ ዐዲስ ስደተኛ ኾኖ ኒው ዮርክ ደረሰ።



ማርቆስ ሞዚሃ ጋርቬይ

ማርቆስ ጋርቬይ በትውልዱ ጃማይካዊ የነበረ ሰው ነው። የተወለደው ነሐሴ 17 ቀን 1887 ሲኾን በቅጽል ስሙ የጥቁር ሙሴ በመባል ይታወቃል፤ ጋርቬይ በልጅነቱ መጽሐፍ በጣም ያነብ ነበር። በዕድሜው ከፍ ሲል ወደ ጃማይካ ከተማ ኪንግሥተን ኼዶ የንግድ ሥራ መሥራት ጀመረ። በዚህ ወቅት አይቶ የማያውቀውን የነጭና የጥቁር የዘር አድልዎን በግልጽ አየ። ከዚያም ወደ ደቡብ አሜሪካ ባሉት አንዳንድ ግዛቶች ኒካራጓ፣ ጉዋቲማላ፣ ኤልሳልቫዶር እና ጋያና አገሮች ተዘዋውሮ

በሚያይበት ጊዜ በከበርቴዎች ፋላጭ ቆራጭነት ባርያዎች (ኔግሮዎች) በትንሽ ደመወዝ ሥራ እያሠሩ ሲያሰቃዩአቸው አየ ። ወደ አገሩ ጃማ ይካ ተመልሶ ለቅኝ ገዢው ለብሪታንያ መንግሥት ጥቁሮች በኑሯቸው እንዲሻሻሉ ዕርዳታ እንዲደረግ ጠየቀ ። በኋላም "ደቡብ አሜሪካ ፤ ሰሜን አሜሪካና ካሪቢያን ያላችሁ በባርነት የተያዛችሁ ጥቁሮች ተሰባሰቡ" በሚል አንድነት እንዲፈጥሩ ጥሪ አቀረበ። ወደ እንግሊዝ አገር በ1912 በመኼድ በዚያም እንደዚሁ በጥቁሮች ላይ የሚደረገውን አድልዎ አየ።

ማርቆስ ጋርቬይ የግብርና ሳይንቲስት የነበረውን ጆርጅ ዋሽንግ ተን ካርቨር የጻፈውን መጽሐፍ አነበበ ። ይህ ሰው ቀደም ሲል ከኔግሮ መካከል በገጠመው ዕድል የተማረ ሰው ነው። የታወቀ የጥቁር ጸሐፊ እና የዕፅዋት ሳይንቲስት እንደነበር ይነገርለታል ። ማርቆስ ጋርቬይ ይህን የተጻፈ መጽሐፍ በማንበቡ መነሻ ኹኖት ጥያቄውን አቀረበ ። ጥያቄዎቹ እንዲህ የሚሉ ነበሩ። የጥቁር መንግሥታችን የታለ ? የጥቁ ሮች አገራችን የታለ? ንጉሣችንና መንግሥቱ የታለ ? አምባሳደራችን የታለ? ወታደራችን የታለ? መርከባችን የትአለ ? የሚል ነበር።

ማርቆስ ጋርቬይ ወደ አሜሪካ ጉዞ ያደረገው በ1914 ነው ። በዚያም ሲደርስ ቀደም ብሎ ዝናው ተሰምቶና ታውቆ ስለነበረ በኒው ዮርክ ከተማ ሀርለም ቀበሌ ያሉት በድህነት የሚኖሩት ብዙ ጥቁሮች በደስታ ተቀበሉት፤ ንግግር እንዲያደርግ ጋበዙት። ጋርቬይ በእንግድነት ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ በሚጠብቀው ቦታ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋጣለት ንግግር ሳያደርግ ቀረ። ይህን የንግግር ችሎታውን ለማሻሻል ቢሊ ሰን ዴይ የሚባለው የታወቀ የነጭ የወንጌል ሰባኪ በጊዜው ብዙ ሕዝብ የሚከተለው ስለነበር ወደሱ በመኼድ እንዴት በንግግር ችሎታው ብዙ ሰዎችን እንደሚስብ የአነጋገር ስልቱን አጠና። ከዚያም በዚህ የንግግር ዘዴ ራሱን በማዘጋጀት ከፍተኛ ተናጋሪ እና ሰባኪ ወጣው።

ማርቆስ ጋርቬይ በባቡር ወደ 32 የሚጠጉ የአሜሪካ ግዛቶች ተጉዞ ንግግር አደረገ ። አሜሪካን ለኹለት ከፈለው። በ1917 ብዙ ምሁራን ጥቁሮች ተከተሉት። ከዚያ በ1919 አሜሪካ ኒው ዮርክ ከተማ ውስጥ "ዩናይትድ ኒግሮ ኢምፕሩቭመንት አሶሴሽን"[148] በማለት ታላቅ ድርጅት አቋቋመ ። ጥቁር አፍሪካ ወይም ኔግሮ ሰው ይበላል! ጭራቅ (ካኒባል) ነው እያሉ ሕፃናቶቻቸውን የሚያስፈራሩበትን የነጮች ሐሳብ

[148] UNITED NEGRO IMPROVEMENT ASSOCIATION



በመለወጥ "እኔ ከማንኛውም ነጭ ጋር እኩል ነኝ" በማለት የብዙዎችን ለዘመናት የቆየ የተሳሳተ እምነትና አመለካከት ከመሠረቱ አናጋው።

ማርቆስ ጋርቬይ ወደ 54 የሚጠጉ የመብት እና የነጻነት ጥያቄ ዎች ነበሩት። የማኅበሩ አባላት የአንድነት መዝሙር[149] ነበራቸው፤ እን ዲሁም ጥቁር ፥ አረንጓዴና ቀይ ቀለም ያለው ባንዲራ ነበራቸው።

ጥቁር በሙሉ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተሰበሰበ እንዲመካከር ከነጭ ጥገኝነት ወጥቶ የራሱን ሥራ እንዲሠራ ፤ ራሱን እንዲችል አዘዘ። ዝናው በኹሉም ጥቁር ዘንድ ተሰማ። ለጥቁር ሕዝቦች ኹሉ ተስፋ ኾነ። አብዛኛዎቹ ነጮች አደገኛ ሰው ነው ብለው ፈሩ። ይኹን እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የድርጅቱ አባል ኾኑ ። ጋርቬይ "ኒግሮ ወርልድ" የሚል ጋዜጣ ማዘጋጀት ጀመረ ። በ1919 ሦስት ሚሊዮን ተኩል ተከታይ ጋዜጣውን ያነቡ ነበር።

1ኛው የዓለም ጦርነት ሲያበቃ "አፍሪካ ለአፍሪካውያን" የሚል ስብከት ያስተላልፍ ጀመር። "አውሮፓ ለአውሮፓውያን! እስያ ለእስያ ውያን! ከኾነ እኛ ደግሞ የምንጠይቀው አፍሪካ ለአፍሪካውያን እንዲ ኾን ነው ። ስለኾነም በቅኝ አገዛዝ አፍሪካን የያዛችሁ የአውሮፓ ነጮች በቶሎ አህጉራችንን ልቀቁ እና ውጡ! ይል ነበር።

ማርቆስ ጋርቬይ በንግግሩም ኾነ በጽሑፉ ላይ ሁሉ በባርነት ተይዛችሁ በዘርአድልዎ በሽታ በተጠናወተው ኅብረተሰብ ውስጥ የምት ኖሩ ጥቁር አፍሪካውያን በሙሉ ወደ አገራችሁ ወደ አፍሪካ፤ የነጻነት

[149] በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ጥቁር አሜሪካውያን ይዘምሩት የነበረ መዝሙር ። Ethiopia, the land of our fathers, the land where the God loved to be, as storm cloud at night suddenly gathers Our armies come rushing to thee. We must in the fight be victorious When swords are thrust outward to gleam; For us will the vict'ry be glorious When led by the Red, Black and Green.
Advance, advance to victory, Let Africa be free; Advance to meet the foe With the might Of the Red, the Black and the Green.
Ethiopia. The tyrant's Who smote thee upon thy knees, And thy children are lustily calling From over the distant seas. Jehovah, the Great One has heard us, Has noted our sighs and our tears, With His spirit of Love he has stirred us To be One through the coming years. CHORUS – Advance, advance , etc
O Jehovah, thou God of the ages Grant unto our sons that lead The wisdom Thou gave to Thy sages When Israel was sore in need. Thy voice thro' the dim past has spoken, Ethiopia shall stretch forth her hand, By Thee shall all fetters be broken, And Heav'n bless our dear fatherland. Chorus – Advance, advance, etc…

አገር ወደኾነች አገራችሁ ኢትዮጵያ ተመለሱ ። ፊታችኹን ወደ
ኢትዮጵያ መልሱ ፤ ወደ ጥንት ርስታችሁ አፍሪካ ተመለሱ፤ ዘውዱን
የደፋውን ጥቁር ንጉሥ ተመልከቱ፤ እሱ አዳኛችን ነው ይል ነበር።[150]
የጻፈውና የተናገረው ትንቢታዊ ንግግር ፍጻሜ ያገኘው ግርማዊ ቀዳ
ማዊ ኃይለ ሥላሴ በ1945 እና በ1963 በአሜሪካ ጉብኝት ባደረጉ
ጊዜ ፤ እንዲሁ በ1966 ካሪቢያን ደሴቶችንና በጃማይካ ጉብኝት ባደረ
ጉበት ጊዜ ነው ብለው ብዙዎች ጥቁር ሕዝቦች ያምናሉ።

ማርቆስ ጋርቬይ በኒው ዮርክ ያቋቋመው ድርጅቱ (UNIA)
ዝናው እየሰፋ ወደ 40 አገሮች ተዛምቶ ባለ 1,100 ቅርንጫፍ እስከመ
ኾን ደረሰ። በእርግጥ አብዛኛው ቅርንጫፍ ያለው በአሜሪካ ነበር።

ማርቆስ ጋርቬይ ከነጭ የዘረኞች ድርጅት (ኩ ክለክስ ክላን)
ከዋናው መሪ ጋር ተገናኝቷል ። እነሱም ሐሳቡ ትክክል መኾኑን ሲደ
ግፉ አሜሪካ የነጭ ፕሮቴስታንት አገር ነች ስለሚሉ ማርቆስ ጋርቬይ
ጥቁሮች ወደ አፍሪካ ተመለሱ የሚለውን እንቅስቃሴውን አልተቃወ
ሙትም ። እንዲያውም ከ1915 ላይ በዊልያም ሲሞን (የፕሮቴስታንት
ፓስተር) የተደራጁት የነጭ ዘረኞች "ዘ በርዝ አፍ ኔሽን"[151] የሚለው
ፊልም እንዲሠራ አድርገዋል ። ይህ ፊልም ዘረኝነትን የሚያንጸባርቅ
ነው። አይሁዳውያን ስደተኞች፤ የካቶሊክ ስደተኞች ፤ የኮሚኒዝምን
ፓርቲ እና ጥቁሮች ይገርፉ እና ይገድሉ ነበር።

ማርቆስ ጋርቬይ ከ ድርጅቱ (UNIA) በተጨማሪ የአፍሪካ
ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚል 1921 በኒው ዮርክ መሠረተ። በዚህ
ዘመን የሚጓጓለት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍና መምህር
በአካባቢው አልነበረም ። በዚህም ከኤጲስኮፓል የክርስትና እምነት
ሲያገለግል ቆይቶ በዘረኝነት የተነሳ አልፈልግም ብሎ የወጣውን የጥ
ቁር ቄስ ጆርጅ ማክጉር የሚባለውን ጵጵስና ሹመት እንዲሰጠው አደ
ረገ ። ሹመቱም የተሰጠው በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ
ጳጳሳት አማካኝነት ነው ። ከዚያም ቤተ ክርስቲያን ተመሥርቶ አገልግ
ሎት ይሰጥ ነበር ። ራሱ ማርቆስ ጋርቬይ እምነቱን ሲገልጽ

[150] "When you see a King come from Ethiopia, that day salvation wi
ll be up on you"
[151] (The Birth Of Nation)



"እኔ የማምነው አንድ አምላክ በኾነው በአብ በወልድ በመን
ፈስ ቅዱስ ፤ በኢትዮጵያ አምላክ ነው" ይል ነበር።[152]

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በነጭ የበላይነት በጥቁር ላይ በሚደርሰው
ግፍ የተነሳ ማርቆስ ጋርቬይ እግዚአብሔር ጥቁር ነው፤ መላእክትም
ጥቁር ናቸው፤ ሰይጣን ግን ነጭ ነው ፤ ይል ነበር ። ብዙ ጥቁሮች
ይህን ይዘው በቤተ ክርስቲያናችን ሲገቡ በነጭ የተሣለ ምስል ሲያዩ
ቅሬታ ይሰማቸዋል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የክርስትና
እምነት ግን ስለ ሥዕል ያላት አመለካከት በቀለም ላይ ወይም በቁን
ጅና ውበት ላይ የተመሠረተ አይደለም። ማንኛውም አምላካዊ የኾነ
ምስል ወይም የቅዱሳን፥ የመላእክት ምስል ክብር አለው ። በምስሉ
አድሮ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእምነትና በፍቅር ግንኙነት ይደረጋል።

ማርቆስ ጋርቬይ በአንድ ወቅት የአትላንቲክ ውቅያኖስ "የኢ
ትዮጵያ ውቅያኖስ" እየተባለ ይታወቅ በነበረው በባርያ አጋዦች ያለ
ውዴታ በግድ የአፍሪካ ልጆችን ወደ አሜሪካ እንዲገቡ አድርገው
ስለነበር፤ አኹን ደግሞ በድርጅቱ በተገዛው ብላክ እስታር በምትባለው
መርከብ ጥቁር ሕዝብ ኹሉ ከነጭ አገር በመውጣት በዚሁ ውቅያ
ኖስ አቋርጠው አፍሪካ እና ኢትዮጵያ በግድ ሳይኾን በውዴታ ይመ
ለሳሉ የሚል እምነትና ጉጉት ነበረው ። ይኹን እንጂ ብላክ እስታር
የተባለችው መርከቡ ክስረት ደረሰባት ። እንዲሁ በጋርቬይ ላይ የው
ጭም የውስጥም ጠላት ተነሳበተው በተንኮል ተከሶ ለዐምስት ዓመት
ወደ ወኅኒ ቤት እንዲወርድ ተፈረደበት ። ከ1922 እስከ 1927 ድረስ
ታሠረ። ከእሥራት ከተፈታ በኋላ ወደ ጃማይካ እንዲመለስ (Deport)
ከአሜሪካ ፕሬዚዳንት ካልቪን ኮሊጂ ትእዛዝ ወጣ። የአሜሪካ ጥቁ
ሮች በከፍተኛ ሐዘን እና በለቅሶ ተሰናበቱት ። ወደ ትውልድ አገሩ
ጃማይካ ሲደርስ ከፍተኛ አቀባበል ተደረገለት።

እንቅስቃሴውን ባለማቋረጥ በ1928 ለንደን በመኼድ የመሠረተ
ውን ድርጅቱን (UNIA) ቅርንጫፍ ያጠናክር ጀመር ። ኾኖም ግን ለን
ደን በደረሰበት እና በቆየበት ጊዜ ሐሳቡ ኹሉ አልተሳካም ። ፋሽስት
ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በመውረሩ ያሰበውና የተመኘው ፍጻሜ አላገኘለ
ትም። ሥራው ኹሉ በሐሳብ በመገታቱ በጣም አዘነ። እንግሊዝ አገር

[152] **Garvey Said** "We Negroes believe in the God of Ethiopia, the everlasting God – God the Father, God the Son and God the Holy Ghost, the one God of all ages. This is the God in whom we believe, but we shall worship Him through the Spectacles of Ethiopia. (Dictionary of Religions p. 76)

ገብተው የሚኖሩት ግርማዊ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴን ለማግኘት ፈልጎ ሳይሳካለት ቀረ ። ተወዳጁ የጥቁር ጀግና ማርቆስ ጋርቬይ እንደተመኘው የአፍሪካን ምድር ሳይረግጥ ሰኔ 10 ቀን 1940 በ53 ዓመት ዕድሜው በልብ ድካም በእንግሊዝ አገር ሞተ ። አንዳንዶች በጭንቅላት ቱመር ነው ይላሉ ። ማርቆስ ጋርቬይ ዐፅሜን በዚህ በባዕድ አገር እንዳትተውት ፤ እዚህ እንዳትቀብሩኝ ብሎ የኑዛዜ ቃል በማሰማቱ ወደ ተወለደበት አገሩ ጃማይካ ተወስዶ በክብር ተቀበረ ። በጃማይካ የጀግኖች መቃብር ውስጥ ዐፅሙ ዐርፏል። በዚያ መታሰቢያ ሐውልት አቁመውለታል።

ማርቆስ ጋርቬይ ለብዙዎች የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች መንገድ ከፈተ። በዚህ የተነሳ የኔሽን ኦፍ ኢስላም (1930) የድርጅት አባላት የነበሩ ኤላጃ መሐመድ ፤ ማልካለም ኤክስ እንዲሁም የራስ ተፈርያን እንቅስቃሴ በዚሁ በማርቆስ ጋርቬይ ዘመን ተጀመረ። ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኀይለ ሥላሴን በማክበር ዛሬ የራስ ተፈሪ (ራስታ) በመባል በሚጠራው እምነት በሥሩ ኔሄበንጊ፣ ቦቦሻንቲና አሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል (ቱዌልቭ ትራይብ ኦፍ እስራኤል) የሚባሉት እንቅስቃሴዎች በዚሁ በማርቆስ ጋርቬይ ጅምር ቀጥለው ተመሠረቱ ።

## (፪) ራስ ተፈሪያን

የራስ ተፈሪያን እንቅስቃሴ ደጋፊችና አራማጅ ከኾኑት አንዱ ዘፋኝ ቦብ ማርሌይ ስመ ክርስትናው ብርሃን ሥላሴ ነው ። ይህ ሰው በራስታ እንቅስቃሴ በመሳተፍ በሬጌ ሙዚቃ አማካኝነት መልእክት ማስተላለፍ ጀመረ። እንዲሁም አብሲንያና ሌሎች የሙዚቃ ቡድን አቀንቃኞች በዚሁ በማርቆስ ጋርቬይ እንቅስቃሴ ተቋቁመዋል። ቦብ ማርሌይ ከሚዘፍናቸው አንዱ ዘፈን ባቢሎን ሲስተም የሚል ይገኝበታል።[153] ይህም የአሜሪካና የበለጸጉ የምዕራባውያንን ፖለቲካ ለመንቀፍ የተዘጋጀ ነው ። በቅዱስ መጽሐፍ ባቢሎን የኀያል መንግሥት ምሳሌ ኾና ተጠቅሳለች።

**ከእናንተ ጋር ተመርጣ በባቢሎን ውስጥ ያለች ቤተ ክርስቲያን (1ኛ ጴጥ. 2፥13)።**

[153] **Babylon System** = We know where we are going. We know where we are from. We leaving Babylon. We going to our Father Land



በሐዋርያት የወንጌል ስብከት ዘመን በባቢሎን የተመሰለችው ከተማ ሮማ ነበረችና ነው። በምዕራቡ ዓለም የሚኖሩ ጥቁር ሕዝቦች አሜሪካ እና ሌሎቹ ኃያላን የምዕራብ አገሮች ባቢሎን እያሉ ይጠሯቸዋል።

ዐፄ ኀይለ ሥላሴ አሜሪካንን ከጎበኙ ከ ሦስት ዓመት በኋላ በካሪብያን ደሴቶች በጃማይካ፣ በቴቤጎ ፣ በትሪንዳድ፣ በሞንቶጎ ቤይ ለመጀመሪያ ጊዜ በደረሱ ጊዜ በብዙ ሺ የሚቆጠር ሕዝብ መዝሙር እየዘመረ ከፍተኛ አቀባበል አድርጎላቸው ነበር ።

የራስ ተፈሪያን ተከታዮች ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ባንዲራ ስለሚወዱ የማንነታቸው መለያ ክብራቸው አድርገው ይይዙታል። በምዕራቡ ዓለም በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ በካሪብያን ደሴቶች በኢትዮጵያ ሕብረ ቀለም አርንጓዴ ፣ ቢጫና ቀይ ባንዲራ በየቦታው ሲውለበለብ ማየት የተለመደ ነው። ኮታቸው ባንዲራ፣ ኮፍያቸው ባንዲራ፣ ካኔቴራቸው በባንዲራ ያሸበረቀ ቀለም ያለበት ነው ። በተጨማሪ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ፎቶ ግራፍ ማንነታቸውን የሚገልጹበት አንዱ ምልክታቸው ነው። ሲሞቱ አስከሬናቸው ኢትዮጵያን አፈቅራለሁ (I LOVE ETHIOPIA) የሚል ጽሑፍ ባለበት አርንጓዴ ፣ ቢጫና ቀይ በኾነው ባንዲራ ተጠቅልለው የታወቀው ሙዝሙር እየተዘመረ ወደ መቃብር ይወርዳሉ ። ይህንም የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ብዙ ጊዜ አጋጥሞት አይቷል ። በብዙዎች ኢትዮጵያውያን ዘንድ የማይወደደው ዕፀ ፋርስ (ሀሺሽ) የማጨስ ባሕላቸውና በጣም የተድጎለጎለው ጠጉራቸው ነው። እነሱ ግን ናዝራዊ ነን ይላሉ።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ1966 በካሪብያን ደሴቶችና ጃማይካን በጐበኙበት ጊዜ ከፍተኛ አቀባበል ተደርጎላቸው ነበር። ራስ ተፈሪያን ከፍተኛ አቀባበል አድርገውላቸዋል። ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ[154] የሚለውን ለጌታ ኢየሱስ የተነገረውን በነሱው የአተረጓጐም እና የፍልስፍና መንገድ ለውጠው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መለኮታዊ ግብሕርይ አላቸው ይላሉ። በርግጥ የንግሥናው ዘር ከዳዊት እና ከሰሎሞን ቢኾንም ግርማዊ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ መሢሕ አይደሉም

ይህ በኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና አማንያን ዘንድ ተቀባይነት የሌለው የባዕድ አምልኮ መንፈስ ያለበት ነው። ምንም እንኳን መነሻው ልባዊ በኾነ ቀናኢነት፥ ወገንን ፍለጋ ያስከተለው መኾኑን ቢታወቅም፤ ውጤቱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ እምነትና ባህል ጋር የማይጣጣም ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ

[154] ዘፍ. 49፥8-10 ፤ ራእ. ዮሐ. 5፥5

ክርስቲያን ምእመናንና የንጉሠ ነገሥቱ እምነት የተመሠረተው በአንዱ
በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነትና ጌትነት ላይ ነው ። እሱም ከሰዎች
ወገን ተወዳዳሪ የሌለው ፍጹም አምላክ ነው።

የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማንነት ለማወቅ ከስፈለገ
የተወለዱት በሐረር ከተማ ሐምሌ 16 ቀን 1884 ዓ. ም. ነው። የመጀ
መሪያ ስማቸው ተፈሪ ነበር። ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ. ም. ዘውድ
ጫኑ ። በ1916 ዓ. ም. የባርያ ንግድ እንዲቀር የመጀመሪያ ሕግ
አወጡ፤ ንግዱም እንዲቆም አዋጅ አሳወጁ፤ ይህ አሳፋሪው የባርነት
ሥራ ሰውን በሰው መግዛትና ማስቃየት በኢትዮጵያም ውስጥ ነበር ።
በባርነት ማሰቃየት እና ቀጥሮ ማሠራት የተለያየ ነገር ነው ። ግርማዊ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን ለ43 ዓመት በንጉሠ ነገሥትነት
መሩ ። በጣም ከሚከበሩት ስማቸው ገናና ከነበሩት ነገሥታት አንዱ
የኢትዮጵያ ንጉሠ ንገሥት ነበሩ ። ከዚህ ውጭ ፈጣሪ ናቸው የሚለ
ውን አባባል በኢትዮጵያውያን እና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ
ተቀባይነት የለውም።

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ማርቆስ ጋርቬይ ሌላው አፍሪካን
ለአፍሪካውያን ያለው ትንቢት ተፈጸመ። ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት
በኋላ ከአውሮፓውያን ቅኝ አገዛዝ ኹሉም አገሮች ነጻነታቸውን ቀስ
በቀስ ተቀዳጁ። የኔሽን ኦፍ እስላም እና ራስ ተፈሪያን እስከ መጨረ
ሻው ወደ አፍሪካ ለመግባት የተጉት አፍሪካ ምድርን ረገጡ። ለኔሽን
ኦፍ እስላም መሥፈሪያቸው ላይቤሪያ ኾነ።

ለራስ ተፈሪያን ደግሞ በደቡብ ሸዋ ሻሸመኔ ውስጥ ገብተው
እንዲሠፍሩ ዐምስት ጋሻ መሬት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሰጧ
ቸው። በእርግጥ ንጉሡ የሰጡት ለኹሉም ጥቁር ሕዝቦች ይልቁንም
በጣሊያን ጦርነት የተራዱትን "የኢትዮጵያ ወርልድ ፌዴሬሽን"
ጨምሮ ነበር ። ነገር ግን በኮሚኒዝም ሥርዓት ጊዜ መሬት ላራሹ
ሲባል ከዐምስቱ ጋሻ አንድ ብቻ ተፈቅዶላቸው ይኖሩ ነበር ።

በአኹን ጊዜ አንዱ ጋሻ ላይ ወደሦስት መቶ የሚደርሱ ቤተሰ
ቦች ሰፍረው ይገኛሉ። የማርቆስ ጋርቬይ ሕልሙ እውነት የሚኾንበት
ጥርጊያ ተከፍቶ ዛሬ አያሌ አፍሪካውያን ከአሜሪካ ወደ አፍሪካ በየጊ
ዜው በመመላለስ ላይ ይገኛሉ።



## ምዕራፍ ፲

## የዓለም ጦርነቶች እና አግኝቶ ማጣት

ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ ይህ ሊኾን ግድ ነውና
ተጠበቁ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው። ሕዝብ በሕዝብ
ላይ፥ መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሳልና ፤ ረሀብም ፣ ቸነፈርም ፣
የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይኾናል (ማቴ. 24፥6)።

ይህ ቃል ከአንደኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ፍጻሜ አግኝቷል በማለት
ብዙ የፕሮቴስታንት የክርስትና አማንያን ይናገራሉ። ከዐሥራ ዘጠነኛው
መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በፈጠነ ኹኔታ ለሰው ልጅ ማጥፊያ የሚኾኑ
በጣም የተራቀቁ መሣሪያዎች ተፈጠሩ። እኔ እበልጥ የሚለውም ውድ
ድር ከበፊቱ ይልቅ የጨመረበት ወቅት ነው።[155] ይህ የመጀመሪያው
የዓለም ጦርነት መንግሥት በመንግሥት ላይ ሕዝብ በሕዝብ ላይ በጥ
ላቻና የበላይነትን ለመያዝ በፍኩክር በየአቅጣጫው የተነሳሳበት ፤ ከፍ
ተኛ መዋደቅ የተደረገበት ጊዜ ነበር።

የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ ረሀብ፥ የምድር መን
ቀጥቀጥ ፥ እንዲሁ ተከትሎ የኹለተኛ ዓለም ጦርነት ፤ ከዚያም ቀዝ
ቃዛው ጦርነት ተነስቶ በዓለም ላይ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ አል
ቋል ። አኹን እስካለንበት ዘመን ድረስ ከመቶ እስከ መቶ ሰባ የሚደ
ርሱ ጦርነቶች ሲካኼዱ ታላላቅ ጦርነቶች ደግሞ ወደ 12 በመድረስ
የሰው ልጅ እልቂት ተፈጽሞባቸዋል። የእነዚህ የእልቂት ዘመናት ሲቆ
ጠር የአንድ ሰው ሙሉ የዕድሜ ዘመን ነው። በነዚህ ጦርነቶች ውስጥ
በአብዛኛው ኀያላን አገሮች አሜሪካንን ጨምሮ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ
እና ተሳትፎ አድርገዋል።

አሜሪካ በዚህ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ላይ ተሳትፋለች ፤
ይህ ጦርነት መነሻው ብዙ ነገር ነው። ዋናው ግን አውሮፓውያን አፍሪ
ካን በቅኝ ግዛት ይዞ ለመኖር ፤ ለመቀራመድ የሚያደርጉት ሩጫ
ወዳጅነታቸውን በማሻከር አነታርኳቸዋል። ከዚያም በላይ አንዱ የአን
ደኛው አገር የበላይ ለመኾን እኔ እበልጣለሁ በሚል የብሔራዊ ስሜት
በሚደረገው ውድድር ጦርነት ከ1914 እስከ 1918 ባሉት ዓመታት
ውስጥ ተካኼደ።

[155] Chronicle of the 20th Century. 1988 p. 159, 228

አሜሪካ ለሦስት ዓመት ያህል ጦርነት ውስጥ ሳትገባ ቆይታ
ፈረንሳይንና ብሪታንያን ለመርዳት ስትል መሣሪያ ታጓጉዝ ነበር። በዚህ
የተነሳ ጀርመኖች የአሜሪካንን የንግድ መርከቦቻቸውን አስጠሙባ
ቸው። ሚያዚያ 2 ቀን 1917 ኰንግረስ በጀርመን ላይ ጦርነት አወጀ።
ብዙ የአሜሪካ ዜጎች የአሜሪካ መንግሥት ወደ ጦርነቱ እንዳይገባ
ተቃወሙ ። በይበልጥ አየርላንዳውያንና የጀርመን ተወላጆች አሜሪካ
ጣልቃ መግባቷን አልተደሰቱበትም ነበር ። በዚህ በ1ኛው የዓለም ጦር
ነት 10 ሚልዮን ሰው አልቋል።

አሜሪካ ጦርነት ውስጥ በገባች በዓመቱ በ1918 በመስከረም
ወራት በቦስተንና በፊላዳልፊያ ያሉ ወታደሮች እስፓንሽ እንፋሌንዛ
የሚባል የጉንፋን ወረርሽኝ ገብቶ በድንገት ይገድላቸው ጀመር፤ ከዚያ
እየተዛመተ ኼዶ በዚህ የጉንፋን በሽታ 675,000 ሺ ሰው አልቋል ።
ይህ እስፓንሽ እንፋሌንዛ ከአሜሪካ ውጭ ከ 22 እስከ 40 ሚሊዮን
የሚደርስ ሕዝብ በዓለም ላይ እልቂት አድርሷል። የእንፋሌንዛ ጉንፋን
የአንደኛው የዓለም ጦርነት ከጨረሰው ሕዝብ የበለጠ ጨርሷል። ይህ
የእንፋሌንዛ በሽታና የአንደኛው የዓለም ጦርነት ካበቃ በኋላ በ1920
ጀምሮ በአሜሪካ እና በአውሮፓ ትልቅ ለውጥ የነበረበት ጊዜና የተለ
ያየ አመለካከት የተፈጠረበት ዘመኒ ነበር ።

የዳርዊን ሐሳብና አስተያየት[156] በየትምህርት ቤቱ ከፍተኛ ክር
ክር ተደረገበት፤ "ነጭ የሰው ዘር የበላይ ዘር ነው" የሚለውን አመለ
ካከት ብዙዎች ነጮች አመኑበት ። ኩ ክላክስ ክላን የተባለው የዘረ
ኞች ቡድን የአባላቱ ቁጥር ጨምሮ የጥቁርን ዘር በጣም ያጠቁበት
ዘመን ነበር።

ሌላው ለውጥ በ1921 የወንጌል ስብከት በራዲዮ ቴነሲ ላይ
ተጀመረ ፤ በአሜሪካ የክርስትና እምነት ተከታዮች መሐከል ብዙ አከ
ራካሪ የኾኑ ነገሮች ተነሱ ፤ የብዙ ብዙ ፋንዳሜንታሊዝምና ሊበራሊ
ዝም[157] መንፈስ የተከተሉ የፕሮቴስታንት እምነቶች ተፈጠሩ ። ከዚኽ
በፊት ተደርጎ የማይታወቅ ሴቶች ሰው በተሰበሰበበት ሲጋራ ማጨስ ፣
በቤተ ክርስቲያንም ኾነ በማንኛውም ቦታ ከጉልበት በላይ የሚወጣ
ቀሚስ (ፓሪሞድ) በመልበስ አካልን ማሳየት ፤ ሜካፕና ልፒስቲክ መቀ

[156] Theory

[157] Liberal Theology = Cross denominational movement begun in the nineteenth century with a tendency to focus on human freedom and humanity's power to perceive God by reflecting on human experience, rather than through Christian Orthodoxy.



ባት በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በውዝዋዜ በዳንስ የመዘመር
ልማድ ተፈጠረ። ከላይ እንደተገለጸው የማርቀስ ጋርቬይ እንቅስቃሴ
ደጋፊዎችና የሰብአዊ መብት ጥያቄዎች ቀጠሉ ፤ የሀብት ማግኘት ብል
ጽግና እና ጥጋብ በዝቶ ነበር።

የአኗኗር ኹናቴ መለወጡ፣ ሀብት ማግኘቱ ዐዲስ እና ያልተለ
መደ ነገር ስለነበረ የሰዎች ሕይወት በአንድ ጊዜ ተቀየረ ። መኪ
ናዎች ፣ አውሮፕላኖች ፣ ራዲዮን፣ ቴሌፎንና የመገናኛ ብዙኃን በቀላ
ሉና በፍጥነት ዕድገት ማሳየት ጀመሩ፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አሜሪካ
ውያን ፊልም ማየት ጀመሩ ፤ በኹሉም የአሜሪካ ግዛቶችና ቦታዎች
የኤሌክትሪክ መብራት ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘረጋ።

አሜሪካኖች ከመቼውም የበለጠ በጣም ሀብታሞች ኾኑ፤ ኩባን
ያዎች በቀላሉ በጣም የተትረፈረፈ ትርፍ ያገኙ ጀመር ። ተራ ሰዎች
በቀላሉ የታሰረውን ቦንዳ (Stock) ለንግድ የቀረበ ሸቀጣሸቀጥ ገዝተው
ብዙ ማትረፍ ቻሉ ። ደሀው ኹሉ ሀብታም ለመኾን እየተበደረ እንዲ
ሁም በዱቤ አኹን ግዛና በኋል ትከፍላለህ የሚል ግለኝነት ፣ ራስ
ወዳድነት ተፈጠረ። ኩባንያዎች የታሰረውን ቦንዳ ለንግድ የቀረበ ሸቀ
ጣሸቀጥ መግዛትና አትርፎ በመሸጥ መረባረብ ኾነ ፤ የእርሻ መሬት
ሳይቀር በኋላ ትከፍላለህ (በዱቤ) ውሰድ የሚል በጋዜጣ ጭምር
ይወጣ ነበር ።

ማር ባገኘህ ጊዜ የሚበቃህን ብላ። (መጽ. ምሳ. 25 ፥16)

በቃኝ አለማለት ፤ ሀብት ለማግኘት መንሰፍሰፍና አለመርካት ንብረት
ለማካበት የሚደረግ ሩጫ መንፈሳዊነትን አጠፋ ። ይህ የብልጽግና
ዘመን ብዙ አልቆየም ወዲያው ችግር መጣ ። ኤኮኖሚው መሠረት
ሳይዝ እድገ-ድንገት ተንበረከከ ፤ ይህ የገንዘብ ሥርዓት ቀውስ የመንግ
ሥት ገቢና ወጪ ሳይመዛዘንና ሳይመጣጠን ወደላይ ወጥቶ በመውደቁ
ሰውም ደነገጠ ይህም ድንጋጤና ፍርሀት የበለጠ ችግርን እንዲፈጠረ
አደረገው።

በጥቅምት ወራት በድንገት የታሰረ ቦንዳ የሸቀጣሸቀጥ ዋጋ
ወደቀ። ችግሩ የታየበት የመጀመሪያው ቦታ ኒው ዮርክ ዎል እስትሪት
ነበር ። ብዙ ሰዎች የታሰረውን ቦንዳ የሸቀጣሸቀጥ ባለቤቶች የኾኑ
ኹሉ ደንግጠው ቶሎ ለሽያጭ አቀረቡ ፤ ይህም እንደገና ዋጋውን የበ
ለጠ ቁልቁል አወረደው። ወዲያው ማንም ሰው የታሰረ ቦንዳ መግዛት
አቆመ ። ሀብት ማግኘት በድህነት ተተካ ፤ ድህነት በአሜሪካ ምድር
ላይ ሰፈነ።

ማክሰኞ ጥቅምት 29 ቀን 1929 የሸቀጣሸቀጥ ባለቤቶች የ74 ቢሊዮን ዶላር ኪሣራ ደረሰባቸው ። ይህም ቀን "ብላክ ቱውስዴይ"[158] በመባል ይታወቃል። ባንኮች ተዘጉ፤ ብዙ ሰዎች ተቀማጭ ገንዘባቸው ከሰረ፤ የንግድ ሱቆቻቸው ተዘጉ። ብዙ ሰዎች ከሥራቸው ተባረሩ፤ ቤታቸውን እየሸጡ ብድር እየከፈሉ ችግር ላይ ወደቁ ፤ 13 ሚሊዮን ሰዎች ከሥራ ገበታቸው ተፈናቀሉ። ይህ አጋችቶ ማጣት "ግሬት ዲፕሬሽን" በመባል ይታወቃል።

በዚህ ችግር ቤተ ክርስቲያን የሚኼድ የምእመን ቁጥር ቀነሰ። የአባላት አስተዋጽኦ ክፍያ ለመክፈል አለመቻል ደረጃ ላይ ተደረሰ። አይሁዳውያን እና ክርስቲያኖች ችግሩን ለመፍታት የብሔራዊ ስብሰባ (ኮንፍረንስ) አዘጋጁ። የዚህ የኢኮኖሚ ቀውስ ወዲያው ከአሜሪካ አልፎ ከአሜሪካ ጋር የንግድ ልውውጥ የሚያደርጉትን አገሮች ጭምር በችግር ላይ ጣለ፤ ብዙ የንግድ ቦታዎች ተዘጉ፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሥራቸውን አጡ።

ይህ አጠቃላይ ቀውስ ወይም ግሬት ዲፕሬሽን[159] ተብሎ የሚታወቀው ችግር በአሜሪካ አንድ ሦስተኛው ነዋሪ ዜጋ ሥራ አጥና ረሀብተኛ ኾነ ። ከችግሩና ከድህነት የተነሳ መንግሥት የሚያቀርበውን ዳቦ ለመብላት ሰልፍ ተጀመረ ። በኒው ዮርክ ማንሀተን የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ዋና መጠለያ ኾነ ። እነዚያ ቀደም ሲል በሀብታቸው ይፈሩና ይከበሩ የነበሩ ሰዎች ፤ ተርቦ መለመን እንደ ነውር ይቆጥሩት የነበሩ ሕዝቦች ተሰልፈው ይለምኑ፣ ዕርዳታ ይጠይቁ፤ ዳቦ ይመጸወቱ ጀመር። የጥጥ ዋጋ በጣም ረከሰ፤ ነገር ግን ጥጥ ምግብ መኾን አልቻለም። ብዙ ገበሬዎች የእርሻ ቦታቸውን ለመሸጥ ተገደዱ ። አብዛኛውም በየቦታው በመሰደድ ሥራ በማፈላለግና በመፈለግ ጊዜያዊ ሥራ መሥራት ጀመሩ።

ብዙ የፕሮቴስታንት ፓስተሮች ፣ የካቶሊክ ቄሶች ገቢያቸው በመቀነሱ ግማሾቹ አገልግሎት መስጠት አቆሙ። በአንጻሩ የነጭ እና የጥቁር የጴንጤቆስጤ እና የአድቬንቲስት ሰባኪዎች (ፓስተሮች) የተፈጠረውን ኹኔታ በማየት ስለምጽአተ ክርስቶስ መድረስ ስለሚሰብኩ የተከታዩ ቁጥር እየጨመረ ኼደ።

የረሀብ ነገር ሲነሳ በአኹኑ ሰዐት በዓለም ላይ በረሀብተኝነት በቀደምትነት የምትጠቀስ ኢትዮጵያ ነች። ይህም በ1974 (1966 ዓ. ም)

[158] BLACK TUESDAY
[159] GREAT DEPRESSION



በኢትዮጵያ ላይ ሲከሰት ምዕራባውያን በፖለቲካ ፤ ኢትዮጵያውያን ፖለቲካውን ባለማወቅ ፤ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የደረሰውን የራያንና የቆቦን ችግር ለዓለም በከፍተኛ ኹኔታ ይገለጹ ነበር፤ ዕርዳታውም በጣም በተገታ ኹኔታ በጥቂቱ ነበር ። ሰፊው የደቡብና የምዕራብ ክፍል የሲዳሞ፣ የኢሉባቡር፣ የጅማ የሌሎችም ለም የቡናና የፍራፍሬ መሬት አንድም ቀን በዜና ማሠራጫ ሳይታይ ኖረ። በአውሮፓውያን በዜና ማሠራጫ የሚታይ የነበረው ድረሱልን የሚል በረሀብ የሞተችን እናት ልጇ ጡቷን ሲጠባ ማሳየት ነበር። አንዳንዶች የአሜሪካ እና የአውሮፓ ተወላጆች የውጭ ዜጎች ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያን ለማወቅ የሚፈልጉትና የሚያውቋት በረሀብ ነው። በ1974 (1966 ዓ.ም.) እንደገና 1984 (1976 ዓ.ም.) በዐዲሱ የኢትዮጵያ ሚሌንየም ረሀቡ ቀጥሎአል ። እስከመቼ ድረስ በዘፋኙ ሰር. ቦብ ጊልዶፍ አሳሳቢነት ፤ እንዲሁም በቢቢሲ ኢትዮጵያ ቋሚ የምግብ ለማኝ መኾኗንን ሲነገር ይኖራል?

በአሜሪካ እና በዓለም የሚኖሩ የኢትዮጵያ ወዳጆች ጥቁሮቹ አንዳንድ ነጮችም የሚሉት ከገነትን የምትተካከለው ኢትዮጵያ (በጊዮን የተከበበች) እውነት ተርባ ሳይኾን የአስተዳደር ጉድለትና የእርስ በእርስ ተንኮል ስላለ ነው ይላሉ ፤ "የዓባይን ልጅ ውኀ ጠማው" እንደሚባለው ማለት ነው፤ ይህ ለኢትዮጵያውያን የዘላለም አሳዛኝ ገጽታ ነው።

ረሀብና ችግር ከላይ እንደሚታየው ሀብታም ነኝ የምትል አገር አሜሪካ ለአራት ዓመት ችግር መትቷት ነበር ። ልዩነታችን እነሱ ረሀቡን ለማጥፋት ጥበብ በተሞላበት መንገድና ዘዴ ታግለው አሸንፈዋል፤ አግኝቶ ማጣት ፤ ተጣጥሮ ያጡትን ማግኘት በአሜሪካ ምድርም ያለ ነገር ነው። ይህንንም ረሀብና ችግር ለማጥፋት ጥበበኛ መሪ ፕሬዘዳንት ፍራንክሊን ዲ. ሮዜቤልት ለአሜሪካ ታላቅ ሥራ ሠርቶ አልፏል።

## (፩) ፕሬዚዳንት ፍራንክሊን ዲ. ሮዜቬልት (ኤፈ.ዲ.አር)

ፕሬዘዳንት ፍራንክሊን ሮዜቬልት በ1932 አሜሪካንን እንዲመራ 32ኛው ፕሬዘዳንት ኾኖ የተመረጠ ነው ።[160] በንግግሩ መክፈቻ አስደናቂ ንግግር ተናገረ።

"እኛ መፍራት ያለብን ራሱን ፍርሀትን ነው።"[161]

[160] ፕሬዘዳንት ፍራንክሊን የኖረበት ዘመን 1882 – 1945
[161] "Only Thing We Have to Fear Is Fear Itself" FDR's First Inaugural Address

ይህንም የኢኮኖሚ ቀውስ ቶሎ ለማቆም ችግሩንና ረሀቡን ለማቃለል ዕቅድ አወጣ። ይኸም ዕቅድ "ኒው ዲል" ተብሎ ተጠራ ። ይህም ማለት የመጀመሪያው መቶ ቀናት ማለት ነው። የኒው ዲል ፕሮግራም ይዘቱ አዲስ የሥራ መስክ መፍጠር ፤ ኹሉንም በችሎታው ፣ በዕውቀቱ ፣ በተፈጥሮ ዝንባሌው ሳይቀር ማሰለፍ ነበር። በዚህም መሠረት ሕንፃዎችን ፣ መንገዶችን ፣ የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎችን ፤ የአውሮፕላን ማረፊያዎችንና ትምህርት ቤቶችን መገንባት ተያያዙት።

ኰንግረስ መንግሥት ባንክን የሚቆጣጠርበትና የፋብሪካ ሠራተኞችን እንዲሁም ገበሬዎችን የሚረዳ ዐዲስ ሕግ ወጣ። በኹለተኛው የኒው ዲል ፕሮግራም የሥራ ዋጋ ተመን መነሻ ደመወዝ እና የሥራ ሰዓት ሕግ ወጣ፤ ገበሬዎች እርሻቸውን እንዲጀምሩ መንግሥት ብድር ሰጠ። የሶሻል ሴኩሪቲ ሲስተም፤ ይህም ማለት ለችግረኞች እና መሥራት ለማይችሉ ሥራ አጥ ለኾኑ እዲሁም ለአካለ ስንኩላን መንግሥት የሚያደርገው ዕርዳታ ተጀመረ ። ለሥራ አጥ የኢንሹራንስ ፕሮግራም ሕግ ወጣ ። እነዚህ ኹሉ እስከ አኹን እየተሠራባቸው ያሉ ናቸው ። ብዙ ሕጎች ሕዝቦችንና የንግድ ቦታዎችን ከችግር ከዳግም ረሀብ ለማዳን የሚከላከሉ ኾነው ተደነገጉ።

በአሜሪካ በ2008 እንደ ቀድሞው ባይኾንም በቀላሉ ሊገታ የሚይችል ቀውስ ይችላል የሚል ታላቅ ፍርሃት አለ።

ፕሬዚዳንት ፍራንክሊን ሮዜቬልት በድጋሚ ይህን የመሰለ ቀውስ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ እንዳይከሰት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። አሜሪካውያንን ከችግር እና ከረሀብ ያወጣቸው ተወዳጅ እና ታላቅ ከሚባሉት የአሜሪካ መሪዎች አንዱ ነው። ፍራንክሊን ሮዜቬልት ፕሬዚዳንት በመኾን ያገለገለው ከ1933 እስከ 1945 ድረስ ነበረ።

## (፪) የጣሊያን ወረራ ”የኢትዮጵያ ድምጽ” በአሜሪካ

> **ይኄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር እምተአምኖ በእጓለ እመሕያው። ትርጕም ፦ በሰው ከመታመን ይልቅ በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል (መዝ. 117፥8)።**

በአሜሪካ ግሬት ዲፕሬሽን የሚባለው የኑሮ ችግር በተከሰተ በዓመቱ፤ ኹለተኛው የዓለም ጦርነት ከመጀመሩ ከዘጠኝ ዓመት በፊት ኅዳር 1930 (ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም) ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን ኃይለ ሥላሴ በመባል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ኾነው ቅብዐ መንግሥት



ተቀብተው ሲነግሡ ወሬው በዓለም ዜና ተሠራጨ። በአሜሪካ በኒው ዮርክ ከተማ በሀርለም ጥቁር ንጉሥ በመንገሡ በባርነትና በዘረኝነት በነጭ የበላይነት ይሰቃዩ የነበሩ ጥቁር ሕዝቦች መደነቅ እና መደሰት ተዋሕዶባቸው ነበር ። በርግጥ በአሜሪካም ኾነ በአውሮፓ በዙ ጊዜ በሕዝብ መገናኛ አይነገር እንጂ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያ የጥቁር ንጉሥ እንዳልነበሩ የታወቀ ነው።

ማርቆስ ጋርቬይ ቀደም ሲል ታሪከን ለጥቁር ሕዝብ ያስተማረው ፣ የተናገረው ይናፈቅ ነበርና ተፈጸመ ። የአሜሪካ ራዲዮን እና ጋዜጦች (BLACK NEWS-PAPER) ሌሎችም ዜና ማሠራጫዎች በገነተ ልዑል ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የነበረውን የንግሥና ሥርዓት አንዳንድ የሬዲዮ ጣቢያዎች እና ጋዜጦች ከአርእስተ ዜናዎቻቸው አንዱ አደረጉት ። ጋዜጦች በመጀመሪያ ገጻቸው ላይ ፎቶግራፍ ጭምር በማስፈር በአሜሪካ ብቅ ሲሉ የጥቁር ሕዝብ ልብ ተደሰተ።

የቀድሞው ደጃዝማች ተፈሪ ከንግሥናቸው በኋላ ወደ አሜሪካ ተማሪዎችን መላክ ጀመሩ። ከነዚህ ውስጥ ቀደም ብሎ በ1930 በአሜሪካ በኦሀዮ ግዛት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙት መልአኩ በያን በድጋሚ የሕክምና (ሜዲሲን) ትምህርት ጥናታቸውን አጠናቀው በ1936 በሀዋርድ ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዶክተር በመኾን ተመረቁ ። ዶክተር መልአኩ በያን ጥቁር አሜሪካውያንን ወደ ኢትዮጵያ እየወሰዱ ከንጉሡ ጋራ ያስተዋውቁ ነበር።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በዐምስተኛው ዓመት ጣሊያን በሞሶሊኒ አመራር ሥር ዋለች ። በኋላ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመግዛት ለኹለተኛ ጊዜ ሙከራ አደረገች ። ቀደም ሲል በ1888 ዓ. ም በቅኝ ግዛት ለመያዝ በተደረገው ትግል በአድዋ ጦርነት በውርደት ድል በመኾን በዐፄ ምኒሊክ ሽንፈት አግኝቷቸው ነበር ። በዚህ ሽንፈት ቂም ይዘው ኖረው ለመበቀል ወሰኑ ። ሞሶሊኒ የጣሊያንን ሕዝቦች በኢትዮጵያ ምድር ላይ እንደሚያሰፍር ቃል ገባ፤ ሕዝቡንም በፕሮፓጋንዳ ያነሳሳ ነበር።

> **"እንዲት ከኤደን ገነት ጋር የምትተካከል አገር አለች ይህችም ኢትዮጵያ ነች። ዐዲሲቷ የሮማ ግዛት (New Roman Empire) በማድረግ ለተከበረው የጣሊያ ሕዝብ አበረከትለታለሁ" አለ።**

ለማስፋፋት ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ወሰነ። በዚህ ቅስቀሳው የጣሊያ ሕዝብ ደገፊው ሴቱ ኹሉ ለወረራው ድጋፍ የሚኾን ያንገት፣ የጆሮ ወርቁን እያወለቀ ሰጠ።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋራ ለመደራደር ቢፈልግም እንቢ አሉት ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን መኾኑን ቢረዳም ያንን በማጥፋት የሮማ ካቶሊክን ለማስፋፋት እና ሥልጣኔን አስገባለሁ በማለት ፖፑ ጉዞውንና ወረራውን እንዲባርኩለት አደረገ። ከዚያም የአንድ ወር ዝግጅት አድርጎ ሰራዊቱን ወደ ኢትዮጵያ አዘመተ። ጥቅምት 3ቀን 1935 (መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ. ም) 100,000 ሺ የጣሊያን ወታደሮች ኢትዮጵያን ወረሩ ። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፓርላማ ንግግር በማድረግ አዋጅ አወጁ። "በባርነት ከመኖር ለአገር ለነጻነት መሞት አለብን አሉ።"[162]

ጦርነቱ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ግርማዊ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ለአቤቱታ ወደ ጄኔቫ ኼዱ ። ሰኔ 23 ቀን 1935 በተደረገው የ72 የአገር መሪዎች እንዲሁ የተወካይ ሕዝቦች መካከል በጄኔቫ ሸንጎ[163] ፊት ቀረቡ ። በጣሊያኖች እና በደጋፊዎቹ የተናቀው ጥቁር ንጉሥ ብቅ ሲል ፉጨት ተሰማ ነገር ግን አልቀጠለም ። የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንግግር የሚያስቆም አልነበረም ያንን የተንጫጫውን ኹሉ ገረመሙት ፤ ከዚያም ጸጥ ካሰኙ በኋላ ንግግራቸውን ቀጠሉ ። በጉባኤው ዝነኛ ሊኾን የቻለውን ንግግራቸውን ተናገሩ። በመጀመሪያ ለሕዝባቸው ትክክለኛ ፍርድ ለማግኘት ከኢትዮጵያ ተጉዘው እንደመጡ ገልጹ፤ ከአቤቱታው ጥቂቱ እንዲህ የሚል ይገኝበታል።

> የኢትዮጵያ ጦር የጠየቀው መከላከያ ነበር፤ እኔም ለመከላከያ የሚኾን መሣሪያ ጠይቄ ነበር ፤ ይህንንም የጠየቅሁትን ዕርዳታ ተከለከልኩ ። በመንግሥታት ማኅበሩ በ16ኛው ክፍል የተጻፈ ቃል፤ መንግሥቶች እየተባበሩ መረዳዳት እንዳይጠፉ ያደርጋሉ የተባለው የአፈጻጸሙ ስያሜ ምን ይኾን?
>
> ከጅቡቲ እስከ ዐዲስ አበባ የሚኼደው ባቡር ለኢትዮጵያ ወታደሮች መሣሪያዎች የሚተላለፍበትና ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዲያገለግል በተጠየቀ ጊዜ ፤ መሣሪያ በዚያ በኩል እንዳይገባ ብዙ ችግር ተደረገ።

[162] Chronicle of the 20th Century. 1988 p. 455

[163] በ1919 የዓለም ማኅበረሰብ ጉባኤ (the league of Nation) ሲመሠረት ኢትዮጵያ ከአፍሪካ የመጀመሪያዋ መሥራች እና አባል አገር ነበረች። የዚሁ ሊግ ኦፍ ኔሽን ጽሕፈት ቤቱ በጄኔቫ ነበር ። ይህ ጉባኤ ወረራውን ማስቆም ሲገባው አላስቆመም።



> በአኹኑ ሰዓት ግን በኢትዮጵያ ውስጥ በማይገባ ኹኔታ ለገባው ለኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ዋና የስንቅ ማመላለሻ ኾኗል.
>
> ...
>
> ...አኹን በመጨረሻ በመንግሥታት ማኅበር ታላቅ አግባብ ያላቸው ታላላቅ መንግሥቶች በምክር ቤታቸው አጥቂው የኢጣሊያ መንግሥት የኢትዮጵያን መሬት አንዱን ክፍል ከያዘ በገንዘብ ጥቅም ረገድ ይህ እንዳይኾን ያቆምነውን መከላከያ መቀጠል አያስፈልግም ብለው አስታወቁ።
>
> ጥያቄው በአጥቂው በኢጣሊያን ምክንያት የኾነውን ነገር ለመመርመር የተሰበሰበው የመንግሥታት ማኅበር ዋና ጉባኤ ዛሬ በፊቱ የሚገኘው አኳኋን ይህ ኾነ።
>
> ዛሬ የመንግሥታት ማኅበር ዋና ጉባኤ በፊቱ ያለው ጉዳይ ፤ ኢጣሊያ በአጥቂነት የሠራችውን ለመናገር ብቻ አይደለም፤ በሙሉ የዓለምን መንግሥታት የሚነካ ጉዳይ መኾኑን አረጋግጫለሁ ይህንንም አስታውቃለሁ።
>
> ይህ ጉዳይ በዓለም ጸጥታ እንዲኾን መንግሥታት በመረዳዳት የሚገባቸውን ቪቶ ኮኔክቲቭ የመንግሥታት ማኅበር ሕይወት፤ የዓለም መንግሥታት በተዋዋሉት ውል መስጠት የሚገባቸውን እውነት፤ ትንንሾቹን መንግሥቶች አገራቸውና ነጻነታቸው እንዳይነካ የተቀበሉትን ቃል ኪዳን የሚከበርበትን ዋጋ የሚገመትበት እና የመንግሥታት እኩልነት የተመሠረተበት ምክንያት፥ መሠረት ለማጽናት ወይም ትንንሾች መንግሥቶች ኀይለኞች መንግሥቶች ተገዢ ለመኾን መቀበል ይገባቸው እንደኾን ለመፍረድ ነው።...

በማለት ገለጹ ፤ በንግግራቸው ማጠቃለያ

> "ምን መልስ ይዤ ልመለስ? ፍርዳችኹን እግዚአብሔርና ታሪክ ይመለከተዋል ዛሬ በእኛ የተደረገው ነገ በእናንተ ይደርሳል።

በማለት ትንቢታዊ ንግግር ተናገረው ከንግግር ቦታው ላይ ወረዱ ። ንግግሩ በጉባኤው ላይ የተሳተፉትን የጣሊያን መልእክተኞችን አስደነገጠ። የዓለም መንግሥታት መሪዎች (ሊግ ኦፍ ኔሽን) የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ማስጠንቀቂያ ችላ ብለው ጣሊያን ኢትዮጵያን እንድትወር እንድትገፋበት አደረጉ፤ ለጥያቄው መልስ አልሰጡም ። ይህ የሚደነቀው ንግግራቸው በአሜሪካ ሕዝቦች ዘንድም ተሰማ ፤ በይበልጥ ጥቁር ሕዝብ አስቆጣው ፤ ኢትዮጵያን ለመርዳት ተነሳሳ።

የነጭ የበላይነትን የማይቀበለው ፤ ሃይማኖቱን፣ አገሩን የሚወድ፤ በታላቅነቱ የሚያምን ኢትዮጵያዊ በሰማዕትነት ለመሞት ቆርጦ ተነሳ ። የጦር መሣሪያ ቢከለከልም ያለውን ጋሻ እና ጎራዴውን ፤ ቤልጂግ ፣ ዲሞትፎሩን እና ናስማሠሩን ይዞ ውጊያውን ገጠመ ። ለአገሩ ክብር ፣ ለነጻነቱ ሰማዕት ኾኖ አለፈ።

የሞሶሊኒ ጦር ሐምሌ 22 ሊቀጳጳሱን አቡነ ጴጥሮስን ገደለ፤ በጥቅምት ወር ንብጌ ገዳም እና ዝቋላ ገዳምን አቃጠለ። ግንቦት 13 ቀን 1936 (1929 ዓ. ም.) ደብረ ሊባኖስን ዘረፉ ። 300 የሚኾኑ መነኰሳት በጥይት ተደብድበው ተገደሉ ፤ ገዳሙ ተዘጋ። 25 የሚደርሱ የማኅበረ ሥላሴ መነኰሳት ተገደሉ።[164] ይህ የመንፈሳዊውን ብቻ የተመለከተ ነው።

ሞሶሊኒን የሾመው የጣሊያ ንጉሥ ቪክቶር ኢማኑኤል የሰሎሞን የንግሥና ስርወ መንግሥትን ተመኘ፤ ተመኝቶም አልቀረ ግንቦት 9 ቀን 1936 የጣሊያን ንጉሥ በሚለው ተጨማሪ ሥልጣን ላይ ቅብዓ መንግሥት ሳይቀባ፤ ድልን ሳይቀዳጅ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ብሎ ራሱን ሾሞ አነገሠ ። ነገር ግን በታሪክም ኾነ በኢትዮጵያውን ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም።

በዚህ ጊዜ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ አሜሪካ ኒውዮርክ ጥቁርን ሕዝብ እንዲያነሳሳ ዶክተር መላኩ በያንን መመሪያ ሰጥተው ላኩ ። ዶክተር መልአኩ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ከኾነች ጥቁር አሜሪካዊት ሚስታቸው ዶረቲ ሄድሊን ጋራ በመኾን "የኢትዮጵያ ድምጽ" (VOICE OF ETHIOPIA) የሚል ጋዜጣ በአሜሪካ እያዘጋጁ ያወጡ ጀመር።

**ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።**
**የምድር ነገሥታት ለእግዚአብሔር ተቀኙ ፤ ለጌታም ዘምሩ።**
**(መዝ. 67(68)፥31)**

የሚለውን የመዝሙረ ዳዊት ጥቅስ በመጻፍ የሚበተን ወረቀት እያዘጋጁ የአሜሪካንን ሕዝቦች ይቀሰቅሱበት ነበር። በዚህም ጥቅስ ጥቁር ሕዝብ ኢትዮጵያ ማለት እኛ ነን በማለት ተነሳሳ ። ዛሬ ድረስ ጥቁር ሕዝብ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለው በዓለም ኹሉ የተበተነውን ጥቁሮች ያጠቃልላል እና እኛም ነን የሚለው ስሜቱ እንደቀጠለ ነው።

[164] ጌታቸው ኃይሌ ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቆጠራ ቅርሳችንን ገጽ 273



ጣሊያን ኢትዮጵያን በመውረሯ የጭካኔ ተግባር በመፈጸሟ የዓለምን ሕዝብ አስቆጣ። በኒው ዮርክ ሀርለም ያሉ የጣሊያን ነዋሪዎች እና ጥቁሮች በመካከላቸው ታላቅ ብጥብጥ ተነሳ። የኒው ዮርክ ነዋሪ ጣሊያኖችም ወረራውን ተቃወሙ ። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ በአሜሪካ የሚኖሩ ጥቁር ሕዝቦች እና የኢትዮጵያ ወዳጆች በሀርለም ተሰልፈው በመውጣት ሞሶሊኒ ይውደም! (Down with Mussolini) እያሉ ተቃውሟቸውን አሰሙ ። ይህ የኢጣሊያ ወረራ ለአፍሪካውያን አንድነት (ፓን አፍሪካ) እንቅስቃሴ የበለጠ እንዲፋፋ እና አንድነት እንዲኖርው አስተዋጽኦ አድርጓል።

ጣሊያን ኢትዮጵያን ከወረረች ከሦስት ዓመት በኋላ የንጉሡ ትንቢት ተፈጸመ ። የሙሶሊኒ ጓደኛ ሒትለር ፖላንድን ከዚያም ፈረንሳይን ወረረ ። በዚህ የተነሳ የኹለተኛው የዓለም ጦርነት በአውሮፓ ተቀሰቀሰ ። ሞሶሊኒም ከአሸናፊ ወገን የኾነ መስሎት በፈረንሳይ እና በእንግሊዝ ላይ የጦርነት አዋጅ አወጀ ። የሞሶሊኒ በአውሮፓውያን ጦርነት ተካፋይ መኾን የኢትዮጵያን እና የብሪታንያ ጦር ጓደኛነት ፈጠረ ። ለዐራት ዓመት ብቻቸውን ይዋጉ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ዐርበኞችን ለመርዳት ብሪታንያ ወሰነች።

በአሜሪካ አገር የነበሩት ዶክተር መልአኩ በያን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በቀይ መስቀል ውስጥ ተሰማርተው በጦርነቱ የቆሰሉትን ኢትዮጵያውያንን ያክሙ ነበር ። የዶክተር መልአኩ በያን አያታቸው የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እናት የወይዘሮ የሺ-እመቤት እኅት ናቸው።

መላኩ በያን በአሜሪካ ያቋቋሙት ኢትዮጵያ ወርልድ ፌዴሬሽን የካሪቢያንን ደሴቶች ጨምሮ 28 ቅርንጫፎች ነበሩት። የድርጅቱ አርማ እና የአባልነት መታወቂያ ካርድ ነበራቸው።[165] በየጥቁር ጸሎት ቤት እንዲሁ በአደባባይ ሞሶሊኒ ይውደም! (Down with Mussolini) በማለት የፋሽስት ወረራን የሚገልጽ ጽሑፍ በማዘጋጀት ኢትዮጵያን አድኑ (SAVE ETHIOPIA) የሚል ትናንሽ የመቀስቀሻ ጽሑፎች ይበተኑ ነበር። ለጦርነቱ ገንዘብ ይዋጣ ነበር፤ ጄነራል ካርናል ዶንቢ እና ሌሎችም ጥቁር ጀት አብራሪዎች እንዲሁም 37 000 ሺህ በላይ አፍ

[165] We the Black Peoples of the World in order to effect Unit, Solidarity, Liberty, Freedom and Self determination to secure Justice and maintain the Integrity of Ethiopia. Which is our divine heritage. Do hereby establish and ordain this Constitution for the Ethiopian World Federation, Incorporated.

ሪካን አሜሪካን ኢትዮጵያን ለመርዳት ለጦርነቱ ውጊያ ተመዝግበው
ነበር። ኸርበርት ጁሊያን በቅጽል ስሙ "ብላክ ኢግል ኦፍ ሀርለም"
የተባለው አውሮፕላን አብራሪ ለመጀመሪያ ጊዜ አውሮፕላን ይዞ ወደ
ኢትዮጵያ ምድር ገባ ፤ በኋላም የአየር ኃይልን በማሠልጠኑ እና
በመምራቱ የኢትዮጵያዊነት ዜግነት ተሰጠው።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል ከዐምስት ዓመት የእንግ
ሊዝ አገር ኑሮ በኋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው የኢትዮጵያ የነጻነቷን
አዋጅ አሳወጁ ። ጦርነትና ስደት አብቅቶ እንደተመለሱ እንጦጦ ራጉ
ኤል ሲያስቀድሱ ከተጸለየው አንዱ የመዝሙረ ዳዊት ምስባክ (ጸሎት)
እንዲህ የሚል ነበር ።

> ይኄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር እምተአምኖ በእጓለ እመሕ
> ያው ። <u>ትርጉሙ፦</u>
> በሰው ከመታመን ይልቅ በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል ፤
> በገዥዎች ተስፋ ከማድረግ ይልቅ በእግዚአብሔር ተስፋ ማድ
> ረግ ይሻላል ፤ አሕዛብ ኹሉ ከበቡኝ በእግዚአብሔር ስም
> አሸነፍኋቸው (መዝ. 117 ፥8) ። የሚል ነበር ።[166]

ኢትዮጵያ በቅኝ አገዛዝ ሊይዛት የመጣውን የጣሊያንን መንግሥት
ለኹለተኛ ጊዜ በማሸነፍ ድልን ተቀዳጀች። የጣሊያን አብሪት እንደ
ጎልያድ ነበር ። እግዚአብሔር ግን ጦር እና የጦር ልብስ ያልነበረው
ትንሹ ዳዊት ጎልያድን ድል እንዲያደርግ እንደረዳው ኹሉ፤ ዘመናዊ
ጦር እና ትጥቅ ያልነበራቸውን ትጥቃቸው እምነታቸው ብቻ የነበረ
ኢትዮጵያውያን ዐርበኞች እንደ ዳዊት ታላቁን ጦር ድል አደረጉ።

የአሜሪካ ነዋሪ ጥቁሮች በዚህ ጦርነት ኢትዮጵያን ለመርዳት
ፈቃደኝነታቸውን አሳይተዋል። የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሊግ
ኦፍ ኔሽን ትንቢታዊ ንግግር ፍጻሜ ማግኘቱ በአሜሪካና በዓለም የበለ
ጠ ክብርን ለኢትዮጵያውያን እና ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ገና
ናንትን አስጥቷል። ዛሬም በአሜሪካ በዓለም ጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን
ዐርበኞች የኢትዮጵያን እና የአፍሪካን ልጆች (አፍሪካን አሜሪካንን)
አኩርቷቸዋል።

[166] ምንጭ የተገኘው በጊዜው በቦታው ላይ አገልግሎት ይሰጡ ከነበሩት ከመ
ምሬ ብሥራት ወልደ አማኑኤል የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ የዲቁና ትምህርት
ሲያጠኑ የተነገራቸው ነው።



(፫) የጀርመን ወረራ

> "ፍርዳችኹን እግዚአብሔር እና ታሪክ ይመለከተዋል፤
> ዛሬ በእኛ የተደረገው ነገ በእናንተ ይደርሳል"። (ግርማዊ ቀዳ
> ማዊ ኃይለ ሥላሴ)

ይህ ትንቢት ቃል የተነገረበት ምክንያት ኢትዮጵያ እንድትደበደብ
ዝም ያሉት ፤ የመሣሪያ ዕርዳታ እንዳታገኝ ማዕቀብ የጣሉባት፤ የአን
ድነት ማኅበሩ ወይም የሊግ ኦፍ ኔሽን ወረራውን ማስቆም ሲገባ እኛም
ሌላውን የአፍሪካ አገር በቅኝ ግዛት ይዘናል፤ ጣሊያንም በቅኝ ግዛት
መያዝ ይገባታል ብለው በተዘዋዋሪ ድጋፍ በማድረግ ዝም ያሉት ኃያ
ላን መንግሥታት እግዚአብሔርም ክፋታቸውን አየ ፍርድም አልቀረላ
ቸውም ፤ አውሮፓውያን ላይ ከፍተኛ የጦርነት እልቂት ደረሰባቸው።
ዛሬ በእኛ የተደረገ ጭካኔ በናንተም ይደርሳል የተባለው ትንቢት
ተፈጸመ።

ከ1939 እስከ 1945 ባለው ጊዜ የኹለተኛው የዓለም ጦርነት
ተቀሰቀሰ ። የጦርነቱ መነሻው ጀርመን ፖላንድን በ1939 በመውረሯ
ነው። የሒትለር ዓላማ በጀርመን ዙሪያ ያሉ አገሮች ኹሉ የጀርመን
ግዛቶች ለማድረግ ከዚያም ኮሚኒዝምንና አይሁዳውያንን ለማጥፋት
ነበር። ኹለተኛው ደግሞ ጃፓን ቻይናን በመውረሯ ፤ ጣሊያን ኢትዮ
ጵያን በመውረሯ ሌሎችም የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮችን ጨምሮ
ኹሉም ዘንድ ጦርነት ተነስቶ ነበር ። ይህን የኢትዮጵያን ጦርነት ምዕ
ራባውያን ኹለተኛ የዓለም ጦርነት ታሪክ ውስጥ በጥቁር በመሸነፋቸው
ውርደት ስለሚመስላቸው ለማስገባት አይፈልጉም።

ሒትለር የተወለደው ሚያዚያ 20 ቀን 1889 በኦስትርያ አገር
ሲኾን በክርስትና ሃይማኖት ደግሞ የተጠመቀው በሮማ ካቶሊክ ቤተ
ክርስቲያን ነው ። በኋላ ዘመኑ ግን የሮማ ካቶሊክ ቀሳውስቶች ጦር
ነቱ እንዳይቆጥል በመፈለጋቸው ጠልቷቸዋል ። እንዲሁም የፕሮቴስ
ታንት ፓስተሮችን ይሰድባቸው ነበር ። ከእስር ቤት በ1925 ሲወጣ
መጽሐፍ ጽፎ ወጣ (My Struggle)። ሒትለር የሞሶሊኒ የቅርብ ወዳጅ
ነበር። በ1933 የጀርመን ቻንስለር ኾነ።

አዶልፍ ሒትለር ቻንስለር ኾኖ እንደተመረጠ ጀርመን የተከ
በረ ሕዝብ ስለኾነ መጀመሪያ ጀርመንን ከዚያም የጀርመን ሕዝብ
ይዞታዋንም ማስፋፋት አለባት ፤ ዓለምን መግዛት አለበት የሚል የእብ
ሪት አመለካከቱን ይናገር ጀመር ፤ ወዲያው ፈላጭ ቆራጭነቱን

ቀጠለ። የፖለቲካው ግፊት የናዚ ፓርቲ ፕሮፖጋንዳ ሕዝቦቹ ዓለምን እንዲወሩና ኹለተኛው የዓለም ጦርነት እንዲቀሰቀስ አደረገ።

በዓለም ኃያል ነች ተብላ የምትታወቀው አሜሪካ በመጀመሪያ ወደ ጦርነቱ ያልገባችበት ምክንያት የራሷ የኢኮኖሚ ችግር ስለነበረባት ነበር ። በኋላ ግን ይህ የዓለም ጦርነት መጀመሩ ለኢኮኖሚዋ ከፍተኛ ጠቀሜታን ሰጠ ። ይህም ወታደራዊ ትጥቅ ፤ መሣሪያ በማምረት እና ለገበያ አቅርቦ በመሸጥ የተንኮታኮተውን የአሜሪካ ኑሮ እንዲንሰራራ አደረገው ። ብዙ ሰዎች በመሣሪያ ማምረቻ ፋብሪካ ውስጥ ለመሥራት ዕድል አገኙ። አሜሪካ የመጀመሪያዋ የኒኩለር ቦምብ አምራች ነበረች። ይኽን የምታመርተውን የጦር መሣሪያ ፣ ቦንቦች እና ሌሎችንም በመርከብ ለብሪታንያ ስታጓጓዝ በመርከቦቿ ላይ በጀርመኖች ጥቃት ደረሰ።[167] አሜሪካ የጃፓንን ጦር ከቻይና ፣ ከፊሊፒን ፣ ከበርማ ለማስለቀቅ ጦርነት ከጃፓን ጋር ገጠመች።

ጃፓንም በታኅሣሥ 7 ቀን 1941 የአሜሪካን ግዛት የኾነችውን ሀዋዪ ደሴት ወደብ (ፓርል ሀርበርን) ደበደበች። በዚህ ምክንያት ከጃፓን ጋር ጦርነቱ ተጀመረ። ከጀርመንም ጋር በሂትለር ጦር የሚጨፈጨፉትን አይሁዳውያንን ለማዳን እንዲሁም ብሪታንያን ለመርዳት ጭምር ጦርነት ላይ ተሳተፈችበት ። የብሪታንያው ጠቅላይ ሚኒስትር ዊንስተን ቸርችል እና የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ፍራንክሊን ሮዜቬልት በፖላንድ ዲሞክራሲ ለማስፈን ፈልገው ነበር ። በአንድ ላይ በመኾን ምክክር ያደርጉ ነበር።

በ1933 እስከ 1945 መካከል 6 ሚሊዮን አይሁዳውያን ፤ የጂፕሲ የሚባሉት ኅብረተሰቦች እና የሶቬት ኅብረት የጦር ምርኮኞች በኦሸዊትዝ ዳቦ መጋገሪያ እንዲቃጠሉ ተደርገዋል ። በኋላም ብሪታንያ፣ አሜሪካ ፣ ፈረንሳይ ፣ ሶቭት ኅብረት ሌሎችም ተባብረው የሒትለርን ጦር አሸነፉ ። ሒትለር በጦርነት በመሸነፉ ሚያዚያ 30 ቀን 1945 ሽጉጡን በራሱ ላይ አድርጎ ጠጥቶት ሞተ።

የሒትለር የቅርብ ጓደኛ ሞሶሊኒ በኢትዮጵያውያን ዐርበኞች በመሸነፉ የራሱ የፋሽስት ፓርቲ አገለለው ። የጣሊያን ንጉሥ ዐዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር በምትኩ ተካ ። ኢትዮጵያውያንን ሲወር አይዞህ ያሉት ወርቃቸውን እያወለቁ በመስጠት የደገፉት የጣሊያን ሕዝቦች በኋላ ተጸጸቱ ። በመርዛማ (ሙስታርድ) ቦንብ ያስደበደበው ፤ በድኝ (ሳልፈሪክ አሲድ) ያስጠበሰው ፤ ገዳማትን መነኩሳትን ያስፈጀው

[167] Chronicle of the 20th Century. p. 553, 554



ሞሶሊኒ በፓርቲዣን ፓርቲ ተይዞ በሞት እንዲቀጣ ተፈረደበት። ሚያዚያ 29 ቀን 1945 በሚላን ከተማ በሕዝብ መካከል ከነፍቅረኛው የቁልቁል አንጠልጥለው ሰቅለው ገደሏቸው። ከሒትለር ጋር የሞቱበት ቀን ልዩነቱ የአንድ ቀን ብቻ ነው።[168] ሰው የዘራውን ያጭዳል እንደተባለው ሞሶሊኒም ሒትለርም የእጃቸውን አገኙ ። ይህም ከእግዚአብሔር የታዘዘ ነው።

ይህ የኹለተኛው ዓለም ጦርነት ከማብቃቱ በፊት በ1945 የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ፍራንክሊን ሮዜቬልት ፤ የብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ቸርችል እና የሶቭየት ኅብረት ፕሬዚዳንት ጆሴፍ እስታሊን በአንድ ላይ በመኾን ጉባኤ አደረጉ ። በዚህ ጉባኤ የተነጋገሩበት አንዱ እና ትልቁ ጉዳይ ቀደም ብሎ የተቋቋመው የዓለም ማኅበረ ሰብ ጉባኤ(ሊግ ኦፍ ኔሽን) ይህንን የኹለተኛውን የዓለም ጦርነት ማስቆም ባለመቻሉ በሌላ መልክ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ዩናይትድ ኔሽን) እንዲቋቋም ተደረገ ። የዚህ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሰብሰቢያ ቦታ በአሜሪካ በኒው ዮርክ ከተማ ኾነ ። ከዚህ በኋላ ኃያል መንግሥት ነኝ የምትለው እንግሊዝ የዓለም መሪ መኾኗ ቀርቶ አሜሪካ የዓለም መሪ ኃያል መንግሥት ኾነች።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ዩናይትድ ኔሽን) ከተመሠረተ በኋላ ፤ አሜሪካ የዓለም ኃያል መንግሥት በመኾኗ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፕሬዚዳንት ሮዜቬልት ጋራ የካቲት 13 ቀን 1945 ኩንሲ ላይ ተገናኝተው ስለኹለቱ አገሮች ወዳጅነትና ስለ ኹለተኛው የዓለም ጦርነት ተነጋግረው ነበር። ከዚያም በመቀጠል ሥልጣኔ ወደኢትዮጵያ ለማስገባት ከአሜሪካ ጋር ወዳጅ ለመኾን የቀጠሉበት ጊዜ ነው። ይህ የፕሬዚዳንቱ እና የንጉሠ ነገሥቱ ግንኙነታቸው እና ፎቶግራፋቸው በአሜሪካና በዓለም ጋዜጣዎች ሲሰራጭ የበለጠ አፍሪካን አሜሪካንና በካሪቢያን ደሴት ያሉትን ጥቁር ሕዝቦችን አስደስቷቸዋል።

ፕሬዚዳንት ሮዜቬልት የኹለተኛ ዓለም ጦርነት ሊያበቃ ዐራት ወራቶች ሲቀሩት የፕሬዚዳንትነት ዐራተኛ ዙሩን ሳይፈጽም ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር በተገናኙ ልክ በኹለተኛው ወር ሚያዚያ 12 ቀን 1945 በሞት ተለዩ ። በአሜሪካ ታሪክ የመጀመሪያ ፕሬዚዳንቱን የጆርጅ ዋሽንግተንን ቃል ሳይፈጸም ዐራተኛ ዙር (13 ዓመት) የመራ ፕሬዚዳን ሮዜቬልት ብቻ ነው።

[168] Chronicle of the 20th Century. p. 621

## (፲) ፕሬዚዳንት ሀሪ ትሩማን (ባፕቲስት)

ሮዜቬልት የፕሬዘዳንት የሥልጣን ዘመኑ ሳይፈጸም በማረፉ ቤሱ ምትክ የተተካው ፕሬዚዳንት ሀሪ ትሩማን ነበር ። ይህም ሰው በባፕቲስት እምነት ያደገ ሰው ሲኾን የፍሬሜሰን እምነት ተከታይ ከኾኑት አንዱ ፕሬዚዳንት እንደኾነ ይነገራል። ኹለተኛው ዓለም ጦርነት በአውሮፓ እንዳበቃ ለተወሰነ ወራት በመንግሥት ሥልጣን ቆየ ። በዚህ ጊዜ በጃፓኖች ላይ ጥቃት አድርሷል።

ጃፓኖች ለብዙ ዘመን ለአውሮፓውያን እና ለአሜሪካውያን በራቸውን ሳይከፍቱ ባህላቸውን ጠብቀው የኖሩ ሕዝቦች ናቸው ። በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግን ወታደራዊ ኃይላቸው ተጠናክሮ በ1937 ቻይናንና የፓስፊክ ደሴቶችን በጦርነት ወረሩ። በወታደራዊ ኃይላቸው በመጠናከር ምሥራቁን ዓለም ለመቆጣጠር አሰቡ። አሜሪካና ቻይናውያን ይቀራረቡ ስለነበር አሜሪካ በጃፓን ላይ ጥላቻዋን አሳደረች ። ከዚያም ከላይ እንደተገለጸው ጃፓን የአየር ኀይሏን እና የምድር ኃይሏን ተጠቅማ በታኅሣሥ 7 ቀን 1941 ሀዋዪ ደሴት ፓርል ሀርበርን ደበደበች ፤ ጦርነቱ ቀጠለ። አሜሪካውያን በጦርነቱ ጃፓንን ማሸነፍ አቃታቸው ፤ በዚህ ወቅት የኹለተኛው የዓለም ጦርነት ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያበቃ ጥረት የተደረገበት ጊዜ ነበር። በዚህ ምክንያት በጃፓን ከተሞች የሰፈሩትን የጦር ካምፕ እና የወታደር ማሠልጠኛ ለመደምሰስ አሜሪካኖች ዝግጅት አደረጉ።

በብሪታንያ እና በአሜሪካውያን ሳይንቲስቶች በኒው ዮርክ በተሠራው የአቶሚክ እና የዩራኒየም የመርዝ ቦምብ ጃፓንን ለመምታት ወሰኑ ። ለዚህም ተልእኮ ፈጻሚ የሚኾን የአየር ኃይል ታዋቂ አብራሪ የኾነው ፓውል ዋርፊልድ ቲቤትስ ተመረጠ። ይህ ሰው በ1942 በጦር አውሮፕላን የጀርመንን ኀይል በመደምሰስ ታላቅ ተጋድሎ የፈጸመ ሰው ነው ። እሱም የመጀመሪያውን የመርዝ ቦምብ እንዲጥል ታዘዘ። ከዚህ በፊት በሰው ልጆች ላይ ያልተሞከረ ኹለት የአቶሚክ ቦምብ በጃፓናውያን ላይ በጭካኔ አወረዱባቸው። ነሐሴ 6 ቀን 1945 የአሜሪካ ቢ. 29 ቦምብ ጣይ አውሮፕላን በዓለም ላይ የመጀመሪያውን የዩራነየም ቦምብ በጃፓን በሒሮሺማ ከተማ ላይ ጣለ፤ አንድ ሚልዮን ሰዎች ተለብልበው ሲሞቱ አንድ ሚልዮን ሰዎች ያለመጠለያ ቀሩ። ከዐራት ቀን በኋላ የጃፓን መንግሥት ተሸንፌአለሁ ብሎ እጅ እንዲሰጥ ነሐሴ 9 ቀን ኹለተኛውን ቦምብ በናጋሳኪ ከተማ ላይ ጣሉ፤ 60 ሺ ሰዎች እንደዚሁ አለቁ ። ከሞት የተረፉት የከተማዋ ሕዝቦች በቦ



ምቡ ጨረር ምክንያት ለዘመናት ሰውነታቸው በቁስል ይጠበስ እንዲሁ የሚወለዱት ሕፃናት አካለ ስንኩሎች ኾነው ይኖሩ ነበር ። ፕሬዚዳንት ትሩማን ይህን ትእዛዝ ያዘዘው በተወሰኑ አማካሪዎቹ ተመክሮ ነበር።[169]

በአኹኑ ጊዜ ይህ ኒኩሊያር ቦምብ በዓለም ላይ ስምንት አገሮች አላቸው። ከነዚህም የመጀመሪያዋ አሜሪካ ስትኾን ራሽያ ፣ ፈረንሳይ ፣ ቻይና፣ ብሪታንያ፣ ህንድ፣ ፓኪስታን እና እስራኤል ናቸው። በሰሜን ኮርያና በኢራን ግን ከመጠርጠር በስተቀር የታወቀ ብዙ ነገር የለም። ነገር ግን ይህ የኒኩሊያር ማምረቻ አላቸው እየተባለ ይወራል። በዓለም 185 አገሮች ይህ ነገር የላቸውም ። ወደፊት ዓለምን የሚያሰጋው ይህ መሣሪያ ነው። ኃያልነቱም እንደ ኹለተኛው የዓለም ጦርነት በጃፓን ሒሮሺማና ናጋሳኪ ከተሞች ላይ የወረደው ዓይነት ሳይኾን በጣም የረቀቀና ዓለምን ለማጥፋት የሚችል መኾኑ ይነገራል።

## (፳) አሜሪካ አይሁዳውያንን አሰፈረች

በሒትለር ከመቃጠል የተረፉት አይሁዳውያን በአሜሪካ አጋዥና ረዳትነት ወደ አባቶቻቸው ምድር መመለስ የጀመሩት እና በመንግሥት ደረጃ የተመሠረቱት በ1948 ነው ። ከዚህ ዘመን በኋላ ብዙዎች አይሁዳውያን ዝርያ ከተሰደዱበት አሜሪካ ፣ ራሽያ፣ ፖላንድ፣ ከሌላ ቦታዎችም ወደ አገራቸው ገብተዋል።

አይሁዳውያን ቀደም ሲል ከአገራቸው ወጥተው መበተናቸውን እና እንደገና መሰብሰባቸውን የሚገልጽ ትንቢት ተነግሮላቸው ነበር ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 የመቅደሱን መፈራረስ ፤ የአይሁዳውያንን መበተን እና የእንስሳት መሥዋዕት መቅረቡ መጨረሻ መኾኑን የተናገረው ትንቢት እሱ ከዐረገ በኋላ በ70 ዓ. ም. ተፈጽሞ ነበር። የትንቢቱ ፍጻሜ የኾነው ቲቶ (ጥጦስ) ኢየሩሳሌምን ተቆጣጥሮ ቤተ መቅደሱን በማቃጠል እና ከተማይቱን በመደምሰሱ እነሱም ተበትነው ነበር ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አይሁድ ዝርያ ሁሉ ከአገራቸው ወጥተው በመላው ዓለም በየቦታው ተበትነው ይኖሩ ነበር። ይህ የመበታተን ጊዜ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ በአንድ ትውልድ ዘመን የተፈጸመ ነው።

[169] Chronicle of the 20th Century. p. 630 - 631

እነዚህ የተበተኑት አይሁዳውያን በሒትለር ከመቃጠል የተረ
ፉት ወደ አባቶቻቸው ምድር ተመልሰው መኖር ሲጀምሩ የኢትዮጵ
ያም ንጉሥ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የእስራኤል መንግሥት እን
ዲመሠረት ከአሜሪካ ጋር ተባብረው ነበር ። ስለዚህም በ1948 እሥራ
ኤል በመንግሥት ደረጃ ተመሠረተች። ነገር ግን ከተማዋ ኢየሩሳሌም
በዓረቦች እጅ ተይዛ ነበር ። በሰኔ 1967 ከዓረቦች ጋር ስድስት ቀን
የፈጀ ጦርነት ተደርጎ ኢየሩሳሌምን በማስለቀቅ አይሁዳውያን ወደ
ሰሎሞን ግንብ ተጠግተው መጸለይ ጀመሩ ።[170] ጌታችን ኢየሱስ ክርስ
ቶስ በለስ ስታቆጠቁጥ አስተውሉ ያለው ቃል ተፈጸመ።

> ምሳሌም ነገራቸው እንዲህ ሲል ፦ በለስንና ዛፎችን ኹሉ እዩ
> ሲያቆጠቁጡ ተመልከታችሁ በጋ አኹን እንደቀረበ ራሳችሁ
> ታውቃላችሁ ። እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይህ ኹሉ መኾኑን
> ስታዩ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ቀረበች እወቁ (ሉቃ.
> 21፥29 – 30)።

ይህም ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመምጫው ጊዜ እንደቀረበ
የሚያመለክት ቃል ነው ። የበለስ ማቆጥቆጥ ምሳሌ የአይሁዳውያን
መመለስ ነው። ብዙ ጊዜ አይሁዳውያን በቅዱስ መጽሐፍ በበለስ ይመ
ሰላሉ፤ በዚህ ዘመን ከየአህጉራቱ ወደ እስራኤል እየገቡ ነው። ከኢት
ዮጵያም ኢትዮጵያውያን አይሁድ ወይም ፈላሻ ተብለው በኢትዮጵያ
ውያን ዘንድ የሚታወቁት በመጀመሪያ በ1985 ቀጥሎ በ1991 ኹለተኛ
ጊዜ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በአውሮፕላን ተግዘው ወደ እሥራኤል
ምድር ገብተዋል።

አሜሪካ በአኹኑ ጊዜ ስድስት ሚሊዮን አይሁዳውያን ይኖሩባ
ታል ። ብዛት ያላቸው አይሁዳውያን በኒው ዮርክ እና በካሊፎርኒያ
ይኖራሉ። በኒው ዮርክ ሊበዙ የቻሉበት ምክንያት በጦርነቱ ጊዜ በጀር
መናውያን ሲሰደዱ መግቢያው በር ስለነበረ ነው ። በአሜሪካ ኾነው
አገራቸውን ይረዱ ነበር። የታወቀው የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የፊዚ
ክስ ሳይንቲስት የነበረው አይሁዳዊው አልበርት አንስታይን ከጀርመን
ወደ አሜሪካ ተሰደው ከኼዱት ምሁራን አንዱ ነበር። በዚያም ኾኖ
የፊዚክስ ጥናቱን በማካኼድ የዩራኒየም ቦምብ ፈልስፏል።[171] በአሜሪካ
ብዙ አይሁዳውያን በጣም የተማሩ ሙያተኞች ይኖራሉ፤ አብዛኛዎቹ

[170] Chronicle of the 20th Century. p. 965
[171] *ቶም ሔስ ፤ ለኢየሩሳሌም ሰላም ጸልዩ ገጽ 7*



በሀብት የበለጸጉ ናቸው። በኢኮኖሚው፣ በሳይንሱ፣ በመንግሥት አስተ
ዳደር ኹሉ ገብተው ለአሜሪካ ጥቅም ይሰጣሉ።

ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተገኘው ውጤት አሜሪካ
በሀብት ስትበለጽግ በተቃራኒው ደግሞ የጀርመን ከተሞች ፈራረሱ ።
አገሪቷ ምሥራቅና ምዕራብ በመባል ለኹለት ተከፈለች ። ቀስ እያለ
ግን አውሮፓም የሀብት ብልጽግና መጣ ፤ የሰው ፍላጎት ወደ ቁሳቁስ
ላይ በማዘንበሉ የክርስትና እምነት እየተዳከመ ኼደ።[172] ይህም የክር
ስትና እምነት መዳከም በዘመናችን የምናየው የአውሮፓውያን አሳፋ
ሪው ገጽታ ነው።

## (፮) ፕሬዚዳንት ድዋይት ኤይሰንሀወር (ጀሆቫህ ዊትነስ)


በአሜሪካ ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ፕሬዚዳንት የኾነው
አንዱ ድዋይት ኤይሰንሀወር ነው። በኹለተኛው ዓለም ጦርነት ብዙ
ሚና የተጫወተ ጀብዱ የፈጸመ በመኾኑ የሜጀር ጀነራልነት ማዕረግ
የተሰጠው ሰው ነው።[173] በዚህ በቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን የአሜሪካ
ፕሬዘዳንት ከኾኑት አንዱ ነበር ።

ኤይሰንሀወር እናቱ የጀሆቫህ ዊትነስ አባል ስለነበረች በመ
ጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ እየተሳተፈ ያደገ የጀሆቫህ ዊትነስ አባል
ነበር። ጀሆቫህ ዊትነስ ጦርነትን ፣ ውትድርናን ፣ ለባንዲራ ክብር መስ
ጠትን የሚቃወም ሃይማኖት ነው። ኤይስነሀወር ከጓደኞቹ ጋር ኾኖ
የወታደር ማሰልጠኛ ገባ ። በዚህ ጊዜ የጀሆቫህ ዊትነስን ሙሉ አገልግ
ሎቱን አቆመ ። በኋላ በየካቲት 1 ቀን 1953 የአሜሪካ ፕሬዚዳንት
ከኾነ ከ12 ቀን በኋላ በፕሬስቤተርያን የክርስትና እምነት ተከታይ
በመኾን ተጠመቀ። ይህም በአሜሪካ ታሪክ ፕሬዘዳንት ከሆነ በኋላ
ጥምቀተ ክርስትና በመጠመቅ የመጀመሪያ ሰው ነው።

ከ1950 ጀምሮ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በመኾኑ “አሜሪካ የዓለም
ታላቅ ሕዝብ ነው” እያለ በሙሉ ልብነት ይመራ ነበር ። በእርግጥም
ከላይ እንደተገለጸው ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ አሜ
ሪካ ባገኘችው የመሣሪያ ንግድ በጣም በልጽጋ ሕዝቦቿም ከሚገባው
በላይ ሀብታሞችና ደስተኞች የኾኑበት ዘመን ነበር ። እያንዳንዱ አሜ
ሪካዊ የራሱ የኾነ ቤትና መኪና የተሳካ ኑሮ የማግኘት ዕድል ገጥሞት
ነበር።

[172] Materialistic Spirit
[173] Chronicle of the 20th Century. p. 389

ፕሬዚዳንት ድዋይት አይሰንሀወር ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት የኮርያ ጦርነት ሐምሌ 27 ቀን 1953 እንዲቆም አድርጓል።



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለአቢሲኒያ ባፕቲስት
ቤተ ክርስቲያን የመጸር መስቀል ባበረከቱበት ወቅት።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ በግንቦት 25 ቀን 1954 በአሜሪካ ጉብኝታቸው ጊዜ በዚሁ በፕሬዚዳንት ድዋይት አይሰንሀወር የክብር አቀባበል ተደርጎላቸዋል ። በዋይት ሀውስ የአሜሪካና የኢትዮጵያ ወዳጅነትና ትብብርን በተመለከተ ንግግር አድርገዋል።

ፕሬዚዳንት ድዋይት አይሰንሀወር እና ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከተገናኙ በኋላ ግንቦት 27 ቀን 1954 ወደ ኒው ዮርክ ከተማ ሀርለም በምትባለው ቀበሌ በመኼድ ለአቢሲኒያ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን የመጸር መስቀል ስጦታ አበርክተዋል። ይህ የጥቁሮች ቤተ ክርስቲያን የተጀመረው ቀደም ሲል እንደተገለጸው በ1808 ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ኒው ዮርክ በደረሱበት ጊዜ መኾኑም ይነገራል። ይህ ቤተክርስቲያን በአኹኑ ጊዜ (በ2008) ኹለት መቶ ዓመቱን አክብሯል ።

ወደ ቀደመው ነገር እንመለስና ፕሬዚዳንት ድዋይት አይሰንሀወር የሚመራት አሜሪካ በ1957 ድንገት ያልታሰበ ነገር አስደንገጣቸው። ይህም ሶቭዬት ኅብረት ወደጠፈር ተመነጠቀች የሚለው ዜና መሰማቱ ነው። በምድር ላይ ታላቅ እና ኃይለኛ የተጠናከርኩ ነኝ የሚለው የአሜሪካ



መንግሥት ፣ በወታደራዊ ኃይሉ የሚመካ ፣ አቶሚክ ቦምብ አለኝ የሚል ባይታሰብ ድንገት ሌላ አቶሚክ ያለው የሶቭዬት ኅብረት ጠፈር ላይ መገኘት አስደነገጠ። በዓለም ያሉ አገሮች ራዲዮናቸው ዜናውን አስተጋቡት ። ስፑትንኪ አንደኛ የተባለችው ሳተላይቷ ሰው ይዛ ወደ ጠፈር መጠቀች ተብሎ ተነገረ ። ይህ ወቅትና ሰዐት የቀዝቃዛው ጦርነት በይበልጥ የተቀጣጠለበት ጊዜ ነበር።

ሶቭዬት ኅብረት የአሜሪካ ዋና ጠላት ኾነች ። በኹለቱም አቅጣጫ ወታደሮቻቸው በተጠንቀቅ ለመዋጋት ተዘጋጁ ። በዓለም በየትኛውም አቅጣጫ መፋጠጥ ጀመሩ ። የኮሚኒዝም ሥርዓትና የካፒታሊዝም ሥርዓት በሚል ዓለም ለኹለት ተከፈለ ። በተዘዋዋሪ መሣሪያዎቻቸውን እየሸጡና እየሰጡ የኃያልነትን ቦታ ለመያዝ መዋጋት ጀመሩ። ቀዝቃዛው ጦርነት በመሣሪያና በወታደሮቻቸው ብቻ ሳይኾን በቴክኖሎጂና ዐዲስ ሐሳብ በማፍለቅ ጭምር ከፍተኛ ወድድር ነበረበት
በኹለቱም ወገን የተሳካ የሳይንስ ግኝትና የቴክኖሎጂ ውጤት ካረጋገጡ ለፖለቲካቸው የተሻለ ይኾን ነበር ።

ሶቭዬት ኅብረት በአንድ ወቅት ትንሽ የምታንጸባርቅ የብር ሳተላይት ከካዛክስታን ሪፑብሊክ ባመጠቀች ጊዜ ዓለም በሙሉ ሶቭዬት ኅብረት (ራስያ) ዐዲስ ሐሳብ በማፍለቅ ተወዳዳሪ አይገኝላትም በማለት አደነቀ። በአሜሪካ ሻይም ማንዣበብ ጀመረች ። አሜሪካውያን በዚህ ነገር ተጨነቁ። ሶቭዬት ኅብረት በጠፈር ላይ ሳተላይቷን መስቀመጥ ከቻለች ስንበት ብላ አንድ ቀን ምን ታደርገን ይኾን የሚል ፍርሀቻ አደረባቸው። በፍጥነት ምናልባት ቦምብ በሕዝቦቻችን ላይ ልትጥልብን ትችላለች የሚልስጋት አደረባቸው ። ጋዜጦች ወዲያውኑ ዐዲሱን አደገኛ የጠፈር ጦርነት ወሬ (ፕሮፓጋንዳ) መንዛት ጀመሩ ብዙ አሜሪካውያንም አመኑ።

ፕሬዚዳንት ድዋይት አይሰንሀወር ጥር 7 ቀን 1958 የመንግሥት ታላቅ የቴክኖሎጂ ሥራን የሚቆጣጠር ድርጅት አዋቀረ ። ዐዲስ ሐሳብ የሚያፈልቁትን ምሁራን ወንዶችንና ሴቶችን አሰባሰበ ። ሳይንቲስቶች በሽታን መዝራት የሚችል ቦንብ መሥራት ጀመሩ ። ኢንጂነሮች ወደ ጠፈር ላይ ወጥቶ ጦርነት እንዴት መክፈት እንደሚቻል መንደፍ ጀመሩ። የሰውን ባሕርይ አጥኚዎች (ሳይኮሎጂስቶች ፣ ፊዚዮሎጂስቶች) ስለሰዎች ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ማጥናትና ሰዎችን ማሠልጠን ጀመሩ። ከፍተኛ ገንዘብ ወጭ ተደረገ ። የዛሬዎቹ የኮምፒዩተር ሶፍት ዌር ፈጣሪዎች እና ሀብታሞች እነ ቢል ጌት የተፈጠሩት በዚያን

ጊዜ ለዚሁ የሳተላይት ጥናት ታጭተው በነበረበት ጊዜ ጀምሮ ነው። አሜሪካ አኹን ለደረስንበት የኮምፒዩተር የሥልጣኔ ዕድገት በቃች።

የኮሚኒዝም መነሻው ቀደም ሲል ጀምሮ በአውሮፓ እና በሶቭዬት ኅብረት በክርስቲያኑ ዓለም ሀብታም እና ደሀ በመራራቅ ይኖሩ ነበር ። በዚህም ምክንያት ማርክስ እና ኤንግልስ የሚባሉ የፍልስፍና ሰዎች ተነሱ። ማርክስ ሲሶ መንግሥት የያዙትን ካህናትንና አብያተ ክርስቲያናትን የሚቃወም እንዲሁም ካፒታሊዝም በሶሻሊዝም መተካት አለበት የሚለውን "የኮሚኒስት ማንፌስቶ" ጽሑፉን ጻፈ ፤ ይህ ጽሑፍ የዓለምን ዓመለካከት ለወጠ። ነገር ግን በተግባር ለመተርጎም አስቸጋሪ ኾኖ ኖረ።

ሌኒን (1870–1924) የሶቭዬት ኅብረት ቤተ ክርስቲያን እና የቀድሞውን የንጉሣውያንን አገዛዝ አጠፋ ፤ ንብረትን ኹሉ ለመንግሥት በማድረግ ወረሰ ። በጥቂት ዓመታት ውስጥ ኮሚኒዝም ሥርዓት ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ ወደ 1000 የሚደርሱ ጳጳሳትን እና ቀሳውስትን የሞት ፍርድ ፈርዶ ፈጃቸው፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ገዳሞችን አጠፋ፤ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ንብረቶችን ወረሰ። የንጉሣውያን መንግሥት ይመለስ ብለው የተነሱትን ፓትርያርክ ከሥልጣናቸው ተወግደው እንዲታሰሩ አደረገ። ከኹሉም በላይ የክርስትና እምነትን ጎድቶት የነበረው ከ18 ዓመት በታች ያሉትን ወጣቶች ስለክርስትና እምነት የሚያስተምር እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ ይታሰራል የሚል ሕግ የወጣበት ጊዜ ነበር።

ሌኒን ሲሞት በምትኩ የነገረ መለኮት ተማሪ የነበረው ጆሴፍ እስታሊን (1879 –1953) የሶቭዬት ኅብረት መሪ ኾኖ ሲመረጥ በዚሁ በማርክስ ፅንሰ ሐሳብ (theory) በመመራት እግዚአብሔር የለሽ ኾነ። ካህናትን በጭካኔ በመጨፍጨፍ የኦርቶዶክስን እምነት አመናመነ ። የቤተ ክርስቲያን ሰባኪዎች በፖሊስ ጥበቃ ወይም በድብቅ ስላይ በካሴት እየተቀረጹ ለባለ ሥልጣን አሳልፎ በመስጠት በብዙ ሺ የሚቆጠሩት ካህናት ወደ እስር ቤት ገቡ። የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ያለፉ ብዙዎች ናቸው። በማኅበር መሰብሰብና መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት የተከለከለ ነበር።

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልትጠፋ ደርሳ ነበር ። በዚህ የተነሳ ብዙ የኦርቶዶክስ ካህናት እና ምእመናን ከሶቭዬት ኅብረት በሽሽት ወደ ሰሜን አሜሪካ ገቡ።

ከላይ እንደተገለጸው ሶቭዬት ኅብረት፣ አሜሪካ እና ብሪታንያ ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እንዴት ጀርመንን መቅረብ እንዳለባቸው እና ሌላ ጦር በጀርመን እንዳይቀሰቀስ ፤ እንዲሁ የየራሳቸውን ፍልስፍና የኮሚኒዝምንና የካፒታሊዝንም ሥርዓት ለማስተላለፍ አሰቡ ። ሶቭዬት ኅብረት የምሥራቅ ጀርመንን ያዘች ፤ ብሪታንያ ፣ አሜሪካ እና ፈረንሳይ ምዕራብ ጀርመንን ክፍል ተቆጣጠሩ። በ1949 ምዕራብ ጀርመን ነጻነት ቢትጐናጸፍ ሶቭዬት ኅብረት ምሥራቅ ጀርመንን እና የምሥራቁን የአውሮፓን ክፍል አጠቃላ መቆጣጠር ቻለች። አሜሪካ፣ እንግሊዝ እና ፈረንሳይ የቀሩትን የአውሮፓ አገሮችን በቁጥጥራቸው ለማድረግ ሞከሩ ። የዚህ ለራስ ወዳጅ ለማድረግ መሯሯጣቸው በመካከላቸው መለያየትንና ኹለት ተቃራኒ ክፍሎች እንዲፈጠሩ አደረገ ። ስለዚህ ሶቭዬት ኅብረትና አሜሪካ የዓለም ኃያል መንግሥት ለመኾን የረዥም ጊዜ ትግል አደረጉ።



ከ1945 እስከ 1989 አሜሪካና ሶቭዬት ኅብረት የዓለም ኃያል መንግሥት ለመኾን ብዙ ትግል ፈጥረዋል ። ይኼም “ቀዝቃዛው ጦርነት” በመባል ይታወቃል። ኾኖም ግን ወታደሮቻቸው በቀጥታ በፍጹም ተዋግተው አያውቁም ። ይህ ከላይ እንደ ተገለጸው ቀዝቃዛው ጦርነት የኹለት ኃያላን መንግሥታት ትግል ለብዙ ታዳጊ አገሮች ለሕዝቦች እልቂት ኾኗል። ይህ ቀዝቃዛው ጦርነት ያቆመው የሶቬዬት ኅብረት ፕሬዚዳንት ሚካኤል ጎርባቾቭ እና የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬጋን በ1988 ባደረጉት ስምምነት ነው። ይህ የኮሚኒዝም እና የቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም እና መውደቅ የእግዚአብሔር ምስጢር እንዲሁም ተአምር አለበት ። ኮሚኒዝም ይኹን ካፒታሊዝም የብዙዎች ንጹሐን ወገኖች ደም በከንቱ ያስፈሰሱ ፍልስፍናዎች ናቸው ። ኾኖም ግን አብዛኛው የዓለም ክፍል ከኮሚኒዝም ይልቅ ካፒታሊዝምን ተቀብሎታል።

እነዚህ ኹሉ ጦርነቶች የተቀሰቀሱት በድንበር፣ በሐሳብ አለመግባባት ፣ በብሔረኝነት፣ በመናናቅ፣ በሃይማኖት መጠላላት እና በሌሎችም ነው ።

በዚህ ዘመን የጦርነት መብዛትም አንዱ የምጽአተ ክርስቶስ ምልክት መኾኑ ብዙዎች ይናገሩታል ። በጥቂት ዘመናት ውስጥ በኹሉም አህጉራት ቁጥራቸው የበዛ የእርስ በእርስ ጦርነት ተካኺዷል። ጦርነት በመሣሪያ ብቻም ሳይኾን የመጠላላት ጦርነት ፤ የክፋት ጦርነት ፤ የምቀኝነት ጦርነት ፤ የጥቅም ፍሉጋ ጦርነት (ፕሮፓጋንዳና ውሸት) ፤ የተንኮል ጦርነት ተካኼዷል ። ይህንም የሚያስደርገው የሐሰት አባት የተባለው ዲያብሎስ ነው (ዮሐ. 8፥49)።

# ምዕራፍ ፲
# የ20ኛው ክፍለ ዘመን የጥቁር መብት ተከራካሪዎች

## "ወንድምህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ"

(ማቴ. 22፥39 ፤ ዘሌ. 19፥18)።

በኹለተኛው የዓለም ጦርነት በሒትለር ከተቃጠሉት የማይተናነስ አፍሪካውያን ጥቁሮች ወደ አሜሪካ ለባርነት ሸያጭ በግፍ ከገራቸው ከአፍሪካ ምድር እየተጋዙ ተሰቃይተው የሞቱት ቁጥራቸው በሚሊዮን የሚገመት መኾኑን ቀደም ሲል አይተናል።

"ኹሉም የሰው ዘር እኩል ነው" የሚለው እውነተኛ የነጻነት አዋጅ ቢታወጅም የጥቁር ሰው ዘር በቀለሙ የተነሳ ስቃዩና አድልዎ አልቀረለትም። በአሜሪካ ምድር በነበረው የነጻነት ስብከት ከዚያም የነጻነት አዋጁን እና ሕገ መንግሥቱን በተግባር ለመተርጎም ጥረቱ ለዘመናት አልተቋረጠም ። ይህ ነጻነት በተግባር መገለጽ አለበት የሚሉ ከቀድሞ ጀምሮ ሲከራከሩ እንደነበሩት ኹሉ አኹንም በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የዘር ልዩነቱን ለማስቀም የጥቁር መብት ተከራካሪዎች ብቅ አሉ። በዚህ ክፍለ ዘመን ውስጥ ጥቁሮችን ነጻ ለማውጣት የታገሉ የሰብአዊ መበት ተከራካሪዎች ብዙዎች ነበሩ ። ጥቂቶቹን ለመግለጽ ያህል ፤ ሲዛር ቸአቤዝ (1927-1993) ተሃርጉድ ማርሻል (1908–1993) ፤ ባርባራ ጆርዳን (1936–1996) ፤ ሮጀር ባልድዊን (1884-1981) ፤ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ማልኮልም ኤክስ እና ሌሎችም ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ በጣም ገናና የኾኑት ማርቲል ሉተር ኪንግ እና ማልኮልም ኤክስ ናቸው።

በ1997 በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ ሌሎች ጥቁር ሕዝቦች ሳይጨመሩ አፍሪካን አሜሪካን ብቻ 33.8 ሚሊዮኑ እንደሚኖሩ በጥናት ቀርቧል።[174] በቀድሞ ጊዜ ይኖሩ የነበሩት በአብዛኛው የደቡብ ክፍል ውስጥ የትምባሆ እና የጥጥ እርሻ ላይ ተሰማርተው በባርነት ሲሠሩ ነበር ። ነገር ግን በ1860 ከእርስ በእርስ ጦርነቱ በኋላ በፕሬዘዳንት አብርሃም ሊንከን ሕግ እና የነጻነት አዋጅ በማወጅ ባርነትን እና ዘረኝነትን ለማጥፋት ተሞክሮ ጨርሶ ሳይጠፋ ለአንድ መቶ ዓመት ቆየ።

[174] Jackie Staddon., *p., 29*




የተደራጁት የነጭ ዘረኞች ኩ ክለክስ ክላን ጥላቻቸው ኔግሮን፣ ጃፓናውያንን፣ የሮማ ካቶሊክ፣ የአሜሪካ ኮሚኒስት ፓርቲን፣ አይሁዳውያን እና የውጭ ዜጎችን በማጥፋት አሜሪካ የፕሮቴስታንት አገር ብቻ መኾን አለባት ፤ መመራት ያለባትም በነጭ ፕሮቴስታንት ነው እያሉ በግልጥ ይናገሩ ነበር ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የጀምስ ክሮው (ጂሚ ክሮው) ሕግ በ1950 በይበልጥ ተጠናክሮ እስከ 1960 ድረስ ቀጠለ። ኔግሮ ሲያምጽ ሲያሴር የተገኘ እንደኾነ ያለምንም ርኅራኄ በጅራፍ ይገረፍ ነበር።[175] ማርቆስ ጋርቬይ ጥቁር ወደ አገርህ አፍሪካ ተመለስ ያለውም ለዚህ ነበር።

በደቡቡ የአሜሪካ ክፍል ጥቁሮች በአውቶቡስ ላይ ከበስተኋላ በተለየ ቦታ ይቀመጣሉ እንጂ በነጭ አጠገብ በፍጹም እንዲቀመጡ አይፈቀድላቸውም። በምግብ ቤት (በሬስቶራንት) ለጥቁሩ የተለየ ቦታ ሲኖረው፤ ለነጩ ለየት ያለ የተሻለ ቦታ ይኖረዋል። ጥቁር የበላበትና የጠጣበት ወዲያው ዐይኑ እያየ ይጣላል ። ወይም የሚሰበርም ከኾነ ይሰበራል ። ቤተ ክርስቲያንም የተለየ ቦታ ፤ መቃብሩም የተለየ ቦታ ነው። እንዲኹም በተለያየ ትምህርት ቤት ልጆቻቸውን በመላክ ፤ የተለየ ምግብ ቤት ፤ የተለየ ፊልም ቤት ፤ የተለየ ቲያትር ቤት ፤ የተለየ የአውቶቡስ እና የባቡር የመቀመጫ ቦታ ፤ የተለየ የሕዝብ መጸዳጃ ቦታዎች፤ የተለየ የመጠጥ ውሃ ቧንቧ ቦታዎች የነጭ እና የጥቁር በሚል ተለይተው የኔግሮ ነው የሚል ጽሑፍ ተጽፎ ይለጠፍ በታል። ይህ የቀለም ልዩነት ሰግርጌሽን (SEGREGATION) ይባላል።

ይህን የዘር እና የቀለም ልዩነት የጥቁር ጸሐፊዎች ፤ ታዋቂ ዘፋኞች የመድረክ ቲያትርኞች፤ አርቲስቶች ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አቅራቢዎች ፣ እስፖርተኞች ከነዚህ ውስጥ ዝነኛው የያንኪ ክለብ የቤዝቦል ተጫዋች ጆርዳን ፤ ከጸሐፊዎች ጀምስ ባለድዊን ፤ ቶኒ ሞሪሶን እና ማያ አንጀላ፤ ታዋቂዋ ኦፕራ ዊንፍሬ ሌሎችም... የጥቁር አሜሪካውያን ሕይወት በጽሑፋቸው፣ በዘፈናቸውና በቴሌቪዥን ፕሮግራማቸው የሕዝብን አመለካከት ለውጠዋል ። ከነዚህም ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት የጥቂቶቹን ሥራ እናያለን።

[175] Lutz Norma Jean., *p., 49*



የቀለም ልዩነት (SEGREGATION)

## (፩) ማርቲን ሉተር ኪንግ

በ1950 የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ካህን የነበረ ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ የጥቁሮች ሰብአዊ መብት እንዲከበር ትግል ጀመረ።

ኪንግ ጥር 15 ቀን 1929 በአትላንታ ጆርጂያ ተወለደ። አባቱ ቄስ ነበር ። ቤተሰቦቹ እንደ ብዙኃኑ ጥቁሮች ድሆች አልነበሩም ። ለመኖሪያቸው በቂ ገቢ የነበራቸው መካከለኛ ኑሮ የሚኖሩ ነበሩ። የሚ ኖሩበት ሥፍራ በአትላንታ የተከበረና ጥሩ ሰፈር ውስጥ ነበር ። ሲወ ለድ ስሙ ማይክል ኪንግ ነበር ። በኋላ ግን ዐምስት ዓመት ሲሞላው አባቱ በጀርመን የኢንተርናሽናል ባፕቲስት ኮንፈረንስ ላይ ኼዶ የፕሮቴ ስታንት እምነት በዐራት መቶ ዓመት ውስጥ ያደረገውን እንቅስቃሴ አይቶ የልጁን ስም ማርቲን ሉተር በማለት ቀየረው።[176]

ኪንግ በልጅነቱ ከቤተሰቦቹ ጋር ሲኖር የነጭ ጎረቤቶች ነበራ ቸው ። ኪንግ ትምህርት ሲጀምር ጎረቤት ካለው ከትንሽ የነጭ ልጅ ጋራ ጓደኛው በማድረግ አብሮት ይጫወት ነበር። ትምህርት ቤታቸው

[176] Michael A. Schuman *Martin Luther king, JR. Leader for Civil Rights., p., 13*



የተለያየ በመኾኑ አንድ ቀን ከተምህርት ቤት ሲመለስ ወደ ልጁ ቤት በመኼድ መጫወት ፈለገ። የልጁ እናት ከርሱ ጋራ መጫወት እንደሌ ለበትና እንደማይችል ለነጭ ልጇ አስጠነቀቀች ። ምክንያቱም ኪንግ ጥቁር አገልጋይ የኔግሮ ልጅ ሲኾን የርሷ ልጅ ነጭ በመኾኑ ነው ። ኪንግ በዚያን ዕለት በቤቱ እንደ ደረሰ አብሮ ባለመጫወቱ አለቀሰ ። ለእናቱም ነገራት፤ እናቱም አጽናናችው። በትምህርቱም እየገፋ ኼዶ ከፍተኛ ደረጃ ሲደርስ ብዙዎች ሰዎች ባሉበት ቦታና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ንግግር ያደርግ ነበር። በትምህርት ቤት ደግሞ የደቡብን ግዛት የዘር ልዩነት ለማስወገድ እንደሚፈልግ ይናገር ነበር።

ኪንግ በ14 ዓመቱ ከትምህርት ቤቱ በንግግር ውድድር አሸንፎ ዋሽንግተን በመኼድ ሽልማት አግኝቷል። ነገር ግን ወደ አትላንታ ሲመለስ በአውቶቡስ ላይ ኾኖ አውቶቡሱ ሙሉ በለነበረ የአውቶቡስ ሹፌር ኪንግ ከተቀመጠበት መቀመጫ እንዲነሳና ለነጩ ጌታ እንዲ ለቅ ጠየቀው፤ እሱም ደክሞት ስለ ነበረ አልለቅም ለማለት ሞከረ ፤ ሹፌሩም በጣም ተቆጣው ፤ ሰደበውም ኪንግ ችግር እንዳይደርስበት በመፍራት ፥ ይልቁንም በአስተማሪው ላይ ችግር እንዳይፈጠር ሲል በመስጋት ተነሳለት ፤ በጣምም ተበሳጨ። ነገሮች የሚሻሻሉት የጥቁር ሕዝቦች ለመብታቸው ሲታገሉ ብቻ ነው የሚል እምነት አደረበት።

ኪንግ 15 ዓመት ሲሞላው በአትላንታ ሞሪ ሀውስ ኮሌጅ ገባ። በትምህርቱ በጣም ጎበዝ ነበር። አባቱ ቄስ ስለነበረ ይመኝለት የነበረው እንደ እሱ ቄስ እንዲኾን ነበር። ነገር ግን ኪንግ በመጀመሪያ የቅስና ሐሳብ አልነበረውም በኋላ ግን ቀስ እያለ እያደር ሐሳቡን በመለወጥ እንደ አባቱ ቄስ እና አስተማሪ መኾንን መረጠ።

ኪንግ በ18 ዓመቱ በባፕቲስት በአባቱ ኢብኔዜር ቤተ ክርስቲ ያን የዲቁና ክህነት ተሰጥቶት ረዳት ሰባኪ ኾነ ። ለቅስና ትምህርት ወደ ፔንስሊቫንያ በስሜኑ ክፍል ኼዶ በዚያም በኮሌጁ ውስጥ ብዙ የነጮች ልጆች ይማሩበት በነበረው ምንም ችግር ሳይኖርበት እየተማረ ብዙ ጓደኞችን አፈራ። በዚህ ጊዜ ጥቁርና ነጭ ሕዝቦች በተፈጥሮ ልዩነት የለንም ፤ ጥላቻ መኖር የለበትም የሚለው እምነት ይበልጥ አደረበት ። የተመኘውም ምኞት በደቡብ ያሉ ነጭ ሕዝቦች ይህንን እንዴት ማየት እንደሚችሉና አእምሯቸው እንዲለወጥ ምንድን ነው ማድረግ ያለብን? የሚል ሐሳብ አደረበት።

## (፱) ኪንግ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘው ትምህርት

> ዓይን ስለ ዓይን፣ ጥርስ ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ ክፉውን አትቃወሙ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ኹሉ ኹለተኛውን ደግሞ አዙርለት (ማቴ. 5፥38-40 ፤ ሉቃ. 6፥29 ፤ ዮሐ. 18፥23)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ የተናገረውን ክፉን በክፉ አትቃወም። የሚለውን መመሪያ ኪንግ በሥራ ላይ ለማዋል ተነሳ ።

ይህን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መመሪያ የህንድ መሪ ጋንዲ በሥራ ላይ እንዴት እንዳዋለው ለመስማት ዕድል አጋጠመው። የመጨረሻው የኮሌጅ ዓመት ሲፈጸም ፣ የሀዋርድ ዩንቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሞርዴካይ ጆንሰን ስለ ህንድ መሪው ማህተመ ጋንዲ በጥቁሮች ኮሌጅ በዋሺንግተን ዲ. ሲ. አንድ ቀን አሑድ ንግግር እንደሚያደርግ ሰማ ። በቦታውም በመኼድ ጋንዲና ተከታዮቹ በብሪታንያ የቅኝ አገዛዝ እንዴት ይሰቃዩ እንደ ነበረና እንዴት በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞ አሰምተው ነጻነታቸውን እንዳገኙ በሰማ ጊዜ ማርቲን በጋንዲ ዘዴ ሳይደነቅ አልቀረም። ህንዶች በጠመንጃ እንዲሁም በማናቸውም የጦር መሣሪያ ሳይጠቀሙ በሰላማዊ ሰልፍ ፤ በርሃብ አድማ ከብሪታንያ ቅኝ አገዛዝ በመውጣት ድልን ያደረጉ መኾናቸውን ፤ ከጥላቻ ይልቅ ፍቅር ታላቅ ኃይል እንዳለው በሚገባ ተረዳ።

ኪንግ በቦስተን ዩንቨርሲቲ ጥናቱን ቀጠለ። የፍልስፍና ዶክትሬቱን በዚያው ዩንቨርሲቲ አጠናቀቀ ። ቀደም ሲል ግን ባችለር ኦፍ ዲቪኒቲ (ነገረ መለኮት) ዲግሪ። በፔንሲልቫንያ ዩንቨርሲቲ እንዲኹም የኅብረተ ሰብ ጥናት (ሶሲዮሎጂ) ከአትላንታ ሞሬ ሀውስ ቢ.ኤ. አግኝቷል።[177] ከተወለደበትና ካደገበት ቦታ እርቆ በሰሜን በመኖሩም ብቸኝነት እንዲሰማው አደረገው። ጥቂት ጓደኞቹ ከደቡብ ክፍል ተወላጅ የኾነች ኮሬታ ስኮት የምትባል ወጣት አስተዋወቁት ። ከወጣቷ ጋራ ፍቅር ያዘው ። በ1953 ተጋቡ፤ ወዲያው ልጅ ወለዱ። ኮሬታና ኪንግ በአንድ ላይ ወደደቡብ ተመልሰው በደቡብ ያለውን የዘር ልዩነትን መታገል ጀመሩ። በ1954 ኪንግ በደቡብ ሞንትጎሞሪ በአላባማ የአንድ ቤተ ክርስቲያን ቄስ ኾኖ ማገልገል ጀመረ።

[177] Coretta Scott King *The words of Martin Luther king, Jr., p., 7*



## (፲) ኪንግ እና ሮዛ ፓርከር

በአውቶቡስ ተሳፋሪ የመቀመጫ ወንበር ማንኛዋም ሴት ወይም ወንድ የነጭ ዘር የኾነ ሰው ሲመጣ ወንበር ይለቃል ፤ ወይም ጥቁር የተለየ ቦታ ይቀመጣል፤ ሽማግሌ፣ አሮጊት፣ ወጣት ፣ ጎልማሳ በማንኛውም ዕድሜ ያለ ጥቁር (ኔግሮ) በመነሳት ወንበር በመልቀቅ ነጭን ማስተናገድ አለበት። እንዲያውም ለነጭ ሰው በተመደበ ቦታ ላይ መቀመጥ ክልክል ነው ። ባንዳንዱ ወንበር ሰው እንኳን ባይኖር ለጥቁር እንዲቀመጥ አይፈቀድለትም።

በጥቁሮች ኅብረተሰብ በጣም የምትከበረው ሮዛ ፓርከር የምትባል ጥቁር ሴት ነበረች። የምትሠራው በሞንቶጎሞሪ ከተማ ባለው የታወቀ ሱቅ ውስጥ ነበር። ታኅሣሥ 1 ቀን 1955 ከምትሠራው የሥራ ቦታ ጨርሳ እንደተለመደው በክሊቭ ላንድ አውራ ጎዳና (አቨንዩ) ወደ ቤቷ ለመመለስ አውቶቡስ ጠብቃ ተሳፈረች ። በጣም ስለደከማት ከበስተኋላ ባለው በፊት መስመር ለጥቁር ባልተፈቀደው ወንበር ከሷዋ ጋራ ሦስት ጥቁሮች ተቀመጡ ። ይህ ቦታ ለነጮች ተብሎ የፊቱ ሲሞላ በመጠባበቂያነት የተያዘ ቦታ ነው ፤ በሕግም የተደነገገ ነው።

መጀመሪያ ብዙ ሰው የሌለው አውቶቡስ ቀስ እያለ ከያውቶቡስ ማቆሚያ እየተጨመሩ በመብዛታቸው ሞላ። ትርፍ ወንበር ታጣ፤ ነጭ ሰዎች ቆሙ። ሹፌሩም አውቶቡሱን አቁሞ ለነጮቹ ልቀቁ አለ፤ ሦስቱ ጥቁሮች ለቀቁ ፤ ሮዛ ግን አለቅም አለች ፤ ሹፌሩ እንድትለቅ ጠየቃት፤ ደጋግሞ ቢጠይቃትም ደክሟት ስለነበረ አሻፈረኝ ብላ ባለመልቀቋ አውቶቡስ ነጂውን አስቆጣው። ያውቶቡስ ነጂው አውቶቡሱን አቁሞ ፖሊስ ጠራ ። ፖሊስ መጣ ፤ ሮዛንም ወስደው ከከተማው እስር ቤት ከተቷት ። በመጨረሻም ወንጀለኛ ኾና ተገኘች፤ ጓደኛዋን ወይዘሮ ኢ.ዲ. ኒክሰንን ከእስር ቤቱ የፍርድ ቦታ ዋስ ኾና እንድትፈርምላትና እንድትለቀቅ አስጠራቻት ። ሮዛ የከተማውን የአውቶቡስ የመቀመጫ ሕግ በመጣሷ $14 ዶላር እንድትቀጣ ተወሰነባት ።

ሮዛ ይህን ያውቶቡስ የመቀመጫውን ሕግ ስትጥስ የ42 ዓመት ዕድሜ ነበረች ። ዋስ በመኾን ያስፈታቻት ጓደኛዋ ወይዘሮ ኢ.ዲ. ኒክሰን በማግሥቱ ወደ ኪንግና ባለቤቱ ኮሬታ ዘንድ በመኼድ ስለደረሰባቸው አሳዛኝ ጉዳይ ነገረቻቸው። የአውቶቡስ መሳፈር ማቆም አድማ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ተስማምተው ተለያዩ፤ ይህም ዐመፅ ቦይኮት

(Boycott) በመባል ይታወቃል።[178] በሞንትጎሞሪ የሚኖሩ ጥቁሮች የሮ መታሰር ወሬው ተዳረሳቸው ፤ በጣም አስቆጣቸው ፤ ሮዛና ባለቤቷ ከሥራ ተባረሩ። በነጮች በየጊዜው ማስፈራሪያ ይደርሳቸው ነበር።

የጥቁር መሪዎችና ካህኑ ኪንግ ይህን በአውቶቡስ ውስጥ የሚደረገውን የነጭና የጥቁር የቦታ ልዩነት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመነጋገር ዋና የጥቁር መሪዎች ወደ 40 የሚደርሱ ለመሰብሰብ ተጠራሩ ። በየቦታው የሚኖሩ በኪንግ ቤተ ክርስቲያን ዲክስተር አውራ ጎዳና (አሸንዩ) በሚባለው የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ አደረጉ። ኪንግን የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አድርገው መረጡት። ማኅበራቸውን ሞንቶጎሞሪን የሚያሻሽል ማኅበር (MIA) ብለው ሰየሙት ።

ኪንግ የሰጣቸው ሐሳብ በሞንቶጎሞሪ የሚኖሩ አውቶቡስ ውስጥ የሚሠሩና የሚጓጓዙ ጥቁሮች በሙሉ ይህንን የአውቶቡስ መሳፈር ያቆሙ እንደ ኾነ፤ በአውቶቡሱ ውስጥ የሚደረገው የዘር ልዩነት ይቆማል በሚል ተወሰነ። ስብሰባው ከተፈጸመ በኋላ ኪንግ ተጨነቀ። ዋናው ምክንያትም ብዙ ጥቁሮች የግል መኪና የላቸውም እንዴትስ ወደ ሥራቸው ይኼዳሉ ? ይህ የአውቶቡስ መሳፈር ማቆም አድማ ይሳካ ይኾን አይኾን ? በሚል ሌሊቱን ኹሉ እንቅልፍ ሳይወስደው በሐሳብ አደረ።

በማግሥቱ ታኅሣሥ 5 ቀን 1955 ኪንግንና ሚስቱ ኮሪታ በጠዋት ተነስተው በመስኮት ማየት ጀመሩ። በቤታቸው ፊት ለፊት የአውቶብስ ማቆሚያ ስለነበረ የመጀመሪያው አውቶቡስ ሲመጣ ምን ያኽል ሰው በውስጡ ተሳፍሮ እንደኾነ ለማወቅ ይጠብቁ ጀመር ። የመጀመሪያው አውቶቡስ ሲመጣ ባዶውን ኾኖ መጣ። ኹለተኛውም ሲመጣ እንደዚሁ ባዶውን መጣ። በሞንቶጎሞሪ የሚንቀሳቀሱት አውቶቡሶች በሙሉ ባዶ ነበሩ። ጥቁሮች የሚንቀሳቀሱት እና ወደ ሥራም የሚኼዱት በእግራቸው ኾነ ። መኪና ያላቸው የሌላቸውን በመርዳት እየተረዳዱ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ወደ ትምህርት ቤት አብረው

---

[178] Coretta Scott King., *p.,8*
በኋላ ዘመን ሮዛ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች እናት (the “mother of the Civil Rights Movement”) የሚል ቅጽል ስም ወጣላት፤ ብዙ የክብር ሽልማት አገኘች ። በ1999 ፕሬዚዳንት ክሊንተን ከፍተኛውን የሕዝቦች የክብር የወርቅ ሜዳልያ ሸለማት ። ሮዛ ብዙ ዓመታት ኖራ በ92 ዓመቷ ሰኞ ጥቅምት 24 ቀን 2005 ዐረፈች።



ይኼዱ ነበር ። ይህ አድማ ለአንድ ቀን የተባለው፥ ለአንድ ዓመት ያኽል ቀጠለ።

የከተማዋ የነጭ መሪ ዋና የአድማ መሪዎቹን እየመረጠ በየምክንያቱ ለማሰር ወሰነ ። አንድ ቀን ኪንግ በመኪናው ሦስት ሰዎች ጭኖ እየነዳ ሲኼድ ከፊቱ የፖሊስ ሞተር ብስክሌት መጥቶ አስቆመው። ምንም ጥፋት አልነበረበትም። ነገር ግን ተሳፋሪዎቹን አስወርዶ የ25 ማይልስ በሰዐት መነዳት የሚገባውን ክልል አንተ በ30 ነድተሀል ብሎ አስቆሙት ። በከተማዋ እስር ቤት ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጥቁሮች ጋር ንጽሕና በሌለው ጨለማ ቤት እንዲታሰር ተደረገ። መታሠሩ ወዲያውኑ በየቦታው ተሰማ። እስር ቤቱ በብዙ ጥቁሮች በአንድ ጊዜ ተከበበ ። ወዲያው አሻራ ሰጥቶ እንዲፈታ አደረጉት ። ይህ ሲኾን ኪንግ ዕድሜው 26 ዓመት ነበር።

የአውቶቡሱ ኩባንያ ብዙ ገንዘብ ከሰረ፤ ፖሊሲውን ሊለውጥ አልፈለገም ። የአድማዎቹን መሪዎች ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት ይዞ ቀረበ። በታኅሣሥ 20 ቀን 1956 ፍርድ ተሰጠ። ፍርዱም በአውቶቡስ ውስጥ የሚደረገው አድልዎና የዘር ልዩነት የአሜሪካንን ሕግ የሚቃወም ነው የሚል ነው ፤ በዚህ የተነሳ የጥቁሮች መሪዎች አሸነፉ፤ የሞንቶጎሞሪ የአውቶቡስ ያለመሳፈር የእምቢታ አድማው ዝነኛ አደረጋቸው ። ወዲያው ቢታይምስ ጋዜጣ ላይ የኪንግ ዝነኛነቱ ተጻፈ ። ጥቂት ነጮችም በኪንግ አሳዳሚነት ተበሳጩ ። አደገኛ ሰው ነው ብለው ስለአመኑ ጥር 30 ቀን 1956 ምሽት ላይ በቤቱ ደጃፍ ቦንብ አፈነዱ ፤ ነገር ግን ማንም አልተጎዳም ። በሌላ ጊዜ ደግሞ አእምሮዋን የተነካች ወፈፍ የሚያደርጋት ሴት በተጨናነቀ ሰው መካከል አልፋ በስለት ወጋችው። ጉዳቱ ጥቂት ቢኾንም ታክሞ ዳነ ። በዚህ ጊዜ ለጥቁሮች መብት ብዙ መናገሩን ከቀጠለ ሞትም እንደማይቀር ለት ቱረዳ ። ስለዚህም የኹል ጊዜ የአእምሮ ጥያቄው

ማን ቤተሰቤን ይመለከትልኛል ?
ማንስ ይህንን የጀመርኩትን ሥራ ይፈጽማል?
ገና ብዙ የምንሠራው ሥራ አለ ይል ነበር።

ኪንግ የሞንቶጎመሪው እንቅስቃሴ የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው እንደማይኾን ያውቃል፤ ምክንያቱም በደቡብ ብዙ ነጻነትን ለማግኘት የሚታገሉበት ነገር አለ ። ስለዚህ ለማሸነፍ ለመብታቸው ራሳቸውን በደንብ ማደራጀትና መታገል እንዳለባቸው ብዙዎቹ ጥቁሮች ያምናሉ። ኪንግ ከሞንቶጎሞሪው የአውቶቡስ አድማ በኋላ ዝነኛ ኾነ። በደቡብ አፍሪካና ጋና፥ በእንግድነት ተጋበዘ ። በዚያን ጊዜ አብዛኛው

የአፍሪካ ምድር በአውሮፓውያን በቅኝ ግዛት ቁጥጥር ሥር የነበሩት ቀስ እያሉ ነጻ እየወጡ ነበር ። ኢትዮጵያ ብቻ በቅኝ ግዛት ሳትያዝ ነጻነቷን አስከብራ የኖሩች አገር ስትኾን ላይቤሪያ አሜሪካኖች ስለነበሩባት ነጻ ትኹን አትኹን የሚያጠያይቅ ኾኖ ይኖራል ። ኪንግ በጉዞ ወቅት የናይጄሪያን ሕዝብ እንዲሁ ጎበኘ። በዚህ በጉብኝቱ ጊዜ መጽሐፍ ለመጻፍ ዕድል ገጠመው።

በ1957 በመቶዎች የሚቆጠሩ የደቡብ ጥቁሮች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአንድ ላይ ተሰብስበው ያላቸውን ሐሳብ በጉባኤ ተነጋገሩ። ኪንግ ጥቁር ሕዝቦች በጋራ በመሥራት ፣ በመተባበር ለትክክለኛ መብታቸው መታገል አለባቸው ሲል በስብሰባው ተናገረ፤

በአንድነት በመነሳት እንቆማለን፤ ከፍፍላችን ግን ይጥለናል።

ይል ነበር።

ይህም የማርቲን ምርጥ ንግግር ነው ። ይህን በመከተል

የደቡብ ክርስቲያን የመሪዎች ጉባኤ (SCLC) በማለት የአንድነት የድርጅት ስም ሰየሙ ። ኪንግም የጉባኤው መሪ ኾነ ። ዓላማውም የደቡብ ጥቁሮች ለመብታቸው መታገል አለባቸው የሚል ነው። ሐሳቡን በመጽሐፉ (STRIDE TOWARD FREEDOM) በማለት ገለጸ። በመጽሐፉም የህንድ መሪ የነበረው የጋንዲን ትምህርት ያለ በቀል እንዴት ከብሪታንያ የቅኝ አገዛዝ ነጻ እንደወጡ የሚገልጽ ነው።

ይህም ለጥቁሮች መብት ነጻነት ለማግኘት ያለቁጡነት ስሜት በሰላማዊ መንገድ መታገል እንዳለባቸው ቀደም ሲልም በሞንቶጎሞሪ ያለቁጠኝነት ያለበቀል በሰላማዊ መንገድ ታግለው የአውቶቡስ ላይ ዘረኝነት እንዲወገድ ነጻነት እንዳገኙ ትምህርት ኾኖ አግኝተውታል። ስለዚህ በቀላሉ ያለአግባብ ያልኾነውን ነገር ኹሉ እምቢ ማለት እንደሚገባ ተረዱ።

ቤተ ክርስቲያን የጥቁሮቹ ማኅበራዊ ኑሮ መገናኛ ማዕከላዊ ቦታ ነበረች ፤ በ1962 የቅድስት ማርያም ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያንን ሕንጻ በጆርጂያ ግዛት ዘረኞች ኩ ክላክስ ክላን በጥላቻ አቃጠሏት።[179]

በዚህን ጊዜ ነገሮች ኹሉ በይብልጥ መለወጥ ጀመሩ ። የዘር ልዩነት እንዳይኖር የጥቁሮች መብት እንዲከበር ዐዲስ ሕግ ወጣ ። ይህ ባለመፈጸሙ የተወሰኑ የጥቁር ቡድኖች እያመፁ አድማ በማደም ኃይል በመጠቀም የአሜሪካንን ሕግ መጣስ ጀመሩ። ነገር ግን ኪንግ ይህን በቁጣና አደጋ በማድረስ የሚደረገውን ዐመፅ አልወደደውም ።

[179] Lutz Norma Jean., *p., 63*



በዚህ መንገድ ሳይኾን በሰላማዊ መንገድ መብትን ማስከበር እንደሚቻል አማከረ።

ጠላትህን አፍቅር ማለት ከባድ መኾኑን አውቃለሁ፤ ነገር ግን ፍቅር ምን እንደኾነ ለዚህ ነጭ ሰው አስተምረው ። ወይም ይህን ነጭ ሰው ከታመመበት ከዘረኝነት በሽታ አድነው፤ እያለ ይናገር ነበር ።

የመጀመሪያው የአድማ ዘዴው ጥቁሩ ሕዝብ አቶቡስ ባለመሳፈር ኩባንያ ገንዘብ ሳያገኝ እንዲከስር፤ እንዲሁ ከፍተኛ ልዩነት የሚደረግበት ቦታ ምግብ ቤቶችም ኼዶ ባለመመገብ ከስረት እንዲመጣ በማድረግ አድማው ቢቀጥል ለውጥ እንደሚኖር ኪንግ አመነ። የደቡብ ነጮች ለጥቁሮች የሚወጣውን የመብት ሕግ መቃወም ጀመሩ፤ በግልጽ ትግል ተጀመረ ፤ በአላባማ በኪንግ ዐዲስ ቤትና ቤተሰብ ላይ አስፈሪ ኾነ። ነጮችም አላባማ የነጭ አገር ነች፤ የሚል መፈክር ይዘው ነበር።[180]

በደቡብ ብዙ መለወጥ የሚገባቸው ነገሮች አሉ። በትምህርት ቤት ያለው የዘር አድልዎ ፤ የነጭ ልጆች የሚኼዱት በነጮች ትምህርት ቤት ሲኾን ጥቁሮች ልጆች የሚኼዱት በጥቁሮች ትምህርት ቤት ብቻ ነበር ። ደግሞ ብዙ የጥቁሮች ልጆች ከነጮቹ ልጆች በችሎታ ቢበልጡም አብዛኛው ከመንግሥት ካዝና የሚወጣው የተማሪዎች መርጃ ገንዘብ ከጥቁሩ የበለጠ ለነጭ ልጆች ተማሪዎች ነበር።

### (፬) "መቀመጥ" (Sit-ins)

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በደቡብ የሚኖሩ ጥቁሮች በአንድ አይነት ምግብ ቤት ከነጮች ጋራ ተቀምጠው አይበሉም፣ አይጠጡም ፣ የቧምቧ ውሃ መጠጫና መታጠቢያው የተለየ ነው፤ ሽንት ቤቱም የተለየ ነው። ስለዚህ ይህን ዘረኝነት ለማስወገድ ጥቁር ተማሪዎች በምግብ ቤቶች (በሬስቶራንት) "ሲት ኢን" በማለት ለረዥም ጊዜ ደብተራቸውን እና መጽሐፎቻቸውን እያነበቡ ይቀመጡ ጀመር ።

"ሲት ኢን" በአሜሪካ ግዛት እየተስፋፋ እየገነነ ታዋቂ ኾነ ። ተማሪዎችም እየተጠራሩ መቀመጡን ቀጠሉ።[181] 1 ቀን የካቲት 1960 ዐራት ጥቁር ተማሪዎች በግሪንስ ቦሮ ኖርዝ ካሮላይና አንድ መግብ ቤት ኼደው የነጮች መመገቢያው ቦታ ተቀምጠው ምሳ እንዲሰጣ

[180] Alan C. McLean *Martin Luther King Oxford University Press., p., 9*

[181] Alan C. McLean Martin Luther *King Oxford University Press., p., 14*

ቸው ጠየቁ። አስተናጋጆቹም ለነጭ ብቻ የተለየ ቦታ ስለነበረ እንደማ ይሰጣቸው ነገሯቸው ። በዚህ የተነሳ ተማሪዎቹ ከቦታው አንኼድም ብለው ቁጭ አሉ ። ኹሉም ተማሪዎች እነሱን አይተው "ሲት ኢን" እየተባለ ለረዥም ሰዓት ደብተራቸውን አውጥተው እያነበቡ መቀመጥ ጀመሩ ። የግሪንስ ቦሮ ተማሪዎች በፖሊስ ተወስደው ታሠሩ ። ነገር ግን "ሲት ኢን" ሊያቆሙት አልቻሉም። ተማሪዎች እየገቡ በምግብ ቤቶች ወንበር ይዘው ደብተራቸውን ማንበብ ቀጠሉ። ይህም በሞላው በደቡብ ግዛት ታወቀ። በማንኛውም በነጮች ምግብ ቤት "ሲት ኢን" ቀጠለ። በሰሜን የሚኖሩ ነጮች የጥቁሮች ደጋፊ ተማሪዎች ወደ ደቡብ በመኼድ "ሲት ኢን" ላይ ተካፍለዋል።

በዚሁ "ሲት ኢን" በ1960 ኪንግ በአትላንታ ምግብ ቤት ኼዶ ተባብሮ ከተማሪዎች ጋር ተቀምጧል። በዚህም የተነሳ ተይዞ እስር ቤት ገብቷል ። ቤተሰቦቹና ጓደኞቹ በጣም ይሰጉለት ነበር ። በእስር ቤት ያለው ሕይወቱ በአደጋ ላይ እንደሚኾንና እሱን ለማጥፋት በዙ ጠላ ቶች እንደነበሩት አንዳንዶችም ለመግደል እንደሚፈልጉ ያውቁ ነበር። በ1960 በደቡብ በእስር ቤት ያሉትን ጥቁሮች ለመግደል አስቸጋሪ አል ነበረም ። ሚስቱ ኮሬታ የሴነተር አባል ወደኾነው ጆን ኤፍ ኬኔዲ እና ወንድሙን ጄኔራል ሮበርት ኬኔዲን ባለቤቷ ኪንግ ከሥር ቤት እን ዲፈታ ለዚህም እንዲረዷት ጠየቀች፤ ኬኔዲ ለፍርድ ቤቱ ዳኛ ኪንግ በነጻ እንዲለቀቅ ተጠየቀ። ዳኛውም ተስማማ፤ ኪንግ በነጻ ተለቀቀ።

ኬኔዲ ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት ለመኾን ከተቀናቃኙ ከኒክሰን ጋር ለውድድር ሲቀርብ ኪንግን ከእስራት ማስለቀቁ ውለታ ተቆጥሮለት ብዙ ጥቁሮች የመምረጥ ዕድል የነበራቸው ሰሜኖች ለፕሬዚዳንትነት መርጠውታል ። ኪንግ ከተፈታ ከወር በኋላ ኅዳር 1960 ጆን ኤፍ ኬኔዲ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ኾኖ ተመረጠ ። አገሪቷም በተስፋ ተሞ ላች ። ይህ ዐዲስ ወጣት ፕሬዚዳንት አገሪቷን ለማሳደግ ፤ ለውጥ ለማምጣት፤ ቃል ኪዳን ገባ ። ወደ ዋይት ሀውስ ሲገባ ለጥቁሮች መብት ለመከራከር ሦስት ነጥቦችን ይዞ ገባ።

1ኛ) ለጥቁሮች ሰብአዊ መብት መታገል።

2ኛ) ጥቁሮች የመንግሥት አስተዳደር ቦታ እንዲይዙ ማድረግ

3ኛ) ዋይት ሀውስና ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰብአዊ መብት ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ፤ የሚል ነበር።

በርግጥ ለደቡብ ጥቁሮች መጥፎ የነበረው ሕግ ተለወጠላቸውና ያለምን ም አድልዎ በደቡብ ያሉት ጥቁሮች ምርጫ እንዲመርጡ ሕግ ወጣ። ነጻነት እንዲኖራቸው ተደረገ ። ነገር ግን የጥቁሮቹ ነጻ መውጣት




ነጮቹን አላስደሰተም ። በዚህ የተነሳ ጥቁሮች ነጻነትን በወረቀት ላይ ቢያገኙም የነጻነትን ፍሬ ለማጣጣም ከባድ ትግል ከፊታቸው ተደቀነ። የነጻነቱ መንገድ በቀላሉ ሊያጥርና ሊቀጭ አልቻለም።

## (፳) የጥቁር እና የነጭ ትምህርት ቤት

በ1954 ለጥቁሮች የመማር መብት የተለወጠ ሕግ ነበር። ይህ የጀምስ ክሮው ሕግ ተለውጦ ጥቁርና ነጭ ልጆች አብረው በአንድ ትምህርት ቤት መማር አለባቸው የሚል ነው። ይህ የሕግ ለውጥ በደቡብ ክፍል ለመድረስ በሥራ ለመተርጎም በጣም ዘገየ። የደቡብ ነጮቹም ለዚህ ዐዲስ ሕግ አንታዘዝም በማለት እምቢ አሻፈረን አሉ። አላባማ እና አርካንሳስ የግዛቱ አስተዳደር ጥቁር ተማሪዎች ወደ ነጭ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ገብተው እንዳይማሩ ታገሉ።

በአርካንሳስ በሊትል ሮክ በምትባል ቦታ ነጮች በመንገድ ላይ ታላቅ ብጥብጥ አነሱ። የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ኬኔዲ ብጥብጡን እንዲ ያቆሙ 1,000 ወታደሮችን ላከ ። በየጧቱ ዘጠኝ የጥቁር ልጆች ወደ ሊትል ሮክ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እየኼዱ እንዲማሩ ተፈ ቅዶ ነበር ። እነዚህ ልጆች በነጮቹ እንዳይደበደቡ በየቀኑ ጠዋት ጠዋት በወታደር ተጠብቀውና ታጅበው በተጨናነቀው እና ቁጡ በኾኑ ዘረኛ ነጮች መኻከል ይጓዙ ነበር።




በአላባማ ግንቦት 1961 በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ነጮች በጥቁር ላይ ሸምቀው በላማዊ ሰልፍ ወጥተው ነበር።

## (፮) የበርሚንገሃም ሰላማዊ ሰልፍ

በበግንቦት 2 ቀን 1963 ኪንግ በበርሚንገሃም ፣ በአላባማ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመረ። በርሚንገሃም ለጥቁሮች ከኹሉ በጣም የከፋ ከተማ ነበረ። የክርስቲያን መሪዎች ጉባኤ (SCLC) የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ አስደረጉ ። ነገር ግን የወታደር ፖሊስ አለቃው ቡል ኮኖረ ተቃዋሚዎችንና ሰላማዊ ሰልፉን በዱላ በማስደብደብ ፣ ዉሾች በማስነከሱ፥ የእሳት አደጋ ውሃ በማስረጨት፥ በመቶዎች የሚቆጠሩ የሰላማዊ ሰልፍ ተቃዋሚዎችን ጎድተዋል። ወጣት ልጆችና በአሜሪካ ግዛት ያሉት የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ኹሉ በዚሁ በበርሚንገሃም የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ተገኝተዋል።



በርሚንግሀም እና አላባማ

በመጀመሪያው ቀን ፖሊሶች በጣም ገርሟቸው በመደነቅ ምንም ሳያደርጉ ሰላማዊ ሰልፉን ሳይበትኑ ዋሉ ። በኹለተኛው ቀን ግን በታዘዙት ትእዛዝ መሠረት ኀይለኛ ግፊት ባለው የእሳት አደጋ ውሃ ወንዱንም፣ ሴቱንም፣ ሕፃናቱንም ሳይመርጡ፥ እየገፈታተሯቸው፣ እያንከባለሏቸው ሰልፉን በተኑት ። በዚህን ጊዜ ኪንግ ወደእስር ቤት ተወሰደ ፤ ከሱም ጋር ዐምስት መቶ የሚደርሱ ጥቁር ተማሪዎች ታሰሩ። በመላው አሜሪካ ግዛት የበርሚንገሀም ፖሊሶች ያደረሱትን ጭካኔ በቴሌቪዥን በመታየቱ ሕዝቡን አስደነገጠ።


ፕሬዚዳንት ኬኔዲ ወንድሙ በጉዳዩ እንዲገባበት አደረገ ፤ ኪንግም ተፈታ ። ይህ ኹሉ ግፍ የተፈጸመው ጥቁሮች ከነጮች እኩል መብታችን ይከበርልን ስላሉ ነበር ። በዚህም የተነሳ ድርጊቱ



ትክክል አለመኾኑን የአገሪቱ ሕዝብ ፈረደ ። ይህ ሕገ ወጥ ተግባር መለወጥ እንዳለበት አመኑበት።

## (፯) የዋሽንግተን ዲ.ሲ. ሰላማዊ ሰልፍ

በበጋው ወር ነሐሴ 28 ቀን 1963 የሰብአዊ መብት መሪዎች ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ አዘጋጁ ። ከኹሉም ግዛቶች ተሰባስበው ወደ ዋሺንግተን ዲ.ሲ. ለጥቁር አሜሪካኖች እኩል መብት እንዲኖር ተሰለፉ፤ የተሰለፉትም ከ200,000 ሺ የሚበልጡ ሕዝቦች ናቸው፤ በሰልፉ ላይ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚዘምሩት መዝሙር "WE SHALL OVER CAME SOME DAY" የሚለውን የጥንት የባፕቲስት ቤተክርስቲያን መዝሙር እየዘመሩ ነበር ። ይህ ታዋቂ የኾነና ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ሲዘምሩት የኖረ የጥቁሮች የነጻነታቸው መዝሙር ነው። በቤተ ክርስቲያን ይዘምሩታል ያንድነትና የጥንካሬ መንፈስ ያሳድርባቸዋል።




የዋሽንግተን ዲ.ሲ. ንግግር

በዚህ ቀን በዋሺንግተን ዲ.ሲ. ከፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን የመታሰቢያ ሐውልት ፊት ለፊት በተዘጋጀ የመናገሪያ ቦታ በመቆም ከሰላማዊ ሰልፍ ላይ ተናጋሪዎች አንዱ ኪንግ ነበር።

ኪንግ በዓለም የሚደነቀውን ሕልም አለኝ የሚለውን ንግግሩን አደረገ (I HAVE A DREAM)።[182] ከተናገረው ጥቂቱ እንዲህ የሚል ነበር።

ወደዚህ ከፍተኛ የሕዝቦች ታላቅ ከተማችን የመጣነው ገንዘባችንን ለመቆጣጠር ነው። የሕዝባችን መሪዎች ቀያሾቹ የነበሩት በሚደነቅ ቃላት የነጻነት አዋጁን እና ሕገ መንግሥታችንን በተግባር ለመግለጽ የፈረሙት ፊርማ እያንዳንዱ አሜሪካዊኗ የአገሪቷ ወራሽ የሚያደርግ መስሎን ነበር ።

ይህ የቃል ኪዳን ስምምነት ማስታወሻ ኹሉም የአዳም ዘር አዎ! ጥቁሮችንም እንደ ነጮች የሚመለከት የማይገፈፍ ከአምላክ የተሰጠ የመኖር መብታችን ሕይወት ፣ ነጻነት እና ደስታን የሚደነግግ ተስፋ ሰጪ ስምምነት ኾኖ ሳለ። ዛሬ ግን በአሜሪካ ግልጽ ኾኖ የሚታይና በተለይም ዜጎቿ ጥቁሮችን በተመለከተ ይህን የተላለፈልንን የተቀደሰ ዓላማ ግብ ከማድረስ ይልቅ አሜሪካ ለጥቁር ልጆች የሰጠችው ገንዘብ (ቼክ) መጥፎ እና የተበላሸ ስም (ኔግሮ) ነው።... የተስፋውን ቃል አልጠበቀችም።.......

..... ዛሬ ሕልም አልሜአለኹ ፤ ያም ዐራቱ ትንንሽ ልጆቼ አንድ ቀን በቆዳ ቀለማቸው ይፈረድባቸው እንደነበሩት ሳይኾን በሙያ እና በችሎታቸው የሚገመገሙበት ጊዜ ይመጣል ። የነጻነት ደወል ይደወል! ተውት አትግቱት። በኹሉም ግዛት እና ከተማ ይህ የነጻነት ደወል ይደወል። ይህም በሚኾንበት ጊዜ ኹላችንም የእግዚአብሔር ልጆች መኾን እንችላለን ።

ጥቁር ሰው፣ ነጭ ሰው፣ አይሁዳዊ እና አሕዛብ ፣ ፕሮቴስታንት እና ካቶሊክ በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘን የቀድሞውን የኔግሮ መንፈሳዊ መዝሙር መዘመር እንችላለን። በመጨረሻ ነጻነት ! ነጻነት ! ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው... [183]

በማለት አስደናቂ ንግግሩን ተናገረ፤ በንግግሩ ዓለም ተደነቀ። ሕልሙም የአሜሪካ ሕዝቦች ፤ ጥቁሮች ኾኑ ነጮች እኩል በመኾን በአንድነት በሰላም ይኖራሉ የሚል ነው ። ይህ ንግግሩ ልብን የሚነካ ስለነበረ በኹሉም ቦታ በቴሌቪዥን ሲታይ ሕዝብን በየቤቱ አስለቅሶታል ።

[182] Richard Deats *Martin Luther King, Jr., p., 83*
[183] Richard Deats., *p.*, 83



ከሰላማዊ ሰልፉም በኋላ ፕሬዘዳንት ኬኔዲ የሰላማዊ ሰልፍ መሪዎቹን በዋይት ሀውስ ተቀብሎ አነጋግሯቸዋል ። በርግጥም የኪንግ ሕልም እውን ኾኗል ፤ የወደፊቱ የጥቁሮች የኑሮ ተስፋ በአሜሪካ ጭላንጭል ታየ።

## (፰) ዐራት የሰንበት ተማሪዎች ሞት

የማርቲን ሉተር ኪንግ የዋሽንግተን ንግግር ካለፈ ከአንድ ወር በኋላ በድጋሚ በበርሚንገሃም ከተማ በጥቁሮች ላይ ጥላቻውና ቁጣው የበለጠ ኾነ ። የነጭ ሽብር ፈጣሪዎች የኩ ክላክስ ክላን አባላት ቦምብ በባፕቲስት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ምድር ቤት የወጣቶችን በዓል ለማክበር ከተሰበሰቡት ሰንበት ተማሪዎች ላይ ወረወሩ። በዚህ ጊዜ ዐራት ጥቁር የሰንበት ተማሪዎች ልጆችን ተገደሉ ፤ ብዙዎችም ቆሰሉ።

በቦምቡ የሞቱት ልጆች፤ ዴኒስ ሚክኒየር 11 ዓመት ፣ ኬራል ሮብንሰን 14 ዓመት፣ ሲንቲያ 14 ዓመትና አዲሜል 14 ዓመት ነበሩ። ከዘኒህ ውስጥ አንዷ የኮንደሊዛ ራይዝ (የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ጓደኛ ነበረች። በቦምቡ የተነሳ ከሞቱት ሌላ ብዙዎች ቆሳሰሉ።

ማመን በሚያቅት ኹኔታ ጥላቻው እየተባባሰ ፥ እየተቀጣጠለ ኼደ። ጥቁሮች አጸፋውን እንመልስ በማለት በብስጭት ስሜት በቁጣ የሚያደርጉት ተቃውሞ እና ድንጋይ ውርወራ እንደገና ተጨማሪ የጥቁሮች ልጆች በፖሊስ ይገደሉ ጀመረ። ቦምቡን የወረወሩት የኩ ክላክስ ክላን (የነጭ ዘረኞች) አባላት ነበሩ ፤ ተይዘው ለፍርድ በመቅረብ የዕድሜ ልክ እሥራት ተፈረደባቸው።

ልጆቹ እንደሞቱ በኹለተኛው ወር ኅዳር 22 ቀን 1963 ፕሬዚዳንት ጆን ኤፍኬኔዲ ቴክሳስ ግዛት በዳላስ ከተማ ሲጓዝ በጥይት ተተኩሶበት ተገደለ ። ኪንግ ፕሬዚዳንት ኬኔዲ ከእሱ ጋራ እንደሚሠራ ያውቅ ነበር። እኩልነት ማምጣት መልካሙ መንገድ እንደኾነ የኬኔዲ እንዱ ምኞቱ ነበር ። እንደማንኛውም አሜሪካውያን ኪንግ በኬኔዲ መገደል በጣም አዘነ ። ለሚስቱ ለኮሬታ ይህች መንገድ አንድ ቀን እኔም ደግሞ የምኼድባት ነች ። እንደነገርኩሽ የታመመ አገር እና የታመመ ኅብረተሰብ ኾኗል አላት ። በኬኔዲ ቦታ ሌላ ፕሬዚዳንት ከደቡብ ክፍል የኾነው ሊንደን ጆንሰን ተመረጠ ። የኬኔዲ ፖሊሲ ዘረኝነትን ለማጥፋት ነበር።

ኪንግ ያለበቀል በሰላማዊ መንገድ የጠሉንን እናሸንፋለን የሚለውን ሐሳቡን እና ዓላማውን ለሰዎች ማሳመን ከባድ ነገር ኾነበት ። ከዋሽንግተን ንግግር በኋላ በዓለም በጣም ዝነኛና ታዋቂ ኾነ። በ1964 በሰብአዊ መብት የኖቬል የሰላም ሽልማት (የኖቬል ፒስ ፕራይዝ) አገኘ፤ የዓመቱ የክብር ተሸላሚ ኾነ። ለዚህ ሽልማት ሲበቃ ዕድሜው 35 ዓመት ነው። ይህንን ታላቅ ሽልማት በወጣትነት ሲያገኝ የመጀመሪያ ሰው ነው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላም ኪንግ ሥራውን ቀጠለ ። በደቡብ በጣም ጥቂት በኃላፊነት የተመረጡ መሪዎች ነበሩ ። ለመምረጥም በጣም ጥቂት ጥቁሮች ተመዝግበው ነበር ። ለምሳሌ በሚሲሲፒ ለመምረጥ የሚችሉ ተብለው 7% በመቶ ጥቁሮች ብቻ ተመዝግበው ነበር ። ለመመዝገብ ሲኼዱ እንዲመለሱ ይደረጋሉ ። ማርቲን ይህን ነገር ተገንዝቦ በቀለም ልዩነት የሚደረገው አድልዎ የተነሳ የምርጫ ሕግ መለወጥ እንዳለበት ያምን ነበር ። በአላባማ 300,000 ጥቁሮች አልተመዘገቡም ። እነዚህ ግዛት ውስጥ ዘረኝነት በጣም የከፋ ነበር ። ኪንግ ጥቁሮች ተመዝግበው እንዲመርጡ በሴልማ አላባማ ግዛት ጠየቀ ። በየቀኑ ጥቁሮች በሴልማ በሕግ ፍርድ ቤት መሰለፍ ጀመሩ ። ፖሊስ ሰልፉን በመበተን ሊያቆማቸው ቢሞክርም አልቻለም። ሰላማዊ ሰልፍ ተሰላፊዎቹም ተደበደቡ አንድ ሰው ሞተ። ኪንግ ከሴልማ እስከ ሞንቶጎሞሪ እንዲኼዱም ዋና ከተማው አላባማ ድረስ ሰልፉን ለመምራት ወሰነ ። ከ30 ሺህ በላይ የሚኾኑ በሰልፉ ተሳታፊ ነበሩ። የግዛቱ አስተዳዳሪ ጆርጅ ዋላአስ ሰላማዊ ሰልፉን ለመቀበልና ለመገናኘት አልፈቀደም። ነገር ግን ዋሽንግተን የሚገኘው የመንግሥት አስተዳደር ሰላማዊ ሰልፉ ምን እንደኾነ መረጃ ደርሶታል ።

ከዋሽንግተን ሰላማዊ ሰልፍ በኋላ በ1964 ፕሬዚዳንት ሊንደን ጆንሰን አሜሪካውያን በሙሉ የመምረጥ መብት አላቸው የሚለውን ሕግ በፊርማው ሲያጸድቅ ኪንግ በዚያ ከተገኙት አንዱ አስፈጻሚ ነበር።

## (፱) በጥቁርነቴ እኮራለሁ

በ1960 በአሜሪካ ታላቅ ለውጥ የተደረገበት ዘመን ነው ። ወጣቶች ልጆች እንደ ወላጆቻቸው ባህልና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓት ጠብቀው የሚኖሩት አኗኗር ሳይኾን ማንኛውንም ነገር ነጻነት እንዲኖራቸው



የጠየቁበት ዘመን ነው ። በብዙ አቅጣጫ የነጻነት ለውጥ የታየበት ዘመን ነው።

ኪንግ ለጥቁር ወጣቶችም ለመብት፣ ለነጻነት እና ለእኩልነት ለውጥ ማድረግ አለብን በማለት በከፍተኛ ጥንካሬ ይሠራ ነበር። ነገር ግን የሱ መንገድ ቶሎ ለውጥ አላመጣም፤ ለውጡ ዘገየ። ስለዚህ ብዙ ጥቁሮች ኀይል መጠቀም እንጂ በትሕትና መጠየቅ አልፈለጉም ። አስፈላጊ በኾነ ጊዜ ቁጠኛነታችንን ማሳየት አለብን ብለው ወሰኑ።

በ1966 ቦቢ ሴል እና ሁይ ኒውተን የጥቁር ግስላዎች (PANTHERS) የሚል ድርጅት አቋቋሙ ። ግስላዎቹ የወሰኑት ውሳኔ ጥቁሮች መታጠቅ አለባቸው ። ጠመንጃ ገዝተው ራሳቸውን መከላከል አለባቸው ። በነጮች ሲጠቁ መልሰው ማጥቃት አለባቸው ብለው ወሰኑ። መሪዎቹ ሴልና ሁይ ኒውተን የሚባሉት ተይዘው ወደ እስር ቤት ገቡ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ እነዚህ የጥቁር ግስላዎች እንቅስቃሴያቸው ቆመ። ብዙ ወጣት ጥቁሮች፥ ጥቁር በመኾናችን እንኮራበታለን በማለት ተነሱ። ስለ አፍሪካ ለመማር ለማወቅ ይሞክሩ ጀመር ። የአፍሪካዊ ምግብ መመገብ ፣ የአፍሪካዊ ልብሶች መልበስ ፤ አፍሪካዊ ቋንቋ ለማጥናትና ለመናገር ጥረት ያደርጉ ጀመር ። ኔግሮ የሚለው ስም የሚያንጸባርቀው ባርነትን ስለኾነ ጥቁር ወይም አፍሪካን አሜሪካ ቢባል የሚመረጥ መኾኑን አመኑበት። ዛሬ አንድ ጥቁር ሰው ኔግሮ ተብሎ ቢጠራ ስድብ ኾኖ ስለሚቆጠር ከፍተኛ አንባጓሮ ያስነሳል።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም በጉብኝታቸው ጊዜ ተንኮለኞቹ የአሜሪካ ጋዜጠኞች ኔግሮ ነህ ሲሏቸው አይደለሁም ጥቁር ነኝ በማለታቸው እንዳንዶች በጊዜው ኔግሮ ተብለው በነጮች የሚጠሩት ጥቁር አሜሪካኖች አልተደሰቱም ነበር ። ነገር ግን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተናገሩት ትንቢታዊ ቃል ተፈጽሞ ዛሬ ኔግሮ ነኝ የሚል ጥቁር የለም ። ነገር ግን ጥቁር አሜሪካዊ (አፍሪካን አሜሪካ) ነኝ ተብሎ ይነገራል።

## (፲) ማልኮልም ኤክስ

ሌላው የጥቁሮች ቡድን መሪዎች ቀደም ሲል ጀምሮ ተቃውሞ ያሰሙ የነበሩት ኤላጃ መሐመድና ተከታዮቹ ማልኮልም ኤክስ እና ሊዊስ ፋረካን ሌሎችም ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ከአሜሪካ ፕሮቴስታንት የነጭ የክርስትና ሃይማኖት ልዩ ለመኾን "ጥቁር እስላሞች" ተብለው ለመጠ

ራት የእስልምናን ትምህርት መማር ጀመሩ ። ከዚያም "ኔሽንኦፍ ኢስላም" የሚባለውን ድርጅት አቋቋሙ።

የእስልምና ሃይማኖት በሳውዲ ዐረብያ የተመሠረተ እምነት ነው። መሥራቹ ነቢዩ መሐመድ የነበረበት ዘመን ከ570 እስከ 632 ዓ. ም. ነው ። እምነቱም አላህ ነቢያቶችን ላከ ፤ ከነቢያቶች አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እሱም ከድንግል ማርያም ተወለደ ፤ ከእሱ በኋላ ግን የመጨረሻው ነቢይ ነቢዩ መሐመድ ነው ብለው ያምናሉ።


ማልኮልም ኤክስ (Malxolm X) የቀድሞ ስሙ ማልኮልም ሊትል ነበር። ይህን የነጭ ስም አልፈልግም ብሎ ሊትልን ኤክስ በማለት ለወጠው። ማልኮልም የተወለደውና ያደገው ኦሞሀ የምትባል ቦታ ነብራስካ ግዛት ሲኾን አባቱ የማርቆስ ጋርቬይ ደጋፊና የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ቄስ ነበር ። በኋላ ግን ዘረኛ ነጮች በመኪና ገጭተው ገደሉት። አባቱ ሲሞት እናቱ ወደ ላንሲንግ የምትባል ከተማ ሚችጋን ግዛት ልጆቿን ይዛ ተጓዘች ። በዚያም ድህነት እና ብቸኝነት በላጠቃት አእምሯን ስታ ሆስፒታል ገባች ። የ8ኛ ክፍል ተማሪ የነበረው ማልኮልም ትምህርቱን አቋርጦ ወደ ቦስተን እና ኒው ዮርክ ሀርለም በመኼድ ወንጀል ውስጥ ገባ ። ሲሰርቅ ተይዞ ለ8 ዓመት ያህል ተፈርዶበት ታሠረ ። ከእሥር ቤት ሲወጣ "ኔሽን ኦፍ ኢስላም" በሚለው ድርጅት ውስጥ ገብቶ ኃይለኛ የእስልምና ሃይማኖት ሰባኪ በመኾን ብዙ ሰዎችን ሳበ።

ማልኮልም ኤክስ በኪንግ ሐሳብ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞን ማሰማት አይስማማም ። የሚስማማው ልክ እንደ ጥቁር ግስላዎች ሐሳብ ነው። ጥቁሮች ጠንካራ ኾነው ራሳቸው መከላከል አለባቸው። ካስፈለገም ደግሞ በጠመንጃ መከላከል ይኖርባቸዋል ። ከነጮችም ምንም ዕርዳታ መሻትና መቀበል የለባቸውም "ለመብት ሲባልቁጡ ኾኖ መገኘትና መታገል ያስፈልጋል" አለ።[184] ብዙ ወጣት ጥቁሮች በዚህ ሐሳቡ ተስማሙ ። ኪንግን ከሚከተሉት የበለጠ ማልኮልም ኤክስን ተከተሉት። በሰሜኑ ከተሞች ያሉ ደሀ ጥቁሮችም ምርጫም ለመምረጥ አይችሉም ነበር ። የተሻለ ቤትና እንዲሁም ብዙ የሥራ መስኮች እንዲከፈትላቸው ይፈልጉ ነበር ።

ማልኮልም ኤክስ በተከታዮቹ ታላቅ ሸምና ዝና አገኘ ብዙዎች ተከተሉት፤ በዚህ ጊዜ በድርጅቱ እንቅስቃሴ ውስጥ ቅናት ገባ ። የድርጅቱ መሪ ኢላጃ መሐመድ ከእስልምና እንዲወገድ አደረገው።

[184] Susan Altman., *p., 155*





ማልኮልም ኤክስ



በጥቁርነቴ እኮራለሁ

ማልኮልም ኤክስ በ1964 ከኔሽን ኦፍ እስላም ወጥቶ ወደ መካ (ሳውድ ዐረቢያ) በመኼድ ሐጂ ኾነ፤ ከዚያም ከዚያ አድርጎ ኢትዮጵያ ደርሶ ዐዲስ አበባን ጎብኝቷል። በዚህ ወቅት በዐዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ተገኝቶ ለተማሪዎች ንግግር አድርጓል።

ዛሬ ከእናንተ ጋራ በመኾኔ በቤቴ እንዳለሁ ኾኘ ተሰምቶኛል፤ በአሜሪካ እስከዛሬ ድረስ ለ300 ዓመታት ተቀባይነትን አላገኘንም።[185] ሲል በጉባኤ ተናግሯል።

ወደ አሜሪካ ሲመለስ የእስልምና መስጊድ በሀርለም አሠራ። አፍሮ አሜሪካን ዩኒቲ[186] በማለት ድርጅት አቋቋመ ። ተቃውሞው ነጮችን ሳይኾን ዘረኞችን ኾነ። ዋና ምክንያቱ ነጭ የኾኑ እስላሞች በሚገባ ስለተቀበሉትና ስለአስተናገዱት ነው ። የኔሽን ኦፍ ኢስላም መሪ ኤልያስ መሐመድ ዘረኛ መኾኑን አወጀ ። የኔሺን ኦፍ ኢስላም የበላይ ባለሥልጣኖች በማልኮልም ኤክስ ተቆጡ ፤ ጋዜጣ ማውጣት ጀመሩ። ጋዜጣውም "መሐመድ ይናገራል" (MUHAMMAD SPEAKS) የሚል ነበር። በውስጡ የሚይዘውም ማልኮልም ኤክስ ሞት ይገባዋል የሚል ነበር። የካቲት 14 ቀን 1965 የማልኮልም ኤክስ ቤቱን አቃጠሉበት። ከሳምንት በኋላ ሦስት የኔሺን ኦፍ እስላም አባላት በጥይት

[185] TADIAS E. – A. Lifestyle & B. M. March/April 2005 p. 36 Fikru Negash G.
[186] (The ORGANIZATION OF AFRO AMERICAN UNITY)

ተኩሰው ገደሉት። ብዙዎች የጥቁር መብት ተከራካሪዎች ጥቁር እርስ
በእርስ በመጠፋፋታቸው በድርጊቱ በጣም አዘኑ።

## (፲፩) ሊዊስ ፋራካን

አኹን ያለው የኔሺን ኦፍ ኢስላም የበላይ ባለሥልጣን ለዊስ
ፋራካን ይባላል። እሱና ጓደኞቹ ናቸው የገደሉት በሚል ታምተዋል፤
እሱም በጉዳዩ እንደሌለበት ገልጿል ፤ ብዙዎች የማልኮልም ኤክስ
ሞት ከኋላ ኩ ክላክስ ክላን የሚባለው ድርጅት አለበት በማለት ጥር
ጣሬ አድሮባቸዋል።

በ1995 ሊዊስ ፋራካን እና ሌሎች የእስልምና መሪዎች አንድ
ሚሊዮን ሰዎችን ያሳተፈ ሰላማዊ ሰልፍ በአሜሪካ ዋና ከተማ በዋሽንግ
ተን ዲሲ ማድረጋቸው ይተወቃል ። በዚህ ሰልፍ ካልተሳተፉ ማንነታ
ቸውን እንደ ክዱ እንደሚቆጠር ለብዙ ጥቁር ክርስቲያኖች ተነግሯ
ቸው ነበር። ከሰልፉ በኋላ ደግሞ ሊዊስ ፋራካን በአሜሪካ አገር የእስ
ላም መንግሥት መቋቋም እንዳለበት ንግግር አድርጓል። ሊዊስ ፋራካን
በፕሮፌሰር ሄንሪ ሊዊስ ቃለ መጠይቅ በተጠየቀ ጊዜ ስለ ኢትዮጵያ
እና ስለ ኢትዮጵያ ንጉሥ እንዲህ ብሎ ተናገሮ ነበር።

> እኛ ጥቁሮች፣ አገር ያለን እና ቅዱሳት መጽሐፍ ውስጥ ስማ
> ችን የተጠቀሰ አይመስለንም ነበር ። ነገር ግን ኢትዮጵያን ባገ
> ኘን ጊዜ ፤ ከዚያም አፍሪካን ስናገኝ ማንነታችንን አገኘን ።
> ኢትዮጵያን ማግኘት እንደምትሐት ነው የኾነብን ። ይህ ለጥ
> ቁር ሕዝቦች ምስጢርና ምትሐት ነው። በይበልጥም ያ ታላቅ
> ስም ራስ ተፈሪ ፤ በፍጹም ያላየነው የጥቁር ንጉሥ ። የእን
> ግሊዝ ነገሥታቶች ነጮችን አይተናል ። ንጉሥ ጆርጅን ፣ ንግ
> ሥት ኤልሳቤጥን ፤ ኃይለ ሥላሴን በማየታችን እኛነታችንን
> እንድናይ አድርጎናል።[187]

## (፲፪) ጥቁርና ነጭ በአንድነት የተዋጉት የቬትናም ጦርነት

ኪንግ በደቡብ የሚገኙትን ጥቁሮች ነጻ ለማውጣትና ከነጮች እኩል
ለማድረግ በትምህርት ቤትም አድልዎ እንዳይደረግ ብዙ ታግሏል።

[187](**PBS HOME VIDEO** Harry Louis Gates, Jr. AFRICAN WORLD)



በሰሜኑ ያሉት ጥቁሮች ከነጮች ጋር አንድ አይነት ትምህርት
ቤት እየኼዱ ይማራሉ። ነገር ግን ብዙዎቹ የጥቁር ልጆች ትምህርታቸ
ውን ሳይጨርሱ ይቀራሉ። አብዛኛዎቹ የሚኖሩት በድህነት ነበር ።
ትምህርት ቢጨርሱ እንኳን የሚኼዱበትና ሥራ የሚሠሩበት ቦታ አያ
ገኙም፤ የተጉሳቈለ ኑሮ ይኖሩ ነበር ። ከአንድ ቤተሰብ ሲወርድ ሲዋ
ረድ የመጣውን አሮጌና ያልጸዳ ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር። በዚህ የተነሳ
ኪንግ በሰሜኑ ከተማ በቺካጎ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ አሰበ

የሰላማዊ ሰልፉ ዓላማው በሰሜን የሚኖሩት ጥቁሮች እንዴት
በመጥፎ አኗኗር እንደሚኖሩ ለአሜሪካ ለሕዝቦች ለማሳየት ነው ።
ድህነቱ በጥቁሮች ብቻ ሳይኾን በአንዳንድ ነጮችም ነበር ። ስለዚህም
ኪንግ ኹለቱም በአንድነት እንዲታገሉ በመቀስቀስ ሰላማዊ ሰልፉን
በቺካጎ ከተማ ዋና መንገድ ላይ አደረገ። ምንም እንኳን ጥቁሮች ከነ
ጮች ጋር መሰለፍ ባያስደስታቸውም በመጨረሻው ሰልፉን የከተማው
ፖሊሶች በተኑት።

ኪንግ እንደገና ወደ ዋሽንግተን እነዚኽን ድሀ ሰዎች ለማሰለፍ
ዕቅድ አደረገ ። ነገር ግን የቬዬትናም ጦርነት ስለተጀመረ ሐሳቡ
ተቀይሮ ጦርነቱን ከሚቃወሙት ጋራ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ጀመረ ።
በጥር 1967 ኪንግ ለመጀመሪያ ጊዜ የቬዬትናምን ጦርነት ተገቢ
አለመኾኑን ተቃውሞ አሰማ ። ሚያዚያ 4 ቀን በሰላማዊሰለፍ ላይ
ባደረገው ንግግር በጦርነቱ ለሚሞቱት ድምጹን አሰምቶ አለቀሰ ።
"ብዙዎች በጦርነት ትግል ከሚሞቱ በዚሁ በቤታቸው ድህነትን ቢዋጉ
የተሻለ ነው፤" በማለት ንግግር አደረገ።

በቪዬትናም በጦርነት ግንባር ላይ ያሉት ወታደሮች ብዙዎች
ጥቁሮች ሲኾኑ እነዚህም ከድሀ ቤተሰብ የወጡ ናቸው ። በዚህ ጦር
ነት የቪዬትናም ተወላጆች ወንድ ፣ ሴት ፣ ሕፃን ሳይቀር በቦምብ
ተደብድበዋል። መንደሮችና የሩዝ እርሻዎች ተደምስሰዋል ። አሜሪካ
በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው 59 ሺ ወታደሮች ከኼዱበት አል
ተመለሱላትም። የነዚህ ኹሉ ስም በዋሺንግተን ዲሲ በግንብ ግድግዳ
ሐውልት ላይ ለመታሰቢያ ተጽፎላቸዋል። ጦርነቱ በ1966 ተጀምሮ ከዘ
ጠኝ ዓመት በኋላ በ1975 ተፈጸመ።[188] ይህም በአሜሪካ ታሪክ ረዥሙ
ጦርነት ነው ። ብዙ አሜሪካውያን ይህን ጦርነት ተቃውመውታል ፤
ይህም አሜሪካንን የሚያኽል አገር አንዲት ትንሽ አገርን መውጋት የለ
በትም በሚል ነው ። ኪንግ ይህን ሐሳብ ይደግፍ ነበር ። በአሜሪካ

[188] **Patricia S. Daniels &Stephen G. B.**, *P., 311*

ግዛት ውስጥ ኹሉም ተቃውሞውን በማሰማት ሰላማዊ ሰልፍ በተደጋ
ጋሚ አድርጓል ። የተቃውሞ ተሰላፊዎቹም ከፖሊሶች ጋራ ግጭት
ፈጥረዋል ። የቬትናም ጦርነት የተቃውሞ ሰልፉ ብዙ ብጥብጥ አምጥ
ቷል ። ተማሪዎችም ቬትናምን ለመውጋት ወደ ውትድርና አንገባም
በማለት ትልቅ ብጥብጥ አድርገው ነበር። አሜሪካንን ለመለወጥ የሚያ
ለው የኪንግን ፖሊሲ በመከተል በሰላማዊ መንገድ የተሳካ ውጤት
እናመጣለን የሚል እምነት በብዙዎች አድሮባቸው ነበር።

## (፲፫) የሜምፊስ ሞት (ቴነሲ)

የጥቁር ግስላዎችና የማልኮለም ኤክስ ተከታዮች የኪንግን ሐሳብ መቀ
በል አይፈልጉም። ነጮች ለሚያደርሱት ጥቃት መልሶ ማጥቃት ነው።
የሚል አንድ መልስ ሲኾን፥ ይህንም ብዙ ወጣት ጥቁሮች ተስማምተ
ውበታል ። በዚህ የተነሳ ብዙ ብጥብጥ በከተሞችና በየቦታው ተነስ
ቷል። ለምሳሌ ዲትሮይት፣ ቺካጎ እና የሎሳ አንጀለስ ወጣት እየተሰባ
ሰቡ ጋንግ የሚል የቡድን ስም በማውጣት የከተማዎቻቸውን በር ይጠ
ብቁ ነበር ። አንዳንዴም እነዚህ የጋንግ ብድኖች እርስ በርሳቸው
ይጣሉ ነበር። ብዙ ጥቁሮች ሽጉጥና ስለት ስለሚይዙ ተጋድለዋል ።
በዚህ የእብደት ሥራ ኪንግ በጣም ይናደድ ነበር ። ኾኖም ደግሞ
ለምን እነዚህ ጥቁሮች እንደሚናደዱ ይረዳል። የሱ መመሪያ ቁጠኝነ
ትና ኃይለኝነት እንደማያዋጣ መልስም እንደማይኖረው በየንግግሩ ደጋ
ግሞ ይጠቀምበት ነበር።

ኪንግ እስከ 1968 ለዐሥራ ኹለት ዓመት ያለ ዕረፍት ለጥቁ
ሮች መብት ተናገረ። ወደ መቶ የሚደርሱ ከተሞች ኼዶ የነጻነት የኩ
ልነት ንግግሩን አድርጓል ። በሚሊዮን የሚቆጠር የደቡብ ጥቁሮች
ተከትለውታል ፤ አብሯቸው በየሰልፉ ተሳትፏል ። የዚህ ኹሉ ትግል
ውጤት የጥቁሮችን ትግል በ1950 ከነበረው ቀነሰው እንጂ ጨርሶ አላ
ቃለለውም፤ ትግሉም ለረጅም ጊዜ እንደሚቀጥል ተገንዝቦ ነበር።

በመጋቢት ወር 1968 በሜምፊስ ቴነሲ ግዛት ሠራተኞች የሥራ
ማቆም አድማ አደረጉ፤ የህ የሥራ ማቆም አድማ የከተማዋ የጽዳት
ሠራተኞች በሥራቸው በሚያገኙት ገቢ ማነስ ምክንያት ነው። ቆሻሻ
እያጸዱ የሚከፈላቸው በጣም ዝቅተኛና ለኑሮ በቂ ባለመኾኑ አብዛኛ
ዎቹ ሠራተኞች በኑሯቸው ይሰቃዩ ነበር። እነዚህም ጥቁሮች ስለ ነበሩ
ኪንግ ሰላማዊ ሰልፍ አብሯቸው በመውጣት እንዲረዳቸው ጠየቁት ።
እሱም በሜምፊይስ ጀምስ ላውሶን በሚባለው የማኅበራቸው አባል



ካህን ለዕርዳታ ጥሪ ቀረበለት። በጥር 18 በአውሮፕላን በረራ አድርጎ
ደረሰ ። በዚህ ወቅት በሺ የሚቆጠር ሰዎች የሞቀ አቀባበል አደረጉ
ለት ። በተጋበዘበት ቦታ ኹሉ ኼዶ ንግግር አደረገ።

ኪንግ በጥር 28 ተመልሶ በሜምፊስ አውራ ጎዳና አብሮ ሰላ
ማዊ ሰልፍ እንደሚወጣ ተስማማ ። ሰላማዊ ሰልፈኞቹ እጅ ለእጅ
ተያይዘው የተለመደውን መዝሙር እየዘመሩ ወጡ ። የፈለጉት በሰላ
ማዊ መንግድ ተቃውሟቸውን ማሰማት ነበረ። ነገር ግን ጋንግ የተባለው
የጥቁር ወጣቶች ቡድን የሱቆችን መስኮቶች በመሰባበር ከፖሊስ ጋራ
በመደባደብ ሰልፉ ሰላማዊ መኾኑ ቀርቶ የብጥብጥ ኾነ። አንድ የጋንግ
ቡድን አባል የኾነ በትግሉ መኻል ተገደለ ። ከሰላማዊ ሰልፉ በኋላ
ግን ኪንግ ለጋንጎቹ ቡድን ንግግር አደረገ። እሱ የሚፈልገው ቁጣን
በተሞላበት ሳይኾን በሰላማዊ መንገድ መብትን ማስከበር ሲገባ በቁጣ
ግን ምንም መልስ እንደማይኖር ንግግር አደረገ ። የጋንጎች ቡድኖቹ
በዚህ ጉዳይ ተስማምተው በሚቀጥለው መጋቢት በሰላማዊ መንገድ
ከሠራተኞቹ ጋር ለመሰለፍ ቃል ገቡ። በቃል ኪዳኑ መሠረት የቁጣው
ትግል ቀረ ። ኪንግ ወደ መኖሪያው ወደ አትላንታ ተመለሰ።

በሚቀጥለው መጋቢት ወር ላይ ግንኙነት የሚደረገው ቀርቶ
ለሚያዚያ 5 ቀን ሰላማዊውን ሰልፍ እመራለሁ ብሎ የቀጠረው ኪንግ
በዚያ ቀን አልታየም። ሰልፉም አልተካኼደም ። በሚያዚያ 3 ቀን ኪ
ንግ ተስፋና ትንቢት የተሞላበት ንግግር በአመሻሽ ላይ በተጨናነቀ የጥ
ቁሮች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደነቅ ንግግር አደረገ ። ንግግሩም
ቀደም ሲል በ1958 በሕይወቱ የደረሰበትን በመጥቀስ የወደፊቱን በመግ
ለጽ ተናገረ ፤ ከተናገረው ጥቂቱ እንዲህ የሚል ነበር።

ደህና ! አኹን ምን ሊፈጠር እንደሚችል አላውቅም ። በሚቀ
ጥሉት ቀናት አስቸጋሪ ነገር ሊገጥመን ይችላል ። ነገር ግን
በአኹኑ ሰዓት በኔ በኩል ምንም ማለት አይደለም ። ግዴለ
ኝም ፤ ምክንያቱም በተራራው ጫፍ ላይ ነበርኩና ምንም አይ
መስለኝም፤ እንደ ማንኛውም ሰው ረዥም ሕይወት (ዕድሜ)
እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፤ ረዥም ዕድሜ የሚኖርበት የራሱ ቦታ
አለው። ነገር ግን በአኹኑ ጊዜ ስለሱ አያሳስበኝም፤ የእግዚ
አብሔር ፈቃድ ከኾነ መሥራት እፈልጋለሁ ። ኾኖም ግን
የእሱ ፈቃድ ወደ ተራራው እንድወጣ ነው። ይህንም አሻግሬ
አየዋለሁ እናም የቃል ኪዳኗን ምድር አይቻለሁ ። ከናንተ
ጋርም ወደዚያ ላልደርስ እችላለሁ። ነገር ግን በዛሬዋ ምሽት
እናንተ እንድታውቁት የምፈልገው እንደማንኛውም ሰው ወደ

ተስፋዋ ምድር እንደርሳለን ። በዛሬው ምሽት ደስ ብሎኛል ለምንም ነገር አላስብም ፤ ማንንም ሰው አልፈራም ዓይኔ የጌታን በክብር መምጣት አይተዋል።

በማለት ትንቢታዊ ስብከት ሰበከ። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ላይ ያለውን አስተማረ። ይህ ንግግሩ በቪድዮ ተቀርጿል ።

በሚቀጥለው ምሽት ሚያዚያ 4 ቀን 1968 ኪንግ ካረፈበት ሎሬይኔ ሞቴል ወጥቶ ወደ ሰገነቱ እየተራመደ ሲኼድ የጥይት ተኩስ ተሰማ። ጓደኞቹም ተሯሩጠው ወደ ሰገነቱ ኼዱ። ኪንግ በመሬት ላይ ወድቆ አገኙት፤ በጥይት አንገቱንና መንጋጋው ተመቷል። ከአንድ ሰዐት በኋላ ኪንግ በመምፊስ ሆስፒታል ውስጥ ሞተ ተብሎ ተነገረ ፤ በዚህ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዘጠኝ ዓመት ነበር።

የኪንግ ሞት የአሜሪካንን ሕዝብ አስደነገጠ ። በተለይ ጥቁር አሜሪካኖች የሚወዱት ለነጻነትታቸው የሚታገልላቸውና የሚመኩበት መሪያቸው ሲወሰድባቸው ማመን አቃታቸው ። ይህ ድንጋጤም ወዲያው ቁጣና ብስጭትን አስከተለ ። በዚህም ከኃይለኞቹ የጥቁሮች መሪ ከኾኑት አንዱ ስቶክሊ ካአረሚክሰሄል[189] በዋሽንግተን ዲ.ሲ ጥቁሮች እንዲሰባሰቡ አደረገ። ከዚያም ትእዛዝ አስተላለፈ። ትእዛዙም "ወደ ቤት ኼዳችሁ ጠመንጃችኹን አንሱ!! ከዚያም ለመብታችሁ ታገሉ" የሚል ነበር።

በዩናይትድ እስቴት በታላላቅ ከተሞች ከፍተኛ ብጥብጥ ተነሳ። ከ40 የሚበልጡ ጥቁሮች በፖሊስ ተገደሉ። ብዙ ነጮች የከተማ ቤታቸውንና ኑሯቸውን እየለቀቁ ወደ ከተማ ዳርቻ መኖር ተገደዱ ። በዚህ ረብሻ የተነሳ በዋና ከተማው ዋሽንግተን ዲ.ሲ 10 ሰዎች ሞቱ። በነጮች መኖሪያ ቤት እሳት ይለቁባቸው ጀመር። ለምሳሌ እንደ ቦልቲሞር እና ዋሽንግተን ዲ.ሲ ከተማ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ነጮች ቤቶቻቸውን ለቀው ስለኼዱ እስከ ቅርብ ጊዜ ከመኻል ከተማው ወጣ ያሉት መንደሮች እና የተለቀቁት ቤቶች ተዘጋግተው ይኖሩ ነበር ። መዘጋታቸው ብቻም ሳይኾን የዕፀ ፋርስ መቀባበያ፤ የአይጥ መታጎሪያ (ጌቶ) ኾነው በማስፈራራት ይታዩ ነበር። ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ግን አዳዲስ ሕንጻ በመገንባት በፍጥነት ለውጥ እየታዩ ነው።

የኪንግ ገዳይ ነጭ አሜሪካዊ ጀምስ ኤርል ሬይ ይባላል ። ኹለት ወር ከዐራት ቀን ከተሸሸገ በኋላ በብሪታንያ ኢንግላንድ ግዛት ውስጥ በለንደን ከተማ በሰኔ8 ቀን መያዙ በቴሌቪዥን ተነገረ። ተይዞ

[189]. STOKELY CARMIXHAEL



በእስር ቤት ገባ። በመጋቢት 10 ቀን 1969 የዕድሜ ልክ እሥራት ወይም 99 ዓመት ተፈረደበት ። ነገር ግን በአመክሮ ከእስር ቤት 30 ዓመት ከቆየ በኋላ ተፈታ። የኪንግ ልጆች ይቅርታ አደረጉለት። ብዙ ሰዎች የማርቲን ገዳይ ጀምስ ኤርል ሬይ ብቻውን ሳይኾን ከበስተኋላው ነጮች ፖለቲከኞች ያሉበትና በገንዘብ በመግዛት ብዙ ከፍለውት ነው ብለው ያምናሉ።

የጥቁር ሕዝቦች የመብት ተከራካሪው ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር በአባቱ ቤተ ክርስቲያን በአትላንታ ከቅድመ አያቶቹ አጠገብ ተቀበረ። የሰው ልጆች መብት ያለ አድልዎ በእኩልነት መኖር አለባቸው እያለ የሚከራከረውን ኪንግን ለመሰናበት በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ተገኘ። በመጨረሻም በሐውልቱ ላይ ዝነኛ የኾነው የንግግሩ መጨረሻ "FREE AT LAST, FREE AT LAST; THANK GOD ALMIGHTY, I'M FREE AT LAST" የሚለው ተጽፎ ይገኛል።

በ1983 ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬጋን፥ ባለቤቱ እና ልጆቹ ባሉበት የዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ የልደት ቀን በአሜሪካ የዕረፍት ቀን ኾኖ በመታሰቢያነት እንዲከበር ተወሰነ። በሕግ ላይ እንዲሰፍር ፕሬዚዳንቱ ፊርማውን አኖረበት። ይህም ዕለት በመጀመሪያ የተከበረው ጥር 15 ቀን 1986 ነው። በጥር ወር በያመቱ ይከበራል።

በአሜሪካ እኩልነት ተመሥርቶ ጥቁሮች ነጻነት አግኝተው እንደማንኛውም አሜሪካዊ ነጭ ጥቁሮች ተደርጎ የማይታወቀውን የአስተዳደር እና የአመራር የሥልጣን ቦታ መያዝ ጀመሩ ። ኔግሮ ተብሎ ከመጠራት "ጥቁር" መባልን ከዚያም ጥቁር ከመባል በዚህ ዘመን ደግሞ "አፍሪካን አሜሪካን" ተብለው እንዲጠሩ ኾነ ። ዛሬ እነዚህ አፍሪካን አሜሪካ ታላላቅ ቦታ ላይ ደርሰዋል ። በመንግሥት አስተዳደር፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በንግድ ዓለም፣ በእስፖርት፣ በስነጽሑፍ፤ በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች፣ በዩኒቨርሲቲና በኮሌጅ ከፍተኛ ቦታን እየያዙ መጡ። የኪንግ የትግል አጋር ከነበሩት ውስጥ ቄስ (ሬቨረንድ) ጄሲ ጃክሰን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ለመኾን በ1984 እና በ1988 ወድድር ውስጥ ገብቶ ነበር ። የጥቁሮች የሰብአዊ መብት ትግሉን እስከ ዛሬ እንደቀጠለ ነው።

ጥቁሮች የፕሬዚዳንትነት ቦታን እንዲያገኙ የሚደረገው ጥረት ቢቀጥልም በአኹኑ ጊዜ ወደ 300 የሚደርሱ የአሜሪካ ከተሞች በጥቁር አሜሪካውያን ፖለቲከኞች ይመራሉ። የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ

ሚኒስትር ኾኖ ይሠራ የነበረው የቀድሞው ኮሊን ፓዎል ከጥቁር ቤተሰብ የተገኘ ነው ፤ እንዲሁም የፕሬዘዳንት ቡሽ የቀድሞ አማካሪ እንደገና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኾና የተሾመችው ከጥቁር ቤተሰብ የወጣች ዶክተር ኮንዲሊዛ ራይስ ናት። ሌሎችም የአገሪቷ የበላይ የአመራር ሥልጣን ቦታ ይዘዋል።

ለ2009 የፕሬዚዳንት ቦታ ለመያዝ በምርጫ እጩነት ዲሞክራት ፓርቲን ወክሎ ለውድድር የቀረበው በአባቱ ከጥቁር ኬንያዊ እና በእናቱ ከአየርላንድ ዝርያ የተወለደው ባራክ አባማ በአስደናቂ ኹኔታ በአሸናፊነት የአሜሪካን ፕሬዘዳንት ኾነ።

በዕብራይስጥ ቋንቋ ባራክ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ቡሩክ ተብሎ የሚጠራው ይህ የ46 ዓመት ወጣት የአሜሪካና ከአሜሪካ ውጭ የሚኖረውን ጥቁር፣ ነጭ ፣ የሌላም ዝርያ ኹሉም በተሰፋ ሰጭ ንግግሩ ፣ ኪንግ ያለመውን ከ45 ዓመት በኋላ እውን አደረገ ። በንግግራቸው ከተደነቁት የአሜሪካውያን ተናጋሪዎች አንዱ እንደኾነ ብዙዎች መሰከሩ ። ከንግግሩም ውስጥ አትችሉም እንባል ነበረ እንችላለን (Yes We Can) እያለ በመናገሩ ኹሉንም አስደነቀ። የኪንግ የትግል ውጤትና ሕልሙ እውን ኾኖ ታየ ። ባራክ አባማ የቀረውን የኪንግን ሕልም ለመተርጎም ብዙ ነገር ይጠበቅበታል።

ኪንግ ሕልሙ ግማሹ እውን እንዳልኾነም የታወቀ ነው ። ጥቁርና ነጭ ገና እኩል ያልኾኑበት ነገር አለ ፤ ወጣት ጥቁር አሜሪካዊ ከነጩ ወጣት በዐምስት እጥፍ በእስር ቤት ይገባሉ ፣ ከሥራ ይባረራሉ፤ ወይም በመንገድ ላይ ይጋደላሉ ። በትምህርት መስክ ጥቁሮች ዕድሉም ቢመቻችላቸው ብዙም አልገፉበትም ። ይህን ችግር አንድ እርምጃ ወደፊት ኩንግሬስ የነጻ ትምህርት ልዩ ሕግ አውጥቶ በሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል ። ብዙዎቹ ጥቁሮች ለኑሯቸው መሻሻልና ቁልፉ ትምህርት መኾኑ እየታወቀ በዚህ ዕድል አለመጠቀማቸው የሚያሳዝን አንዱ ገጽታ ነው። ኹል ጊዜ የተፈጸመውን ያለፈውን የባርነት ግፍ ወደኋላ በመመልከት በብስጭት ጊዜያቸውን የሚያጠፉ ብዙዎች ናቸው።

ኪንግ የተመኘው ተስፋ በባራክ አባማ መልስ አገኘ።



# ምዕራፍ ፲፩

## ከፕሬዚዳንት ኬኔዲ በኋላ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች

በዩናይትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ አብዛኛዎቹ ፕሬዚዳንቶች የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ናቸው ። የክርስትና እምነት ለፕሬዚዳንት ምርጫ ውድድር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርጋል ። ብዙ ጊዜ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ለመኾን በኅብረተሰቡ ዘንድ መመዘኛው የክርስትና ሃይማኖቱ አንዱ እና ዋናው ነው ። ከፕሮቴስታንት ክርስትና ውጭ አንድ ኬኔዲ ብቻ ከካቶሊክ የክርስትና እምነት ተከታይ የኾነ ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት ተመርጦ አገልግሏል።

አሜሪካ ከተመሠረተች ጀምሮ መሥራቾቹ ፕሬዚዳንቶች በክርስቲያን አምላክ የሚያምኑ መኾኑን የሚገልጹ ብዙ ነገሮች አሏቸው። ፕሬዚዳንት ሲኾኑ ቃለ መሐላ የሚፈጽሙት እጃቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጭነው ነው ። ብሔራዊ የኾኑ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች በመንግሥት አስተዳደሩ ከተማ በዋሽንግተን ዲሲ እንዲሁ በሌሎች ከተሞች አሏቸው ። በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘው የቅዱስ ጴጥሮስ እና የቅዱስ ጳውሎስ የኤጲስቆፓል ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ አንዱ ታሪካቸው ነው።

ይህ የቅዱስ ጴጥሮስ እና የቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ በዓለም ካሉት ታላላቅ ካቴድራሎች በትልቅነት ስድስተኝነት ደረጃ ይዞ የሚገኝ ነው ። እንዲሁም የካቶሊክ የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ካቴድራል ትልቁና ከሚደነቁት አንዱ ነው። መሪዎች እና ታላላቅ ሰዎች ሲሞቱ የክብር የአስከሬን ማሣረፊያ ቦታ ነው ። በሌሎች ከተሞችም ውስጥ ታላላቅ ካቴድራሎች እና አብያተ ክርስቲያናት አሉ።

### (፩) ፕሬዘዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ (ካቶሊክ)

> **እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኛ በከንቱ ይደክማል። ለዚህም እግዚአብሔርን አጋዥ እናደርጋለን ።(ኬኔዲ)**
> **(መዝ. 126 (127)፥1)**

ንድ ከፈለሱት የካቶሊክ ክርስትና እምነት ተከታይ ቤተሰቦች ተወለደ። ኬኔዲ ከዘጠኝ ልጆች መኻከል ኹለተኛው ልጅ ነው ። አባቱ ጆሴፍ ፒ. ኬኔዲ በታላቂቷ ብሪታንያ የአሜሪካ አምባሳደር ኾኖ አገልግሏል።[190] ልጆቹ ጎበዝና በየትኛውም የሥራ መስክ ተወዳዳሪ እንዲኾኑለት ይጥር ነበር። ስለዚህ ኬኔዲ ያደገው በክርክር ፣ በስፖርት ውድድር ነበር። የተማረውም ልዩ በኾነ የግል ትምህርት ቤትና በሐርቫርድ ዩንቨርሲቲ ነው።

ኬኔዲ የተሳካለትን የፕሬዘዳንት ቦታን እንዲሁ በቀላሉ አላገኘውም። በኹለተኛው የዓለም ጦርነት ከጀርመንና ከጃፓን ጋራ ውጊያ በተጀመረበት ጊዜ እሱና ወንድሙ በውጊያው ላይ ተሳትፈዋል ። የባሕር ኃይል ወታደር ኾኖ በባሕር ላይ በተደረገው ውጊያ ጀርባውን በጥይት ተመትቶ ቆስሏል ። ወንድሙ ጆይ ኬኔዲ ደግሞ በቤልጅየም በኩል የጦር አውሮፕላን ሲያበር አውሮፕላኑ ተመትቶ ሞቷል።

ከጦርነቱ በኋላ ኬኔዲ ተመልሶ ለኰንግረስ ምርጫ ተወዳድሮ አሸንፏል ። ከዚያም በኋላ ለምክር ቤት (ለሴኔት) ተመርጧል ። ከጓደኞቹ ጋራ የምሳ ግብዣ ላይ እያለ ተወዳጅ ባለቤቱ የኾነችውን ጃክሊን ሊ ቦቩዬር ጋር ተገናኝተው በ1953 ጋብቻቸውን ፈጽመው ሦስት ልጆች ወለዱ።

ኬኔዲ በድጋሚ በ1958 ለምክር ቤት (ለሴኔት) ከዚያም ከኹለት ዓመት አገልግሎት በኋላ ለዲሞክራቲክ ፓርቲ ለፕሬዚዳንትነት ተመረጠ ። ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት የመሪ ቦታ ለመያዝ የኒክሰን ተቃራኒ በመኾን ኹለቱም እጩዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በቴሌቪዥን ቀርበው ክርክር ገጠመዋል ። ኬኔዲ በንግግር ችሎታ የነበረው ሰው በመኾኑ በራሱ በመተማመን የፖለቲካዊ አቀራረብ እና ፈገግታ በተላበሰ ቀልድ እየቀለደ በቀላሉ ተፎካካሪውንና በዕድሜ የሚበልጠውን ኒክሰንን አሳፍሮ አሸነፈው። የአሜሪካ ሕዝብ በችሎታውና በአቀራረቡ ወደደው።

በ1961 የአሜሪካ 35ኛ ፕሬዚዳንት ኾኖ ተመረጠ። በመመረጡ ብዙዎች ደስ ሲላቸው የደቡብ የአሜሪካ ክፍል ብዙም አልተደሰቱበትም። ብዙዎች የካቶሊክ እምነት ተከታይ ስለኾነ የተደነገገውን ሕገ መንግሥት ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት መለየቱን ትቶ የፖፑን ትእዛዝ ይቀበል ይኾናል ብለው ፈርተው ነበር ። ኬኔዲ ከተመረጠ በኋላ በፕ

[190] **Harry Smith.**, *p., 132*

ንግግሩም (INAUGURATION) እንዲህ ሲል ተናገረ።

> “ወገኖቼ አሜሪካኖች፤ አገሬ ምን ሠራችልኝ ባይኾን ፤ እኔ ለአገሬ ምን ሠርቻለኹ ብላችኹ ጠይቁ።”

ይህ ንግግሩ በአሜሪካኖች ዘንድ ተደነቀለት፤ ለማንኛውም ኅብረተሰብ የሚጠቅም አነጋገር ነው፤ በመቀጠልም

> ኹላችን የወደፊቱ የአሜሪካ ገንቢዎች ነን ። የምንገነባውም ሕዝባችን እና ዜጎችን በማገልገል ነው። ቀደም ብሎ በቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈውን እውነቱን እናውቃለን። “እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኛ በከንቱ ይደክማል” ለዚህም እግዚአብሔርን አጋዥ እናደርጋለን፤ ይል ነበር።

ፕሬዚዳንት ኬኔዲ ካቢኔቶቹና አማካሪዎቹ ብሩህ አእምሮ የነበራቸው ወጣቶች ነበሩ። ከካቢኔቱ ውስጥም ተወዳጅ ታናሽ ወንድሙ አቃቤ ሕግ (አቶርኒ ጀነራል) የቅርብ ረዳቱ ሮበርት ኬኔዲ ነበር።

ፕሬዘዳንት ኬኔዲ የጥቁሮችን የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችን ረድቷል ። በግንቦት ወር 1961 በሞንትጎሞሪና በአላባማ ነጭ ዘረኞች (ኩ ክላክስ ክላን) ጥቁሮች ላይ በሚያደርጉት ሽመቃ ዋና ረዳቱን ጆን ሴኝተአሌርን ስለችግሩ ሪፖርት እንዲያደርግለት ልኮ ነበር። ተላኪውን ጆንን እነዚህ የነጭ ዘረኞች በመደብደባቸው ምክንያት ፕሬዚዳንት ኬኔዲ ስድስት መቶ ፌደራል የመንግሥት ወታደሮች ልኮ ቁጥጥር እንዲደረግ አድርጓል።


የጥቁር ዘር የኾነው ጀምስ መርዲዝ በሰኔ ወራት በ1962 በሚሲሲፒ ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ትምህርት ለመማር አመልክቶ ኔግሮ በመኾኑ በዩኒቨርስቲው ማመልከቻው ውድቅ ኾነበት። በዚህ የተነሳ ፕሬዚዳንት ኬኔዲ በጉዳዩ ጣልቃ ገባ ። ነጮች ዘረኛ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ግቢ በመውጣት የጥላቻ መዝሙር (Glory Glory Segregation) ይዘምሩ ነበር። ፕሬዚዳንት ኬኔዲ በቴሌቪዥን አገረ ገዢዎች ሕግን ማስፈጸም ግዴታ አለባቸው በማለት ንግግር አደረገ ።

የሚሲሲፒ ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ፕሬዚዳንት ኬኔዲን በመጥላት የጥላቻ መፈክር ያሰሙበት ነበር ። ጀምስ መርዲዝ ፍትሕ አግኝቶ ትምህርቱን ቀጠለ ። ፕሬዚዳንት ኬኔዲ የጥቁሮች መብት ተከራካሪዎችን በፊት ለፊት ባይኾን ውስጥ ውስጡን ይረዳ ነበር ። ምክንያቱም የነጮች የበላይነት ስላለ በምርጫ ውድድር ጊዜ በጥላቻ እንዳይጥሉት ስጋት ስላደረበት ነው ። ኪንግ በታሰረ ጊዜ በጉዳዩ ጣልቃ ገብቷል ። የዘር መድልዎ እንዲቀር በሰኔ 19 ቀን

ሐምሌ 2 ቀን 1964 በተተኪው ፕሬዚዳንት ሊንደን ጆንሰን አማካኝነት ፍጻሜ በማግኘት ጸድቋል።

ፕሬዘዳንት ኬኔዲ በተጨማሪ የጠፈር ጉዞ ወደ ጨረቃ መጓዝ ዕቅድና የሰላም ጓድ (Peas Cor) የማቋቋም ዋና ኃላፊነት ነበረበት ። በጥቅምት 1962 ሶቭየት ኅብረት ሚሳኤል ወደ ኪዩባ አመጣች ። ኬኔዲ የባሕር ኃይሉን በማዘዝ ኪዩባ እንዲከበብ አደረገ። 13 አስ ጨናቂ ቀናት በኋላ ሶቭየት ኅብረት ሚሳኤሏን አነሳች ። የታሪክ ሰዎች እንደሚሉት ፤ በምድራችን ክልል የኒኩለር ቦምብ ማፈንዳት ሙከራ እንዳይደረግ ታላቋ ብሪታንያ፣ አሜሪካና ሶቭየት ኅብረት እን ዲፈራረሙ በመሪነት ያከናወነ እሱ ነው ይላሉ።

በ1963 የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለኹለተኛ ጊዜ የአሜሪካንን ሕዝብና እንዲሁም ፕሬዚዳንት ኬኔዲን ጐብኝተዋል።[191]



ፕሬዚዳንት ኬኔዲ እና ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ጥቅምት 1 ቀን 1963፤ ተገናኙ።

[191] Remarks of welcome at Union Station, October 1, 1963

ሥልጣን ከፍተኛ አቀባበል አደርጎላቸዋል ። በአቀባበሉም ሥርዓት ላይ ፕሬዚዳንቱ ስለ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ታላቅነት በማው ሳት አስደናቂ ንግግር አድርጓል።

> በአገራቸው የተከበሩ ብቻ ሳይኾኑ እኛም የምናከብራቸው እና በዓለምም የተለየ የክብር ቦታ የተሰጣቸው ናቸው ። ደግሞም ከተወሰነ ዓመታት በፊት በታሪክ የክብር ቦታ በማግኘት የተረ ጋገጠላቸው ታላቅ መሪ በመኾናቸው እንኳን ደህና መጡ እን ላለን። የሚታወሱበት እና በሠላሰዎቹ ዓመታት አጋማሽ ላይ በዓለም ማኅበረሰብ ጉባኤ (ሊግ አፍ ኔሽን) ስብሰባ በቀረቡበት ወቅት የታየው ንግግርዎ የዓለም ስምምነትን ለማራመድ ረድ ቷል። በዚህ ታላቅ ንጉሣዊ ግርማዊነትዎ ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ለነጻ ሕዝቦች ባንድነት ሊያዋጣ የሚችል ለጋራ ጥቅም የሥራ ዕቅድ ሰጥቷል። በጣም የምናከብረው የመ ሪነት ቦታዎ ነጻ የወጣ እና ራሱን የቻለ ማኅበረሰብ በአፍሪካ ምድር ገንብተዋል።

በሚል የአቀባበል ሥርዓት ላይ ሰፋ ያለ ንግግር አድርጎላቸዋል። በዋሽ ንግተን ከተማ ኹለት መቶ ሺ ሕዝብ ወጥቶ የሚያስደንቅ አቀባበል አድርጎላቸው ነበር።

የክብር እንግዳ ኾነው በዋይት ሀውስ ከፍተኛ አቀባበልና ክብር ተደርጎላቸዋል ። በዚህ ጉብኝታቸው በፕሬዚዳንት ሊንከን መታሰቢያ ሐውልት ስር የክብር የአበባ ጉንጉን አኑረዋል ። በመቀጠልም ጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ በካቶሊክ ኮሌጅ ተገኝተው ክቡስ (ሬቨረንድ) ኤድዋ ርድ ቪሻን የዶክትሬት የክብር ዲግሪ ተቀብለዋል። ከዚያም ወደ ኒው ዮርክ በመጓዝ በናፍቆት ይጠብቋቸው የነበሩት ጥቁር አሜሪካውያን በመንገድ ዳርና ዳር ተሰልፈው ከፍተኛ የኾነ የጀግና የክብር አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ከዚያም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (በዩናይ ትድ ኔሽን) ንግግር አድርገው ወደ ካናዳ ተጉዘዋል።

የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የቅርብ ወዳጅ ፤ ተወዳጁ የአ ሜሪካ ፕሬዚዳንት፤ ለጥቁሮች ነጻነት መብት ተከራካሪ ግርማዊ ቀዳ ማዊ ኃይለ ሥላሴን ካገኙ ከ52 ቀናት በኋላ ኅዳር 22 ቀን 1963 በግ ልጽ መኪና ኾኖ ከባለቤቱ ጋራ በቴክሳስ ግዛት ዳላስ ከተማ ንግግር ለማድረግ ተጓዘ። አቀባበል በሚያደርግለት በሕዝብ በተጨናነቀበት መንገድ መኻል ጥቂት እንደ ተጓዘ ካንድ የትምህርት ቤት መጽሐፍት

ጣጥሮ ራሱን በጥይት መታው።

ኬኔዲ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ዐረፈ። ሊ. ሀርቪ በፖሊስ ተይዞ በሦስተኛው ቀን ከእስር ቤት ወደ እስር ቤት ይዘውት ሲኼዱ ጃክ ሩቢ የሚባል ሰው ከተጨናነቀው ሕዝብ መኸል ወጥቶ በሽጉጥ ሆዱ ላይ መትቶ ገደለው።[192] ሊ. ሀርቪ በፍርድ ቀርቦ የሰጠው ቃል የለም። ሲያዝ የተናገረው ቃል "እኔ አልገደልኩም" የሚል ነበር። በዚህ የተነሳ የፕሬዚዳንቱ ጉዳይ ግልጽ ሳይኾን እስከ ዛሬ ይኖራል። ብዙዎች ከበስ ተኋላው አንድ የስለላ ድርጅት አለ ብለው ያምናሉ ። ብዙዎችም ደግሞ ማንም የስለላ ድርጅት ከጀርባው የለም በማለት ሐሳባቸውን ጥናታቸውን አቅርበዋል።[193]

እንደ ጆን ኦፍ ኬኔዲ ወጣት ፕሬዚዳንት ተመርጦ አያውቅም፤ ሲመረጥ 43 ዓመቱ ነበር፤ የሞተው በ46 ዓመቱ ነው ። በቀብሩ ጊዜ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዋና የክብር እንግድነት ተገኝተው ነበር ። ለክብሩ መታሰቢያ ስድት ኪሎ ባለው ዐዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ሐምሌ 23 ቀን 1970 የኬኔዲ ላይብረሪ ተብሎ መጽሐፍት ቤት በስሙ ተሰይሞለታል።[194]

ፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ ሲሞት በምትኩ የፕሬዚዳንቱን ቦታ የያዘው ምክትሉ የነበረው ሊንደን ጆንሰን ነው። ይህ ምክትል ፕሬዘዳንት በኅዳር 22 ቀን 1963 በሕገ መንግሥቱ መሠረት ቀሪውን ያገለግሉት ዘመን ኬኔዲ በተገደለ ኹለት ሰዓት ባልፈጀ ጊዜ ቃለ መሐላ ፈጽሞ ያለምርጫ ተተካ ። የፕሬዚዳንትነት ኃላፊነቱን ወዲያ ተረክቦ ዋይት ሀውስ በመግባት 36ኛ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ኾነ (1963 - 1969)።

ፕሬዚዳንት ሊንደን ጆንሰን የትውልድ ቦታ በቴክሳስ ግዛት ዳላስ ከተማ ሲኾን እንደ ኬኔዲ የዲሞክራቲክ ፓርቲ አባል ነበር። የክርስትና እምነቱ ዲሳይፕል ኦፍ ክራይስት ከሚባለው የፕሮቴስታንት አንዱ ቡድን ነው።



የደቡብና የሰሜን አሜሪካ የግሪክ ኦርቶዶክስ ሊቀ ጳጳስ ያኮቮስ ሊንደን ጆንሰን ዐዲሱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ቦታ ሲተካ ቃለ መሐላ ሲፈጽምና በዓሉን በጸሎት ሲያጠቃልሉ።

---

[192] Harry Smith., *p., 224*

[193] Jefferson Morley, *Reader's Digest , The New Clue to JFK's M (March 2005) p.88*

[194] **ኹለቱ ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸው ዝነኛ ፕሬዚዳንቶች።**

- አብረሃም ሊንከን ለኮንግረስ ተመርጦ የነበረው በ1846 ነበር። ለፕሬዚዳንትነት የተመረጠው በ1860 ነበር።
- ጆን ኦፍ ኬኔዲ ለኮንግረስ ተመርጦ የነበረው በ1946 ነበር። ለፕሬዚዳንትነት የተመረጠው በ1960 ነበር
- ስማቸው ሊንከን (LINCOLN) እና ኬኔዲ (KENNEDY) ሰባት ፊደላት የያዙ ናቸው ።
- ኹለቱም ለሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ናቸው፤ የኹለቱም ሚስቶች በዋይት ሀውስ በነበሩ ጊዜ ልጅ ሞቶባቸዋል።
- ኹለቱም ፕሬዘዳንቶች በጥይት የተመቱት ዐርብ ቀን ነው፤ ኹለቱም የተመቱት ከበስተኋላ እናታቸውን ነው።
- የሊንከን ጸሐፊ ስም ኬኔዲ ነበር ። የኬኔዲ ጸሐፊ ስም ሊንከን ነበር።
- ኹለቱም በጥይት የተመቱት በደቡቦች ነው። የኹለቱም ተተኪዎች ደቡቦች ነበሩ።
- አንድርው ጆንሰን በሊንከን ቦታ የተተካው የተወለደበት ዘመን 1808 ነበር።
- ሊንደን ጆንሰን በኬኔዲ ቦታ የተተካው የተወለደበት ዘመን 1908 ነው። የአባቶቻቸው ስም አንድ ነው።
- ጆን ዊልኬስ ቡዝ ሊንከንን ገድለሀል ተብሎ የተከሰሰው የተወለደው 1839 ነበር።
- ሊ. ሀርቪ ኦስዋልድ ኬኔዲን ገድለሀል ተብሎ የተከሰሰው የተወለደው 1939 ነበር።
- የኹለቱም ገዳዮች ስም በእንግሊዘኛ 15 ፊደላት የያዘ ነው።
- ዊልኬስ ቡዝ ተኩሶ ከትያትር ቤት ውስጥ ሮጦ የገባው እና የተያዘበት ቦታ በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ነው።
- ሊ. ሀርቪ ተኩሶ ከዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ሮጦ የገባው እና የተያዘበት ቦታ በትያትር ቤት ውስጥ ነው።
- ኹለቱም በፍርድ ቤት ጉዳይ መኾናቸው ሳይፈረድባቸው በሌላ ሰው ተገደሉ።
- ኹለቱም ሕግ ያጠኑ ናቸው፤ ኹለቱም በሚስቶቻቸው አጠገብ ኾነው ነው የተገደሉት። (Wikipedia.org/wiki/List_of_sim

ዓመት ነበር ። በአሜሪካ ፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ከ30 ዓመት በላይ ተባትሮ ያደረገ ልምድ ያለው ፖለቲከኛ ነበር ። በዚህ ልምዱም በጣም ሠራተኛ እንደነበረ ይመሰክርለታል ። በተመረጠ በኹለተኛው ወር ብዙ ነገር ሠራ ። በኬኔዲ ተጀምሮ የነበረውን የጥቁሮች የሰብአዊ መብት እንቅስቃሴ ሕግ የሲቪል ራይት አክት እንዲጠበቅ በ1964 በማጽደቅ ፈረመ ። ትምህርትንና ታክስን በተመለከተ ዐዲስ ሕጎችን ሲያወጣ ፤ ድህነትን ለማጥፋት ደግሞ ዐዲስ የሥራ መርሐ ግብር (ፕሮግራም) አወጣ።

እንደገና በ1964 የፕሬዚዳንት ምርጫ ላይ ተወዳድሮ አሸነፈ። በኰንግረስ ማንኛውም የአሜሪካ ዜጋ የተሟላ ኑሮ እንዲያገኝ የሚያስችል ታላቅ ሕዝብ (ግሬት ሶሳይቲ) የሚለውን ንግግር አደረገ ። ይህም ሀብታምና ደሀ፤ ነጭና ጥቁር ሳይል የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች እንዲሟላለት ማድረግ አለብን የሚል ነው ። በዚህ ሥር ማንኛውም አሜሪካዊ ልጆቹ ጥሩ ትምህርት እንዲማሩ፤ የተመቻቸ ኑሮና በጡረታ ጊዜ ምንም ጭንቀት እንደማይኖርባቸው አደረገ።

ጆንሰንን በዚያን ወቅት ከነበሩት አሜሪካውያን ዘንድ ታላቅ ቦታ ያላሰጠው የቬዬትናም ጦርነት ነው ። የአሜሪካንን ቦምብ የተሸከመ ጀት ሰሜን ቬዬትናም ኮሚኒስት ኾነች ብሎ ደቡብ ቬዬትናም ረድቶ ትእዛዝ እየሰጠ እንዲደበደብ አስደረገ።[195] በዚህ አሳዛኝ ጦርነት ግማሽ ሚሊዮን ወታደሮች በቬዬትናም በመኾናቸው ፤ ከኮሚኒስት ሰሜን ቬዬትናም ጋር ጦርነት ባለመቆሙ በሕዝብ ላይ ቁጣ አስከተለበት። በየሳምንቱ በጦርነቱ ከ200 እስከ 300 የአሜሪካ ወታደሮች ይሞቱ ነበር ። በዚህ ሕዝቡ ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት ጥላቻውን በዘፈን እያደረገ ገለጸበት። የጦርነቱን አላስፈላጊነት በሰላማዊ ሰልፍ ላይ ይናገሩ ከነበሩት አንዱ ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዲሁም የፕሬዚዳንት ኬኔዲ ወንድም ሮበርት ኬኔዲ ነበሩ። እነዚህም ሰዎች የተገደሉበት ዘመን በ1968 ነው ። ኪንግና ሮበርት በአሜሪካውያን ተወዳጅ ነበሩ። በነፍሰ ገዳይ ሲገደሉ በመካከላቸው የነበረው ልዩነት የኹለት ወር ጊዜ ብቻ ነበር።

በዚህ ዓመት ውስጥ ፕሬዚዳንት ጆንሰን ለፕሬዚዳንትነት ውድድር ውስጥ በድጋሚ እንደማይገባ ተናገረ ። በተናገረ በዓመቱ በ1969

[195] Harry Smith., *p., 216*

በኋላም በ1973 በዚያው በሚኖርበት ቴክሳስ ዐረፈ።

## (፫) ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ኒክሰን (ኴከር)

ፕሬዘዳንት ሪቻርድ ኒክሰን የሪፑብሊካን ፓርቲ አባልና የኴከር እምነት ተከታይ የነበረ ሰው ነው ። ሪቻርድ ኒክሰን የትውልድ ቦታው ካሊፎርኒያ ግዛት ከሎሳ አንጀለስ ወጣ ብሎ ዮርባ ሊንዳ በሚባል ቦታ ነው።

ትምህርቱን በዊይቲየር ኮሌጅ ካሊፎርኒያ የተማረ ሲኾን በተጨማሪ በምሥራቅ ክፍል ዱክ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት አጥንቷል። በኮሌጅና በትምህርት ቤት እያለ በጣም ጎበዝ ተከራካሪ ነበር ። በማንኛውም በተሰለፈበት ክርክር ያሸንፍ ነበር ።

በኹለተኛው የዓለም ጦርነት ላይ በባሕር ኃይል ሙያ በመሳተፍ ካገለገለ በኋላ ጦርነቱ ሲያበቃ ወደ ካሊፎርኒያ ተመልሶ መኖር ጀመረ ። በዚያም ለኰንግረንስ 1946 ተመረጠ ። በሪፓብሊካን ፓርቲ ኮሚኒዝምን ኃይለኛ ተቃዋሚ በመኾኑ በጣም ታዋቂነትን አገኘ ። በ1952 ዳዋይት አይሰንሀወር ለፕሬዚዳንትነት ሲመረጥ ምክትል ፕሬዚዳንት (ቫይስ ፕሬዚዳንት) ኾኖ ተመረጦ ለኹት ዙር አገለገለ። በ1960 ከጆን ኤፍ ኬኔዲ ጋራ ለፕሬዚዳንትነት ተወዳድሮ ተሸነፈ ። እንደገና በ1968 ተመልሶ ለፕሬዚዳንትነት ተወዳድሮ የሊንደን ጆንሰን ምክትል ፕሬዚዳንት የነበረውን ሀበርት ሀምፍሬይ የሚባለውን አሸንፎ የአሜሪካ 37ኛ ፕሬዘዳንት ኾነ።[196]

ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ኒክሰን በመጀመሪያ ሕዝቡን ከፋፍሎት የነበረውን የቬዬትናም ጦርነት እንዲቆም አደረገ። በዚህም ተወዳጅነትን አትርፏል ። ከታወቀው የባፕቲስት ሰባኪ ቢል ግርሃም ጋር ወዳጅነት ነበረው ። በዚህ ወዳጅነቱ በኒው ዮርክ በያንኪ እስታዲዮም ቢል ግርሃም ወንጌል ለመስበክ ሲዘጋጅ በቦታው በመገኘት ጉባኤውን በንግግር ከፍቷል።

ፕሬዘዳንት ሪቻርድ ኒክሰን በእንግድነት የኮሚኒስት አገሮችን ቻይናንና ሶቬዬት ኅብረትን ጎበኝቷል።

በ1972 በድጋሚ በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ በከፍተኛ ቁጥር ለፕሬዚዳንትነት ተመረጠ ። ወዲያው በዚሁ ዓመት ውስጥ ግርማዊ ቀዳ

[196] (1969-1974)

ማዊ ኃይለ ሥላሴ ፕሬዘዳንት ኒክሰንና አሜሪካንን ለመጨረሻ ጊዜ ጎብኝተዋል ።

ፕሬዘዳንት ኒክሰን ለኹለተኛ ዙር በከፍተኛ ቁጥር በተመረጠ በኹለት ዓመቱ ነሐሴ 9 ቀን 1974 ከሥልጣኑ ቢሮውን እንዲለቅ ተገደደ። ጉዳዩም በ1972 የነበረው በከፍተኛ ቁጥር የተመረጠው ምርጫ በማጭበርበር መኾኑ ተደርሶበት ነው ። ፖሊሶች ዐምስት ሰዎችን ጭምር በቁጥጥሩ ሥር አደረጉ ። ይህ በናሽናል ዲሞክራቲክ ኮሚቴ የማጭበርበር ሥራ የተፈጸመበት ቦታ በዋሽንግተን ዲሲ ወተርጌት በሚባለው ሕንጻ ውስጥ ነው ። በድብቅ በቴፕ የተቀረጸው የማጭበርበር ሥራ በፌደራል ቢሮ ኦፍ ኢንተሊጀንት (በኤፍ ቢ አይ) ተጋለጠ።[197] በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ወዳጁ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ዋና ሰባኪ ቢል ግርሃም በጉዳዩ ሊገባ ቢፈልግም በማጭበርበሩ ሥራ ውስጥ ፕሬዘዳንቱ የገባበት ስለኾነ ፤ ጥፋቱን ያውቅ ነበረና እንዳይገባ ከልክሎታል ። በኋላም የሴኔት አጣሪ ኮሚቴ እውነቱን አጣርቶ አወጣ ። ነገር ግን ከኒክሰን ጎን የአሜሪካ ሕዝብ ተሰልፎ ስለነበረ በወንጀሉ የገባበት እንዳልኾነ ተደርጎ ሊሸፈንለት ተሞከረ ። አንዳንዶች የታወቁ ረዳቶቹ በአጭበርባሪነታቸው ተፈርዶባቸው ወደ እስር ቤት ገቡ። ፕሬዚዳንት ኒክሰን በመጨረሻ በምክትሉ ፕሬዚዳንት ጀራልድ ፎርድ ተተካ

ፕሬዘዳንት ጀራልድ ፎርድ የአሜሪካንን ሕዝብ ይቅርታ ጠየቀለት። በፕሬዚዳንት ኒክሰን ጊዜ ኒል አርምስትሮንግ እና ኤድዊን አልደሪን በ1969 የመጀመሪያዎቹ ወደ ጠረፍ ላይ በመንዝ ጨረቃ ላይ ደርሰው ዐረፉባት የተባለበት ዘመን ነበር።[198]

ፕሬዚዳንት ኒክሰን ከፕሬዚዳንትነት ሥልጣኑ በወረደ በወሩ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ወረዱ። በኢትዮጵያና በአሜሪካ የነበረው ወዳጅነት ቀዘቀዘ ። በ1974 (መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም.) ወታደራዊ መንግሥት ደርግ ሥልጣን ያዘ ። የመሪነት ሥልጣኑ ሻለቃ በኋላ ኰሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ተተካ። ፕሬዚዳንት ኒክሰን በደም ብዛት ተይዞ ለአራት ቀናት ታሞ ሚያዚያ 18 ቀን 1994 በ81 ዓመት ዕድሜው ሞተ።

[197] Chronicle of the 20th Century. p. 1082 - 1083
[198] George Sullivan., *p., 145*



## (፪) ፕሬዘዳንት ጀራልድ ሩ. ፎርድ (ኤጲስቆፓል)

> ወገኖቼ አሜሪካውያን እኔን በምርጫ ካርድ ፕሬዚዳንት እንድ
> ኾን አልመረጣችሁኝም ። ስለዚህ የምጠይቃችሁ ምርጫች
> ኹን በጸሎታችሁ እንድታጸድቁልኝ ነው።

በማለት የአሜሪካ ሕዝብ በጸሎት እንዲያስቡት ጠየቀ።

ጀራልድ ፎርድ የሪፑብሊካን ፓርቲ አባል እና ኤጲስቆፓል የክርስትና አባል የነበረ ነው ። ግንባሩ ኮስተር ያለ፣ ግልጽ የኾነ ሰው ነበር። የኒክሰን ምክትል ፕሬዚዳንት በመኾን ሲሠራ ቆይቶ ኒክሰን ከሥልጣኑ ሲወርድ ወደ ዋይት ሀውስ ተዛውሮ 38ኛ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት የኾነ ነው።[199]

ፕሬዚዳንት ጀራልድ ፎርድ የተወለደው ኔብራስካ ግዛት ኦሞሀ በተባለ ቦታ ነው። በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዳለ የአሜሪካ የእግር ኳስ ጫወታ ታዋቂ ኮከብ ነበር ። ከሚቺጋን ዩኒቨርስቲ እና ከዬል ዩኒቨርስቲ በሕግ ትምህርት ተመርቋል። በኹለተኛው የዓለም ጦርነት የባሕር ኃይል በመኾን ለዐራት ዓመት ያኽል በደቡብ ፓስፊክ አገልግሏል።

በ1948 ጀምሮ ለኰንግረስ ተመርጦ በተደጋጋሚ ለ12 ጊዜ ያኽል የኰንግረስ አባል ኾኖ አገልግሏል። ፕሬዚዳንት ኒክሰንም ጀራልድ ፎርድ ለምክትል ፕሬዚዳንትነት አብሮት እንዲሠራ በጥቅምት ወር 1973 መረጠው። ኒክሰን ከሥልጣኑ ሲለቅ ጀራልድ ፎርድ ሕዝቡ በሱ ላይ ተስፋውን ጣለ ። በኒክሰን ቦታ በተተካ በወሩ የኒክሰንን ይቅርታ መጠየቁን አምኖበት ተቀብሎታል ። በዚህ የተነሳ ብዙ ትችት ደርሶበታል። የኒክሰንን ሐሳብና ፖሊሲ የሚከተል ነበር።[200]

የካልቪኒስት የክርስትና እምነቱን በግልጽ በሕዝብ እንዲታወቅበት አይፈልግም ነበር። በመጀመሪያ የዳች ካልቪኒስት በኋላ የቦርን አጌን የክርስትና እምነት ተከታይ ነበረ ። በ1976 ለፕሬዚዳንትነት ምርጫ ተወዳድሮ በዲሞክራት ፓረቲ አባልና የቦር አጌን የክርስትና እምነት ተከታይ ጂሚ ካርተር ጋር በቴሌቪዥን ለሦስት ጊዜ ያኽል ተከራክረው በምርጫው ተሸንፏል። ከሠላሳ ዓመት በኋላም ለብዙ ጊዜ ኖሮ በታሕሣሥ 15 ቀን 2006 በ93 ዓመት ዕድሜው ዐርፏል።

[199] (1974-1977)
[200] George Sullivan., *p., 147*